# መለኮታዊ ጠጉር

በጌታነህ ቸርነት (ሊ/ር)

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያው እትም

ሚያዝያ 2004 ዓ.ም

Email: getanehcher@yahoo.com

ፖስታ 55214 አ.አ

# ማ ው ጫ

ገጽ

መቅድም ....................1

1. ጠጉር ....................1
2. የዔሣው ገላ ....................11
3. የዮሴፍ በግዞት ቤት ....................15
4. የኢዮብ መከራ ....................19
5. ከለምጽ መንፃት ....................23
6. የተማረከች ሴት ....................33
7. የአሮን ጢም ....................40
8. የተፈተለ የፍየል ጠጉር ....................47
9. የሶምሶን ጠጉር ....................51
10. ነብዩ ሳሙኤል ....................70
11. ነብዩ ኤልያስና ኤልሳዕ ....................77
12. አቤሴሎም ጠጉር ....................90
13. ሱነማይቱ አቢሻ ....................97
14. የዕዝራ ጸሎት ....................100
15. የሕዝቅኤል ጠጉር ....................108
16. በናቡከደነጾር ላይ የወረደ ቅጣት ....................114
17. የወንድና የሴት ጠጉር ....................118
18. የጽዮን ቈነጃጅት ጌጣጌጥ ....................127
19. በጠጉር የታበሰ እግር ....................134
20. የጌታ ኢየሱስ ጠጉር ....................139

## ምስጋና

ይህን ጽሑፍ እንዳዘጋጅ በጸሎት ለረዱኝ በኮምፒውተር ጽሑፍና በጥቅስ ለቀማ ለተባበረችኝ ለእኅት መሠረት ገ/ኢየሱስ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ::

## መ ቅ ድ ም

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ክብር መልክ የተፈጠረ የእግዚአብሔር የጥበብ ውጤት ነው:: የሰውን ልጅ ተመልክቶ የእግዚአብሔርን ክብር ማድነቅ ይቻላል:: ንጉሥ ዳዊትም ግሩምና ውብ አድርገህ ፈጠርኸኝ በማለት ፈጣሪውን ያመሰግናል:: ለምሳሌ የሰው ልጅ ሰባ አመት ቢኖር ከሰውነት ክፍሎቹ መካከል ልብ ለ70 ዓመታት ሌሊትና ቀን ሳታቋርጥ ያለመለዋወጫና ጥገና ትሠራለች:: በሥጋ መልክ የተፈጠረ ልብ ወይንም ሌላ የሰውነት ክፍል ይህን ያህል መሥራት መቻሉ ፍፁም የሚደንቅ ጥበብ ነው::

የሰው ጠጉር በአብዛኛው በራስ ላይ የሚበቅል፣ አንዷ ቅንጣት ከሌላው ቅንጣት ጋር ሳትጣበቅ ብቻዋን ከጭንቅላት ተነስታ ትበቅላለች:: በሰው ዘመን ሁሉ የማደግ ችሎታዋ የማይገደብ ሲሆን ሁልጊዜ ስርዋን በጭንቅላት ተክላ ለሰው ልጆች ውበትን ወይንም ጭንቅላትን ከአየር ሁኔታ ጋር ለማስማማት ታላቅ አስተዋፅኦ ታደርጋለች::

የሰው ጠጉር አስተዳደግን ስንመለከት አስቀድሞ ወደ ላይ ይወጣል እየጨመረ ሲሄድ አቅጣጫውን ይቀይርና ወደ ታች ተንዠርግጎ ይወርዳል:: ሁልጊዜ ወደታች በመውረድ ውበትን ይጨምራል:: የክርስቲያንም አስተዳደግ ይህንኑ ይመስላል:: በመንፈሳዊ ዓለም ክርስቲያን ራሱን ወደ ታች (ትህትናን) እያደረገ ውበቱ ሳያቋርጥ ዕድሜ መጨረሻ ድረስ እንደ ጠጉር ማደግ ይገባዋል:: ሶምሶንም በእግዚአብሔር የተሰጠውን ጠጉር በሰባት ጎንጉኖ ያኖር እንደ ነበር የክርስቲያኖችም ጸጋ በእግዚአብሔር የሚያድግ ሲሆን እንክብካቤና መጎንጎን ግን የክርስቲያኖች ድርሻ

እንደሆነ ያመለክተናል የተሰጠውን ጸጋ በአግባብ መያዝ ማለት ሴቶች ለጠጉራቸው የሚያደርጉት እንክብካቤ ዓይነት ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት አቋምም የጠጉርን አስተዳደግ ይመስላል። እየመሸ እየነጋ እንደሚያድግ የመንግሥተ ሰማያትም ምሥጢር ለመንግሥት ልጆችም ይኸው ነው። ሁልጊዜ የሚያድግ ሥሩን ከጭንቅላት ላይ ተክሎ ከሌሎች ጠጉር ጋር አብሮ በማደግ ለራስ ውበትን መጨመር የሚችል ጠጉር ነው። ምንም እንኳ አንዲት ቅንጣት ጠጉር ከጭንቅላት ብትበቅልም ብቻዋን ውበትን አታላብስም። ከሌሎች ቅንጣት ጋር ስትሆንና ስትበዛ በአንድነት የምታጎናፅፈውን ውበት መመልከት ይቻላል።

ይህ ጽሁፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ መለኮታዊውን ጠጉር ለማሳየት የታሰበ ነው። ጠጉርን በተመለከተ የተጻፈልን ተመልክተን እኛም ይህንኑ የመለኮት ውበትና ጸጋ እንድንከባከብ የታቀደ ሲሆን ሁሉ ክርስቲያን መለኮታዊውን ጠጉር በወጉ ተመልክቶ በሰማይ ያለውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጠጉር ይመስል ዘንድ ነው። በምዕራፍ አንድ ላይ ጠጉር ማለት በአጭሩ ምን ማለት እንደሆነ ከመጽሐፍ የተገለጠው ፍቺ ቀርቧል። ከምዕራፍ 2 እስከ መጨረሻው ደግሞ በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ አሳብ ነው።



# 1. ጠጉር

ጠጉር ማለት ክር የሚመስል መዋቅር ከአጥቢዎች ሥጋ ላይ የሚበቅል ነው። ብዙ አጥቢዎች ወፍራም የጠጉር ካባ ሲኖራቸው በብዛት ሙቀት ለመጠበቅ ይጠቀሙበታል። ብዙ ዝርያዎች ደግሞ የተለየ ጠጉር ሲኖራቸው የስሜት ሕዋሶቻቸውን ለመከላከያ ይጠቀሙበታል። በሰዎች ልጆች ዘንድ ግን ጠጉር በአብዛኛው ለውበት (Cosemotics values) ይውላል።

የሰዎች ከውጫዊው አካላቸው ላይ ጠጉር ሲበቅል በአብዛኛው ቦታ የሚበቅሉት ግን ልል የሆነ ቀለማትን የያዘ ለዓይን የማይታዩ ናቸው። ጠጉር በአብዛኛው ከጭንቅላትና በአንዳንድ የሰውነት ክፍል ላይ ሲበቅል በእጅ መዳፍና በውስጥ እግር ብቻ መብቀል አይችልም። በዓይን፣ በጆሮዎችና በአፍንጫ አካባቢ የሚበቅሉ ጠጉሮች የሚውሉት ለከለላ ነው። አፈር፣ በራሪና አንዳንድ ነገሮች እንዳይገቡ ይከላከላሉ። በተጨማሪም በዓይን ዙሪያ የሚበቅሉ ሽፋሽፍት (Eye borowes) በዓይን ላይ ሊገቡ ያላቸውን የብርሃን ጨረር ኃይል ለመቀነስ ይረዳሉ።

በአንዳንድ አጥቢ እንስሳ ዘንድ (ከሰው በተለየ) የተለየ ጠጉር ዓይነት ሲኖራቸው የሆነ ነገር ጠጉራቸውን ሲነካ ጠጉሩ መልስን (Respond) ይሰጣል። ብዙ የነርቭ ህዋሶች በነዚህ ጠጉር ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። እነዚህም በሳይንስ ዊስከርስ (Whiskers) ይባላሉ። ዊስከርስ በከንፈርና በጉንጭ ላይ በአብዛኛው ሲበቅል በሌሎችም የሰውነታቸው ክፍል ላይ ሊበቅሉ ይችላሉ። እነዚህ ዓይነት ጠጉር ያላቸው እንስሶች መንገዳቸውን በጠባብና በጨለማ ጉዞራ

ለመጠብጠብ ይጠቀሙባቸዋል:: አንዳንድ እንስሶች የጠጉራቸው ቀለማት ከአካባቢው ጋር በማመሳሰል ከጠላቶቻቸውና ከአዳኞቻቸው ለመሠወር ይጠቀሙበታል:: ጠጉር ከጡጫና ሰውነት ላይ ከሚወድቅ ነገር በመከላከል አካል እንዳይጎዳ ይረዳል::

አምራቾች የእንስሳትን ጠጉር የተለያዩ ቁሳቁሶችን ያበጁበታል:: ወፍራምና በለስላሳ ጠጉር ኮትና የሚሞቅ መደረቢያ ይሠሩበታል:: የበግ ጠጉርን ወደ ልዩ የሱፍ ክር በመቀየር ብርድ ልብስ፣ ልብስና ሌሎች ቁሳቁሶች ይመረቱበታል:: የውሻን ጠጉር በመጠቀም የተለያየ ዓይነት ብሩሽ ይመረታል::

## የጠጉር መዋቅርና አስተዳደግ

## (The Structure & Growth of Hair)

ከቆዳ በታች በሥጋ ውስጥ ያለ የጠጉር ክፍል የሚያርፈው ቦርሣ በሚመስል መዋቅር ሲሆን ይህም ፎሊክል (Folicle) ይባላል:: የጠጉር ሥር ከታች በኩል የሚገኝ የጠጉር ክፍል ሲሆን ሰፋ ብሎ ተዋቅሮ ለስላሳ የሆነ ቀለል ያለ ቀለም የያዘ የጠጉር ባልብ (Hair Bulb) በመባል ይታወቃል:: እንግዲህ ጠጉር ከባልብ ውስጥ በፍጥነት ከሚራባ የጠጉር ህዋስ (Cells) የሚበቅል ነው:: ፓፒላ (Papila) የሚባለውም የጠጉሩ መዋቅር ፎሊክል በሚባል ከጠጉር ክፍል በታች ይስፋፋል:: ፓፒላ የሚባለው የሚያቅፈው አገናኝ ቲሹ (Connective tissue) ለጠጉሩ እድገት የሚጠቅሙ የደም ቧንቧዎችን ነው::

በጠጉሩ ውስጥ የህዋሳት (Cells) ቁጥር ሲጨምር አስቀድሞ የተፈጠሩ ህዋሳት ለአዲሱ ለተፈጠሩት ሥፍራ በመልቀቅ ወደ ላይ ከፍ ይላሉ:: ቀድሞ የተፈጠሩ የጠጉር ህዋስ ወደ ላይ ከፍ ባሉ ቁጥር



ምግብ ከሚያቀብላቸው የደም ሥር እየራቁ ይሄዳሉ ከዚያም ጠንከር ወዳለ የፕሮቲን ክምችት ይቀየራሉ ይኸም ከራቲን (Keratin) በመባል ይታወቃል:: ይህ ፕሮቲን በአጥቢ እንስሳት ጥፍር፣ (Claws) በተሳቢ እንስሳ ቅርፊትና በወፎች ላባ ይገኛል:: የከራቲን በዚህ መልክ የመከማቸት ሂደት በእንግሊዝኛው ቋንቋ Keratinization በመባል ሲታወቅ በዚህ ሂደት ውስጥ የጠጉር ህዋስ በሙሉ ይሞታሉ:: የዚህ ሂደት ተካሂዶ የሚያልቀው ከቆዳ በታች ነው:: የዚህ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ያለው የጠጉር ክፍል አምድ (Shaft) በመባል ይታወቃል::

በነዚህ በሞቱ የጠጉር ህዋሳት አካል ሦስት የተለያዩ መደቦች በጠጉር አምድ ላይ ይገኛል:: የውጪ አካል ኩቲክል (Cuticle) ሲባል ከኩቲክል በታች ኮርቴክስ (Cortex) በመባል ሲታወቅ ፒጋመንትን (Pigament) ሲይዝ ይኸውም የጠጉርን ቀለም ይወስናል ከዚህ በታች ኮር (Core) የሚባል የውስጠኛ መደብ ይገኛል::

ብዙ የጠጉር ፎሊክል ዘይት የሚያመነጭ ግላንድ (Oil gland) ሲኖራቸው ለፎሊክል ዘይትን ያመርታሉ:: ይህ ዘይት በጠጉር ላይ በመፍሰስ ጠጉርን ያለሰልስና ወደ ፈለገው በቀላሉ እንዲንቀሣቀስ ይረዳዋል::

አርክተር ፒል (Arrector pill) ተብሎ የሚታወቀው የጠጉር ጡንቻ ከቆዳ በታች የሚገኝ ሲሆን በብዙ ጠጉር ፎሊክል አንፃር ይገናኛል:: ይህ ጡንቻ ሲኮማተር ጠጉር በጫፍ እንዲቆም ያደርጋል በዚህን ጊዜ ብዙ ጠጉር የተላበሰ አካል ያላቸው አጥቢዎች ዓየርን ከውጭ በመያዝ ወደ አካል እንዲሰርጽ ያደርጋሉ በዚህም ተስማሚ

የሙቀት ሁኔታን በሰውነት ውስጥ ይፈጥራል። የዚህ የጠጉር ጡንቻ እንቅስቃሴ ሲያደርግና ጠጉር ሲቆም እጥቢ እንስሶች ተፈሪ ያደርጋቸዋል። የሰው ልጆችም ሲበርዳቸውና ሲፈሩ የዚህ የጠጉር ጡንቻ መጨማደድ ሁኔታውን ለመቋቋም ይረዳቸዋል።

## የጠጉር ቀለምና ዓይነት

## (Color & Texture)

የጠጉርን ቀለም በአብዛኛው የሚወስነው የቡኒ ጥቁር ፒጋመንት ይኸውም ሚላኒን (Milanin) በመባል የሚታወቀው የስርጭት መጠን ነው። በብዙ ሰዎች ዘንድ ደግሞ የሚታይ ቢጫማ ቀይ ጠጉር የሚታየው የሚላኒን ስርጭት በሚቀንስበት ወቅት ነው። ብዙ ሰዎች የጠጉራቸው ቀለም ወደ ግራይ ወይንም ሲያረጁ ነጭ ይሆናል ይኸውም የፒጋመንት መፈጠር ሲቆም ነው።

የጠጉር ዓይነት (Texture) በአብዛኛው የሚወስነው በጠጉሩ ቅርፅ ሲሆን የጠጉርን ክፍል በአጉሊ መነጥር መመልከት ይቻላል። ቀጥ ያሉ ጠጉር ክብ ቅርፅ ሲኖራቸው (Wavy & curly) ጠጉሮች ደግሞ ጠፍጣፋ ናቸው። በጠጉር ዕድገት ወቅት (Cycle of hair growth) በፎሊክል ውስጥ የሚበቅለው ጠጉር ወቅትን ጠብቆ ነው። ጠጉር በአንድ ወቅት ይበቀላል በአንድ ወቅት ደግሞ በፎሊክል ውስጥ ሳይንቀሳቀስ ይከርማል።

የጠጉር ርዝማኔ የሚወሰነው የፎሊክል የዕድገት ዘመን ጋር የሚሄድ ነው። በሰው ራስ ሥር የጠጉር ፎሊክል ከሁለት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት ያህል ያድግና ለሦስት ወራት ደግሞ ረፍት በመውሰድ ከዕድገት ይታቀባል። የጭንቅላት ጠጉር በወር ከአስራ



ሦስት ሚሊሜትር በታች ያድጋል። አጫጭር ጠጉር ተብለው በሰውነታችን ክፍል የሚገኙ እንደ ሽፋሽፍትና ቅንድብ ለአሥር ሳምንታት ያህል ብቻ ያድጉና ለዘጠኝ ወራት ከዕድገት ይታቀባሉ።

የሰው ጭንቅላት በአማካኝ 100 ሺ የጠጉር ቅንጣት ይይዛል። ከዚህ ውስጥ ከ5-15% የሚሆኑት ጠጉሮች ደግሞ በማንኛውም ጊዜ ከዕድገት ታቅበው ይኖራሉ። ከነዚህም ከቆሙት መሀል ከ70-100 የጠጉር ቅንጣቶች በየቀኑ ከጭንቅላት ይወድቃሉ። ለጠጉር ዕድገት ተፅዕኖ የሚያደርጉ እሉ ዕድሜ፣ አመጋገብ፣ አጠቃላይ ጤንነትና የወቅቶች መፈራረቅ ዋናዎቹ ናቸው። ለምሳሌ በልጆች ላይ ቶሎ ሲበቅል በትልልቆች ደግሞ ይዘገያል። በዓመት ካሉ አራት ወቅት በክረምት በጣም ያድጋል። በማንኛውም የሰውነት ክፍል የሚገኝን ጠጉርን መስተካከልና መላጨት ለጠጉር ዕድገት ወይንም መጠን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

## የጠጉርና የጭንቅላት ቆዳ ቀውስ

መላጣነት የሚመጣው በቆዳ ውስጥ ያለው ፎሊክል ሲሞትና አዲስ ጠጉር ማብቀል ሲሳነው ነው። መላጣነት በአብዛኛው ከዘር የሚተላለፍ ነው ነገር ግን ሌሎች ምክንያቶች እንደ የቆዳ መቆጣት (Infection) የመድኃኒት መስተጋብር፣ የፀሐይ ጨረር ይህን ሊያስከትል ይችላል። በዘር የሚተላለፍ መላጣነት ከሴቶች ይልቅ በወንዶች ያመዝናል። ይህ ከዘር የሚተላለፍ መላጣነት ሊድን አይችልም።

ሌሎች ጉዳዮች በሽታና እርግዝና፣ የጠጉር በፎሊክል ውስጥ የመብቀያ ወቅትን ሊያዛባው ይችላል። በበሽታና በእርግዝና ወቅት ለጥቂት ጊዜ ብቻ ጠጉር በፎሊክል ውስጥ እንዲበቅል ያደርጉትና

ክለብ ጠጉር (Club hair) የሚባለውን ዓይነት ያመርታል ይህ ክለብ ጠጉር የሚባለው ለተወሰነ ጊዜ ሽፋንን ይፈጥርና ጠጉር እንዲሳሳ ወይንም መሳሳ እንዲሆን ያደርጋል:: ይህ ዓይነት ጉዳት ግን ዘለቄታዊ ሳይሆን ከዚህ ነገር ሰዎች ሲላቀቁ አዲስ ጠጉር የመብቀል ውህደትን በጤናማነት ይቀጥላል::

ከጭንቅላት ውጭ በሌሎች የሰውነት ክፍሎች ውስጥ ከመጠን ያለፈ ጠጉር ሊበቅል ይችላል ይኸውም ከዘር ወይንም ከህክምና ጋር ተያያዥነት ያለው ችግር ነው:: እነዚህ ጠጉሮች እንዲወገዱ ከፈለግን ሊወገዱ ይችላል ይህንን የማስወገድ ዘዴ ኤሌክትሮላይስስ (Electrolysis) ይባላል በዚህ ዘዴ ፓፒላ (አስቀድሞ እንደጻፍነው ፓፒላ የጠጉር ሥር ከደም ሥር የሚገናኝበት ስፍራ ነው) በኤሌትሪክ መርፌ በመውጋት አዲስ ጠጉር እንዳይበቅል ማድረጊያ ነው:: ከቆዳ በላይ ያለውን ጠጉር ብቻም ማስወገድ ይቻላል ይህም ዲፕላቶሪ (Diplatory) የሚባል ፈሳሽ ሙጫ ጠጉሩ ካለበት ቆዳ ላይ መቀባት ነው:: ነገር ግን ይህ ዘዴ የጠጉሩን ሥር ስለማያገኘው ከጊዜ በኋላ መልሶ ጠጉሩ ያድጋል::

ሌሎች የጭንቅላት ቆዳ ቀውስ ፎሮፎር (Dandruff) ወይንም ቆሮቆር፣ ቀለበት ተውሳክ (Ring worm) የጠጉር ቅማልና ቅጫም ናቸው:: ዳንድሩፍ የቆዳን ቅርፊት በመላጥ ከቆዳ ላይ ይራገፋል ይህ ብቻ ጠጉርን ሊያጠፋ አይችልም ነገር ግን ከሌሎች በሽታ ጋር ከተዛመደ የጠጉርን ፎሊክል በመጉዳት ፈጽሞ ጠጉርን ሊያጠፋ ይችላል:: የቀለበት ተውሳክ የሚባለው በሽታ የሚመጣው ደግሞ ጥቃቅን ህዋሳት ያቀፈ ፈንገስ ሲሆን ይህም የጠጉር ኮርቴን የተባለውን ይበላል ጠጉር ይሰባበራል በመሆኑም ቆዳን ባዶ



ያደርጋል:: የጠጉር ቅማል የቆዳን ደም በመምጠጥ እንቁላሉን በጠጉር ፎሊክል ውስጥ ይቀብራል::

## የጠጉር ሥራ

## (Hair Dressing)

የጠጉር ሥራ ጠጉርን ማጠብ፣ መቁረጥ፣ ማስተኛት፣ መተኮስ፣ ማድረቅ፣ ማስተካከልና የመቆጣጠር ኪን ነው:: ሴቶችና ወንዶች ጠጉራቸውን በማስዋብ (Style) ውበታቸው እንዲጨምርና ምኞት እንዲሰጣቸው የሚያደርጉበት ጥበብ ነው:: ማንኛውንም የውጭ አካል ለውጥ ለማድረግ ሲሞክር እንደ ጠጉር የሰውን ገጽታ የሚቀይር የለም:: የጠጉር ሥራ የሰው ልጆችን መልካም ገጽታ የሚፈጥር ሲሆን የማያምርን ተክለ ሰውነት የመደበቅ ታላቅ ችሎታው ከፍተኛ ነው:: ወይንም የማያምርን ማንነት አስትቶ እርሱን ብቻ እንዲመለከቱት የማድረግ ችሎታ አለው:: ከሰዎች የሰውነት ክፍል ውስጥ ጠጉር ወደ ፈለጉት አይነትና ቅርፅ ለመቀየር ቀላል ነው:: ጥንት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንኳ ሰዎች ጠጉራቸውን ይቆርጣሉ፣ ያበጃጁታል፣ ቀለም ይነክሩታል፣ በተጨማሪም በፈለጉት ዓይነት ይሠሩታል:: ፕሮፌሽናል የጠጉር ሠራዎች በግልጥነት መታየት የጀመሩት በ1700 ዓ.ም ወዲህ ነው ዛሬ ብዙ ሴቶችና ወንዶች በዚህ ሁኔታ የተካተቱ ናቸው:: ለዚህ አገልግሎት ማለትም ለመቁረጥ፣ ለመቀባት፣ ለማቆም፣ ለመተኮስ የሚያስችል ሙያ አስዋቢዎች (Beautifires) ውበት መካኒኮች (Beauty operators) ኮስሞቶሎጂስት (Cosmotologist) እና ጠጉር ስታይሊስት (Hair stylists) ተብለው ይጠራሉ::

ከ1700 ዓ.ም ወዲህ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች የሚያስደንቅ የጠጉር ሥራዎች የታየበት ዘመን ነው። በተለይም ሴቶች ጠጉራቸውን በነጭ መሳይ ዱቄት በመቀባትና በላባ በማስጌጥ፣ የጠጉር ቀለበት፣ ጌጣጌጥ በማከል ያስውቡታል። አንዳንድ ጊዜ ለጠጉራቸው ውበት (Style) የሚጠቀሙበት ዘዴ በጣም ውስብስብ ከመሆኑና ያወጡትም ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ውበቱና ጌጣጌጦቹ እንዳሉ እንዲቆዩላቸው ለብዙ ሳምንታት ጠጉራቸውን ሳይታጠቡና ሳያበጥሩ ይከርማሉ።

ወንዶች ጠጉራቸውን በዊግ ይሸፍኑታል። ታይ ዊግ የሚባል ስታይል መጠቀም የጀመሩት ከ1600 ዓ.ም ወዲህ ሲሆን ይህን ከተጠቀሙ በኋላ በጠጉር ማሰሪያ ወደ ኋላ ያስሩታል። በ1800 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ቀለል ያሉ የጠጉር ማስዋቢያ ነገሮች ተፈለሰፉ። በ1870ዎች የፈረንሳይ ጠጉር ሰሪ ማርሰል ግሬቱ የተባለው ማርሰል መተኮሻ ሲፈለስፍ በሙቀት የሚያገለግል መተኮሻ በቀላሉ አመረተ። የፈረንሳይ ጠቢብ አሌክሳንደር ጎድፍሮይ ደግሞ የጠጉርን ማድረቂያ ማሽን በ1890 አስተዋወቀ። ከ1890 አካባቢ ዘመናዊ የተባሉ ሴቶች ጠጉራቸውን በስሱ ወደ ላይ በማቆም የጊብሰን ልጃገረዶች ውበት በሚል ቅፅል አስተዋወቁት።

በ1940ዎቹ ደግሞ ብዙ ሴቶች ሺፐዶግ ወይንም ቬሮኒካ ሀይቅ የተባለውን ዓይነት አቆራረጥ መጠቀም ጀመሩ። ይህም ረጅም ጠጉር ሆኖ አንድ ዓይንን የሚከልል ዓይነት ነው። በ1960ዎቹ ደግሞ ጠጉራቸው እንዲዋብላቸው የአበጣጠር ሁኔታን በመቀየር ከጠጉር ጫፍ ይጀምሩና ወደ ቆዳቸው አቅጣጫ በተቃራኒው ማበጠር ጀመሩ ይህም የኋላ ማበጠር (Back combing) ይባላል።



እንግዲህ በሰለጠኑት አገሮች ጠጉር ለብቻው የተለየ የሳይንስ ዘርፍ ሲሆን በዚህ በከፍተኛ ምርምርና ጥናት በማሰልጠን በተለያዩ ዲግሪ ያስመርቃሉ። በዘርፉም ልዩ አስተዋጽኦ ላበረከቱና ለጠጉር ጥንቃቄና ውበት የሚውሉ መገልገያ መሣሪያዎችንና ቅባቶችን የሚያመርቱ ስማቸው በመዝገብ ለታሪክ ይቀመጣል። አንድን ምዕተ ዓመት፣ ዘመን፣ ወቅት፣ የሃገር ባህል፣ ወዘተ ከፎቶግራፍ ላይ በሚገኝ የጠጉር ቅርጽና የውበት አደረጃጀት ተመልክቶ የታሪክን ፍሰት ማወቅ ይቻላል። እንግዲህ የሳይንሱ ዓለም ይህን ያህል ጥልቀትና ክብደት ሰጥቶ በሰለጠነው ዓለም ልዩ ትኩረት ከተሰጠው ፈጣሪያችንን ለዚህ የጠጉር ጉዳይ ወስደን ማድነቅ፣ እውቅናን መስጠት (due to acknowlegement) ከዚያም ከዚህ በተፈጥሮ ጠጉር ተነስተን የውስጥ መለኮት ያስቀመጠውን ጸጋ ለማወቅና ምን ሁኔታ ላይ እንዳለን ማጥናት ተገቢ ይመስለኛል።

በተጨማሪም ለአንድ የጠጉር ቅንጣት ህዋስ የሚመግብ የደም ሥር፣ ፓፒላ፣ የጠጉር በልብ፣ የጠጉር ጡንቻ፣ የጠጉር ግላንድ (subcutaneous gland) ሚዱላ፣ ኮርቴክስ፣ ኩቲክል፣ የከርቲናይዜሽን ስፍራ፣ ሻፍት ወዘተ ከተዘጋጁና ሁሉም ለአንዲት ቅንጣት ጤናማነት የሚሠሩ ከሆነ በውኑ ሁሉን የሚችልና የሚያውቅ እግዚአብሔር በራሱ አምሳል የፈጠረውን የሰውን ልጅ በስሙ፣ በማንነቱ ቢያውቀው የሚያስደንቅ ነገር ነው? ለዚህም አይደል ክርስቶስ "የራሳችሁ ጠጉር እንኳ ተቆጥሯል" በማለት የተናገረው። እግዚአብሔርም ስለ ያዕቆብ በሐዘኔታ ሲናገር "ያዕቆብ ሆይ፥ እስራኤልም ሆይ፥ መንገዶ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች ፍርዶም ከአምላኬ አልፋለች ለምን

ትላለህ? ለምንስ እንዲህ ትናገራለህ? አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ÷ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም÷ አይታክትም÷ ማስተዋሉም አይመረመርም::" (ኢሳ. 40÷27-28)

ከዚህ በላይ እንዳየነው ታላቁ የሳይንስ ዓለም የሚፈትሸው መጽሐፍ Encyclopidia Britanica ስለ ጠጕር ሲናገር በዘር የሆነ የጠጕር መላጣነት ሊድን አይችልም ይለናል:: እንግዲህ በፍጥረት ላይ የሰዎች ደካማ ችሎታ (Impotence) ይህን ያህል ነው:: በተዘጋጀ ራስ በራ ላይ አንዲት ቅንጣት የማብቀል ችሎታ የለውም:: ስለ ክሎኒግ (Cloning) ተፈጥሮን የመቆጣጠር ችሎታ አለኝ የሚል ፍጥረት ጎበዝ ከሆነ አንድ የጠጕር ቅንጣት ያውም በተፈጠረ ሰው ላይ ማብቀል ይቻል? የበቀለን ጠጕር ግን ከላይም በቅባት ከታችም በኤሌክትሮላይስስ ማጥፋት ይቻላል:: እንግዲህ የሰው ልጅ መፍጠር ሳይሆን የማጥፋትን ችሎታ እንዳለው ካወቅን ሁሉ ሰው ሁሉን ማድረግ ወደሚችል ጌታ መቅረብ የሰብዕናው ሁለንተናው ነው::

ከላይ የተገለጸው ጽሑፍ አሳብ የተወሰደው Encyclopidia, Volume 9, Chicago, World Book, Inc. a Scott Fetzer Company, Chicago, Printed in the USA ነው::



## 2. የዔሳዉ ገላ

"ያዕቆብም ርብቃን እናቱን አላት፡ እነሆ ዔሳው ወንድሜ ጠጕራም ሰው ነው፤ እኔ ግን ለስላሳ ነኝ፡ ምናልባት አባቴ ቢዳስሰኝ በፊቱ እንደሚዘብት እሆናለሁ፡ መርገምንም በላዬ አመጣለሁ፡ በረከትን አይደለም:: እናቱም አለችው፡- ልጄ ሆይ፡ መርገምህ በእኔ ላይ ይሁን፡ ቃሌን ብቻ ስማኝ፡ ... ርብቃም ... የዔሳውን መልካሙን ልብስ አመጣች÷ ታናሹን ልጅዋን ያዕቆብንም አለበሰችው፡ የጠቦቶቹንም ለምድ በእጆቹና በለስላሳው አንገቱ ላይ አደረገች፡ ... ይስሐቅም ያዕቆብን፡ ልጄ ሆይ፡ አንተ ልጄ ዔሳው እንደ ሆንህ ወይም እንዳልሆንህ እዳስስህ ዘንድ ቅረብኝ አለው:: ያዕቆብም ወደ አባቱ ወደ ይስሐቅ ቀረበ፤ ዳሰሰውም፡ እንዲህም፡ ይህ ድምፅ የያዕቆብ ድምፅ ነው፡ እጆች ግን የዔሳው እጆች ናቸው አለው:: እርሱም አላወቀውም ነበር፡ እጆቹ እንደ ወንድሙ እንደ ዔሳው እጆች ጠጕራም ነበሩና፡ ስለዚህም ባረከው።" (ዘፍጥ. 27፥11-24)

### 2.1. የዔሳው እጆች

ዔሳው ከሰውነቱ ክፍል በዋንኛነት የሚለየው በእጁ ላይ ያለው ጠጕር ነው:: የበግ ጠቦት በጠጕር እንደተሸፈነ ዔሳውም እንደዚሁ ነው:: ዔሳው በኵር በመሆኑ የአባቱ የይስሐቅ በረከት ወደ እርሱ ነበር:: ሰውነቱ በሙሉ ጠጕራም በመሆኑም የጸጋ ሁሉ ባለቤት ይመስል ነበር:: ታናሹ ያዕቆብ ደግሞ በተቃራኒው ለስላሳ ገላ ያለው ሲሆን ክፉና ደግ ሳያውቁ ከወንድሙ ጋር በሆድ ይገፋፉም ነበር:: የሁለቱን ከፍተኛ መገፋፋት የእናታቸውን ልብ ከጅምሩ አሳዘኑ::

"ልጆችም በሆድዋ ውስጥ ይጋፉ ነበር፡ እርስዋም፡ እንዲህ ከሆነ ይህ ለእኔ ምኔ ነው? አለች።" (ዘፍጥ. 25፡22) ገና በዕንስ ወራት የተጋፉ ሲወለዱ እንዴት ይሆን? "ከዚያም በኋላ ወንድሙ ወጣ፡ በእጁም የኤሳውን ተረከዝ ይዞ ነበር፤ ስሙም ያዕቆብ ተባለ።" (ዘፍጥ. 25፡26) እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባን የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ ምንም እንኳ በመለኮት ምሪት ቢከናወንም 20 ዓመት ሳትወልድ ቀርታ በጸሎት ዕንስን አገኘች ከዚያም በጽንስ ወቅት ታላቁ ግፊያ በሆዷ ተከናወነ ይህስ ለምኔ ነው እስከ ማለት ተማረረች በመሆኑም ምንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ወደ ጋብቻ ቢመጡ በጊዜ አለመውለድና በጽንስ መጨናነቅ ሊሆን ስለሚችል ወደ ሌላ ውስብስብ ጉዳይ ልንገባ አይገባም። የያዕቆብ ሚስት ራሄል በመንገድ በምጥ እንደሞተችም አንዘንጋ።

ዔሳውና ያዕቆብ በዕንስ ወቅት እናታቸውን እስኪያስጨንቁ ድረስ ተጋፉ። የግፊያውም ዋንኛ መንስዔ ብኩርና ነበር። ይህ ሁሉ ሁኖ የርብቃ መውለጃ ወቅት ሲደርስ ባለጠጉራሙ ፈጥኖ ወጣ። ይህም ያዕቆብን አሳዘነው ማድረግ የሚችለውን አደረገ በእጁ የዔሳውን ተረከዝ ያዘ። ክፉ ደጉን ሳያውቅ ተረከዝ ያዘ።

የዔሳው እጅ በያዕቆብ ተለወጠ ማለትም ያዕቆብ በእጁ ብዙ ጠጉር እንዳለው በመምሰል በረከትን ወረሰ። ይስሐቅ በኤሳው እጅ ላይ ባለው ጠጉር ምልክት ለመባረክ እንደ ተነሳ በእግዚአብሔርም ዘንድ በእጆቻችን ላይ ያለው መለኮታዊው ጠጉር መጠበቅ ይገባናል። ያዕቆብ የአባቱን ልብ አወቀ።



የያዕቆብ ፍራቻ አንድ ነበር አባቴን ባርከኝ ብዬ ወደ እርሱ ስገባ አባቴ አንድ ጥያቄ ይጠይቀኛል ወደ እኔ ቅረብና ልዳስስህ ይለኛል። የያዕቆብና የዔሳው ድምጽ ልዩ ልዩ ነው። ይስሐቅ በዚህ ማስረጃ እንደማያውቅ ያዕቆብ ያውቃል። ያዕቆብ እንደፈራው ደረሰ ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ ማንነትህን ለመለየት ወደ እኔ ቅረብ አለው። ርብቃ አስቀድማ ያመቻቸችው የጠቦት ጠጉር ያዕቆብ ይስሐቅን አታለለበት። ያዕቆብ በዚህ ዋናውን በረከት ከይስሐቅ በእምነት ተቀበለ። "ዔሳውም የአባቱን ቃል በሰማ ጊዜ ታላቅ እጅግም መራራ ጩኸት ጮኸ፡ ... በእውነት ስሙ ያዕቆብ ተባለ፡ ሁለት ጊዜ አሰናክሎኛልና፡ ብኩርናዬን ወሰደ፡ አሁንም እነሆ በረከቴን ወሰደ።" (ዘፍጥ. 27፡34-36)

ዔሳው ሁለት ጊዜ እንደተሰናከለ በራሱ አንደበት ተናገረ። የዔሳው ዋንኛ ችግር ምንድነው። በጽድቅና በቅድስና መመላለስ የቻለ ሰው ነበር? ወይስ ብኩርናም በረከትም አይገባውም? በአዲስ ኪዳን ይህ ሰው ተጠቅሷል። "የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ... ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ። ... በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ስፍራ አላገኘምና።" (ዕብ.12፡15-17) የእግዚአብሔር ጸጋ በዔሳው ነበር። ዔሳው በኩርም ነበር ይህ ሁሉ ሆኖ ግን መራራ ሥር በነፍሱ በመብቀሉ ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው ሆነ የእርሱም እንባ ዓለማዊነቱን አልሻረውም። እግዚአብሔር ዔሳውን ሲፈጥረው ባለሙሉ ጸጋ አድርጎ ነበር ለዚህም ዋንኛው ማስረጃ መላ

ሰውነቱ ጠጉራም ነበር። በይስሐቅም ይወደድ ነበር የዚህ ዓለም ፍቅር ይህን ሁሉ አስጣለው።

ክርስቲያንም በሰውነቱ ሁሉ መለኮታዊው ጠጉር ቢኖረውም በዚህም የይስሐቅን በረከት ለማግኘት ቢሞክርም ይህን ዓለም ከተመኘና መራራ ሥር በነፍሱ ከበቀለ ከእንባ አይወጣም። ለስላሳ የሆነው ሰው በረከቱን በቀላሉ ይቀበላል። ለስላሳ የሆነ ሰው የበጉን ጠጉር በሰውነቱ በመክደን የእግዚአብሔርን በረከት ይቀበላል።

ያዕቆብ የዔሳውን ጠጉር በማስመሰል ወደ አባቱ ደፍሮ በመግባቱ ይስሐቅ ተደባለቀበት። ከድምፅ ይልቅ በእጅ ላይ ያለው ጠጉር አየለ በዚህም ባረከው። በእርግጥም ከድምፃችን ይልቅ በእጃችን ያለው ጠጉር ማንነታችንን የበለጠ ይገልጠዋል። ርብቃ መርገሙ በእኔ ይሁን በማለት ያን ያህል ፍቅር ለያዕቆብ መኖርዋን አሳወቀች ነገር ግን የልጇንም መጨረሻ ሳትመለከት ሞተች።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ ራሱን በእግዚአብሔር በግ አስመስሎ በሽላቶቹ ፊት ዝም ብሎ ታረደ የዚህን በግ ቆዳ በላያችን በመልበስ ከጽድቅ የራቀ የነበረውን ገላ በዚህ እንሸፍነው። እግዚአብሔር የአዳምን ገላ በቁርበት እንደሸፈነ የኛም ገላ በሙሉ ጠጉር ይከደን ዘንድ የእግዚአብሔርን በግ እንልበስ በኩር ልጅ በመሆኑ የእርሱን ማንነት በኛ ተፈፃሚ ይሆናል። እርሱ በሽላቶቹ ፊት ዝም እንዳለ እኛ ግን በጌታ ፊት በመጮኸ የእርሱ ጸጋ ሽፋን እንደ ደበሎ ለብሰን ተራመድን።



# 3. ዮሴፍ በግዞት ቤት

"ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራ፡ ከግዞት ቤትም አስቸኰሉት፡ እርሱም ተላጨ፡ ልብሱንም ለወጠ፡ ወደ ፈርዖንም ገባ። ፈርዖንም ዮሴፍን አለው፡ ሕልምን አየሁ፡ የሚተረጕመውም አልተገኘም፡ ሕልምን እንደ ሰማህ፡ እንደ ተረጐምህም ስለ አንተ ሰማሁ።" (ዘፍጥ. 41፡14-15)

## 3.1. የዮሴፍ ታሪክ በአጭሩ

ዮሴፍ የያዕቆብ አሥራ አንደኛ ልጅ ሲሆን ከሚወድዳት ከራሔል የተገኘ ፍሬ ነበር ራሔልም ይህንን ብቻ አሳድጋለች። ብንያምን እንደወለደች በመሞትዋ የብንያምን ማንነት አታውቅም በመሆኑም ለያዕቆብና ለራሔል ብቸኛ የእግዚአብሔር የፍቅር ስጦታ ነበር። በሃያ ዓመት የላባ ቤት አገልግሎት ውስጥ የሚረካው በራሔል ሲሆን እርስዋ በመሞትዋ የተገኘው ቀዳሚ ፍሬ ዮሴፍ ነበር። ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ ዮሴፍን ይወድዳል፡ ከልጆቹም መካከል መልካም ልብስ ያለብሰውና ያስጠጋው የነበረው ዮሴፍን ነበር። በያዕቆብ በመወደዱ ወንድሞቹ ጠሉት፡ በተጨማሪም የዮሴፍን ዕድል በዮሴፍ ሕልም በመረዳታቸው ጠላትነት ተጠናወታቸው በዚህ ምክንያት ዮሴፍ በወንድሞቹ በጉድጓድ ተጣለ። ወንድሞቹ ለመግደል ሲወስኑ በይሁዳ አማካኝነት ይሸጡት ዘንድ አሳብ ቀረበ በዚህ ምክር ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች ተሸጠ። በሃያ ብር ተሸጦ ወደ ግብፅ ምድርም ገባ። (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚወድዳት ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን ፍሬ እንዴት ይወድ ይሆን?)

የዮሴፍ ታሪክ በግብፅ ውስጥ ሰፊ ነበር በዘፍጥረት መጽሐፍም ከምዕራፍ 39 እስከ 50 የዚህን ሰው ታሪክ እንመለከታለን። በእስማኤላውያን ከተሸጠ በኋላ በድጋሚ ለፈርዖን ጃንደረባ ለጲጢፋራ ተሸጠ። እስማኤላውያን ገዝተው ሸጡት። ዮሴፍ በግብፃዊው ጌታ ፊት ተቃናለት የእግዚአብሔር በረከት በውስጥም በውጭም ሆነ። ዮሴፍ ከፍ ማለት ጀመረ ይህ እንዲህ ሰምሮ እያለ ዮሴፍን የሚፈትን ታላቅ ፈተና ገጠመው ይኸውም በጌታው ሚስት የደረሰበት ፈተና ነበር። ይህ ፈተና የዮሴፍን ሕይወት ጨርሶ ሊያጠፋ የሚችል ሲሆን በዚህም ዮሴፍ በወህኒ ተጣለ።

ዮሴፍ በግዞት ቤት እያለ አሁንም ሕይወቱ የተቃናለት ሆነ። ምንም እንኳ በሐሰት ማስረጃ ዮሴፍ ቢወነጀልና በወህኒ ቢጣልም፥ የዮሴፍ የውስጥ ማንነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። የጌታው ሚስት እውነተኛ ማስረጃ በሚመስል ይህን ዕብራዊ ሰው ብትወነጅልም ዮሴፍ በእውነት የቆመ በመሆኑ የውስጡን ማንነቱን አላበላሸበትም። "እውነትም አርነት ያወጣችኋል" (ዮሐ. 8፡32) የዮሴፍን ሕይወት በግዞት አደባባይ መጽሐፍ ሲያስተዋውቅ እንዲህ በማለት ነው። "የግዞት ቤቱም አለቃ በግዞት ያሉትን እስረኞች ሁሉ በዮሴፍ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፥ በዚያም የሚደረገው ነገር ሁሉ እርሱ የሚያደርገው ነበረ።" (ዘፍጥ. 39፡22)

የዮሴፍ ተስፋ ማበብ የጀመረው ከግዞት አደባባይ በፈርዖን ትእዛዝ ሲጠራ ነበር። በዚህን ጊዜ ዮሴፍ ከፍ ከፍ ማለት ጀመረ። ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ዮሴፍ ፈተና ውስጥ ሲገባ አልታየም።



እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋና ራእይ ይከብር ዘንድ ጀመረ። የጥንቱን ጠጉር በግዞት ይጥል ዘንድ ተገደደ።

በብዙ ዘመን በግዞት የኖረ ሰው ሲፈታ እጅግ አጋጣሚ ጉዳይ ገጠመው። በግብፅና በዓለም የሚመጣው የአስራ አራት ዓመት ክስተት ዮሴፍን ከግዞት አስፈታው። በግዞት የተለማመደው ጸጋ በፈርዖን ዙሪን አካባቢ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረው ዘንድ ተመቻቸለት። የሰባት ዓመቱን የጥጋብና የሰባት ዓመቱን የረሃብ ዘመን ፍቺ አስታወቀ በዚህም የወርቅ ዝርግፍ፣ ቀለበት፣ የተልባ እግር ልብስ ተሸለመ። በፈርዖን ሁለተኛ ሰረገላ ላይ በመቀመጥ አገር ሁሉ ሰገደለት በግብፅም ምድር ሁሉ ላይ ተሾመ። ፈርዖን አለመ ዮሴፍ ፈታ በዚህም ከበረ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ክብር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ አስታወቀ ይህም ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ እንደሚሆን ተገለጠ።

የመከራን ጠጉር በመላጨት አዲስን ልብስ በመልበስ የተጀመረ ክብር ዘላቂነት አለው። በግዞት የበቀለን ጠጉር በግዞት አደባባይ በመተው ወደ ክብር ማቅናት ይገባል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለማክበር ሲነሳ አስቀድሞ የመከራን ጠጉር በግዞት አደባባይ እንዲጥሉ ያደርጋል፥ ከዚያም በአዲስ አናት ላይ የበቀለን ጠጉር በዙፋኑ አደባባይ መብቀል ይጀምራል። ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ጸጋ በንጉሥ አደባባይ እንዲበቅል ፈቅዷል። የመከራን መጎናጸፊያ ጥለን እንደምንነሳ የመከራንም ጠጉር አውልቀን እንድንኖር ይገባል። አሮጌና ውራጅ የሆነው ሊጠፋ ቀርቦአል አዲሱ ጠጉር ጥበብን በፊታንበትና በገለጽንባት አደባባይ መብቀል ይጀምራል። ዮሴፍም ከዚህን ቀን በኋላ ወደ መከራ ሲዘልቅ

አልተመለከትንም። ከዝቅተኛ ሥፍራ ወደ ንጉሠ ነገሥት ለመቅረብ ዮሴፍ ጠጉሩን ተላጨ። ሰው ወደ ወህኒ ሲገባ ይላጫል ዮሴፍ ግን ሲወጣ ተላጨ። እንግዲህ አንድ ሰው በሕልም፣ በራዕይ፣ በቃል ጠጉር መላጨት ብትመለከት ከመደንገጥ ይልቅ የትኛው ጠጉር ተገፍፎ እንደወለቀ ከጌታ ምሪትን መሻት ይገባል። "ፈርዖንም ልኮ ዮሴፍን አስጠራ፥ ከግዞት ቤትም አስቸኰሉት፤ እርሱም ተላጨ፥ ልብሱንም ለወጠ፤ ወደ ፈርዖንም ገባ። ፈርዖንም ዮሴፍን አለው፤ ሕልምን አየሁ፤ የሚተረጕመውም አልተገኘም፤ ሕልምን እንደ ሰማህ፤ እንደ ተረጐምህም ስለ አንተ ሰማሁ።" (ዘፍጥ. 41፡14 -15)

አማድፈውም ያለ ማስረጃ ወደ ወህኒ እንደጣሉት አማድፈው ወደ ፈርዖን ጊቢና ወደ ፈርዖን ልብ አስገቡት። ዮሴፍ ጠጉሩን ተላጭቶ ወደ ፈርዖን ገባ በዚያው አደባባይ ጠጉሩ አደገና በክብር ኖረ። ዮሴፍም ስለራሱ ክብር በግልጥ ሲናገር "... እግዚአብሔር ላከኝ እንጂ፤ ለፈርዖንም እንደ አባት አደረገኝ፤ በቤቱም ሁሉ ላይ ጌታ፤ በግብፅ ምድርም ሁሉ ላይ አለቃ አደረገኝ።" (ዘፍጥ. 45፡8) እንግዲህ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክነቱን የሚገልጠው በእስራኤል ምድር ብቻ ሳይሆን በግብፅ እንኳ ልጆቹን አባትና ጌታ በማድረግ ጭምር ነው።



# 4. የኢዮብ መከራ

"እነሆም፤ ዐውሎ ነፋስ ከምድረ በዳ መጥቶ የቤቱን አራቱን ማዕዘን መታው፤ በብላቴኖቹም ላይ ወደቀ፤ ሞቱም፤ እኔም እነግርህ ዘንድ ብቻዬን አመለጥሁ አለው። ኢዮብም ተነሣ መጐናጸፊያውንም ቀደደ፤ ራሱንም ተላጨ፤ በምድርም ላይም ተደፍቶ ሰገደ፤ እንዲህም አለ፤ ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፤ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔርም ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን። በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም፤ ለእግዚአብሔርም ስንፍናን አልሰጠም።" (ኢዮብ 1፡19-22)

በዖፅ ምድር ኢዮብ የሁሉ አባት ነበር። በዚህ ምድር ይኖሩ የነበሩ ድሆች ተስፋቸው ኢዮብ ሲሆን ሁሉ በእርሱ ቤት ያርፋሉ።

"ለዕውር ዓይን፤
ለአንካሳ እግር ነበርሁ።
ለድሀው አባት ነበርሁ፤
የማላውቀውንም ሰው ሙግት መረመርሁ።" (ኢዮብ 29፡15-16)

የኢዮብ መከራ በአገር ላይ የደረሰ እንጂ በኢዮብና በቤተሰቡ ብቻ አልነበረም። ኢዮብ ከምሥራቅ ሰዎች ሁሉ በላይ በመሆኑ ያለውንም ኃብት ለድሆችና ለአገሩ ሕዝብ የሚያካፍል በመሆኑ ኢዮብ የሁሉ አባት ነበር። ዕውር የሆነ ሰው ወደ ኢዮብ ቤት ከመጣ ይመገባል፣ ይኖራል። አንካሳውም ብዙ ሳይንቀሳቀስ ሁሉ ነገር በሥፍራው ይቀርብለታል በመሆኑም ዓይን የሌላቸውና አንካሶች በኢዮብ ዓይንና እግር ሁሉን ያደርጋሉ።

ኢዮብ በአንድ ጊዜ አራት የተለያዩ መከራዎች ገጠሙት፡፡ የሳባ ሰዎች አደጋ ጥለው ብላቴኖችን በሰይፍ ስለት ገደሉ ከብቶችንና አህዮቹን ወሰዱ፡፡ የሁለተኛው አደጋ የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወደቀች በጎችንም አቃጠለች፣ ጠባቂዎችንም በላች፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የከለዳውያን ሰዎች አደጋ ነበር በዚህም ብላቴኖችን በሰይፍ ስለት ገደሉ ግመሎቹንም ወሰዱአቸው፡፡ የመጨረሻው ጥፋት ግን የዐውሎ ነፋስ ሲሆን በዚህም የኢዮብን አስር ልጆች ከሌሎች ጋር አብሮ አጠፋ፡፡

አራተኛው መቅሠፍት ኢዮብን ባዶውን ሲያደርገው የቀረው ነገር በራሱ ላይ የነበረውን ጸጉ መግፈፍ ብቻ ነው፡፡ መጎናፀፊያውና ጠጉሩ በላዩ የነበሩ ክብር ሲሆኑ እነዚህን ከሰውነቱ ገፍፎ ጣላቸው፡፡ የመጨረሻው ፈተና ኢዮብ ራሱን እንዲመለከት አደረገው፡፡ ወደዚች ዓለም እንዴት እንደመጣ አስተዋለ ከእናቱ ማኅፀን ሲወለድ ራቁቱን እንደነበረ አሁንም አዲስ እንደተወለደ ሕፃን በራቁትነት ለመጀመር እንዲችል መጎናፀፊያውን ቀደደ፡ ጠጉሩንም ተላጨ በአዲስ ሕይወትም ይጀምርም ዘንድ ተመኘ፡፡ ከዚህ በፊት የኖረበት በመውደሙ በአዲስ ሕይወት መጀመርን ፈለገ፡፡ እንደ ገና ከእናቱ ማሕፀን እንደወጣ ሕፃን ራሱን ለመቁጠር ሁሉን አደረገ፡፡ በእግዚአብሔር ፊትም ሰገደ እግዚአብሔር ሰጠ እርሱም ነሳ፡፡ በመሆኑም ስለአሮጌው ሕይወት ማክተሚያ የሚሆነውን ጠጉር ተላጨ፡ መጎናፀፊያውንም ቀደደ፡፡ በዚህም የሰይጣንን አሳብ ኢዮብ በተግባር ሻረበት፡፡

አዲስ ክርስቲያንም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት አዲስ ጠጉርና መጎናፀፊያ ይኖረው ዘንድ አሮጌውን እንደ ኢዮብ መግፈፍ ይገባል፡፡



ከእናቱም ማኅፀን እንደተወለደ ሕፃን በአዲስ ሕይወት በስግደትና በአምልኮ መጀመር ይገባል፡፡ አዲስ ሕይወት የሚጀምረው ልክ ነፋስ እንደሚነፍስ ነው፡፡ በዚህ አዲስ ሕይወት የመጀመሪያው መጎናጸፊያችንና ጠጉራችን ከላያችን መውረድ ይገባዋል፡፡ ሰው በአዲስ ሕይወት የጌታን ጸጋ ሲጀምር ሁሉ አዲስ ይሆናል፡፡ "ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረን መዝገብ ትመስላለች፡ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፡ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠ ና ያን እርሻ ገዛ፡፡" (ማቴ. 13፡44) ኢዮብም ሁሉ ሲሸጥበት ሰገደ የውስጥ መዝገብ ምርመራን ተያያዘ፡ ወደ ውስጡ ገባ፡፡ አስቀድሞ በውጭ ያለ በረከትን በማየት ከእግዚአብሔር ጋር ይጓዝ ነበር አሁን ግን ፍፁም የእግዚአብሔር እውቀትን ያገኝ ዘንድ አዲስ መዝገብን ገዛ፡፡ ኢዮብ ጻድቅና ፍፁምም ቢሆንም አስቀድሞ እግዚአብሔርን የማወቁ ደረጃ ዝቅተኛ ነበር፡፡ "እነሆ፡ እኔ ወራዳ ሰው ነኝ፡ የምመልስልህ ምንድር ነው? እጄን በአፌ ላይ እጭናለሁ፡፡" (ኢዮብ 40፡4)

"መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፡
አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፡
ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፡
በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ፡፡"
(ኢዮብ 42፡5-6)

ኢዮብ እግዚአብሔርን በመስማት ደረጃ ያውቀው ነበር፡፡ መጎናፀፊያውን ቀድዶ ጠጉሩን ተላጭቶ በአዲስ ሕይወት ከጌታ ጋር መጓዝ ሲጀምር ግን አሁን ዓይኔ አየችህ በማለት የእይታውን

አድማስ አመለከተ። ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ይሰማል እግዚአብሔርን እንደ ኢዮብ የተመለከተ ግን ጥቂት ነው። ኢዮብ እግዚአብሔርን ይመለከት ዘንድ አዲስ እንደተወለደ ሕፃን ሆነለት በዚህም ራሱን ናቀ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጦ ተጸጸተ።

ስለ እግዚአብሔር በመስማታችን ብዙ እውቀት ያለን ሊመስለን ይችላል። በእርግጥም ኢዮብ እግዚአብሔርን ባልተመለከተበት ሰዓት እንኳ ብዙ ልጆችና በረከቶች ነበሩት ይህ ግን እግዚአብሔርን የምናውቅበት መንገድ አይደለም። የእግዚአብሔርን በጎነት ያልቀመሰ ትውልድ የለም ከፀሐይ፣ ከዝናብ፣ ከሰብል ከጤንነት ወዘተ እግዚአብሔርን በውስጥ ሰውነት ለማየት ደግሞ መወለድን ይጠይቃል የጸግም የመወለድ ምሥጢር ደግሞ ያለውን በሙሉ በመሸጥ ይሆናል። መጎናፀፊያችንን ቀድደን የድሮውን ጠጉር ላጭተን በአዲስ መጎናፀፊያና ጠጉር ጌታን በመከራ ለማየት መዘጋጀትና መስገድ ይገባል። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የመጀመሪያ በረከት የምንለው በእጥፍ ይመጣል። ኢዮብ ከመከራው በፊት የነበረው የእድሜ ቁጥር በመጽሐፍ አልተገለጠም የአሮጌው ሕይወት ዘመን በእግዚአብሔር ዘንድ ለቁም ነገር አይመዘገብም። "ከዚህም በኋላ ኢዮብ መቶ አርባ ዓመት ኖረ፤ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹንም እስከ አራት ትውልድ ድረስ አየ። ኢዮብም ሸምግሎ ዕድሜም ጠግቦ ሞተ።" (ኢዮብ 42፥16-17)



# 5. ከለምፅ መንጻት

## 5.1. ጥቁር ጠጉር

እስራኤላውያን ጥቁር ጠጉር ተብለው እንደሚታወቁ የዘሌዋውያን መልእክት ይጠቁማል። በአሁኑ ሰዓት በእስራኤል ምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአብዛኛው ድብልቅ በመሆናቸው የተለያዩ የጠጉር ቀለም ይዘው ይገኛሉ። ትክክለኛው እስራኤል ግን በጥቁር ጠጉር ይመደባል። አንዳንድ ምዕራባውያን አንድ ሰው የፈለገ አይነት የቆዳ ቀለም ይኑረው ጠጉሩ ከጠቆረ ይህ ሰው ጥቁር እኛ ብቻ ነጭ ነን ይላሉ። ጌታ ግን ግሩምና ድንቅ አድርጎ ጻዊትን (እስራኤልን) እንደሞዴል ፈጥሯል።

"... ጥቁርም ጠጉር ባይኖርበት፣ ካህኑ የቁረቁር ደዌ ያለበትን ሰው ሰባት ቀን ይዘጋበታል።" (ዘሌዋ. 13፥31)

"... ጥቁርም ጠጉር ቢበቅልበት፣ ቁረቁሩ ሽሮአል እርሱም ንጹሕ ነው፤ ካህኑም፣ ንጹሕ ነህ ይለዋል።" (ዘሌዋ. 13፥37)

በነዚህ ጥቅሶች መሠረት የአንድ ሰው ጠጉር ወደ ጥቁርነት ከተቀየረ የንጽህናና የመደበኛ መልክ ምሳሌ ነው። በመጀመሪያ ጥቁር ቀጥሎም ነጭ ይሆናል። አስቀድሞ ጨለማ ቀጥሎ ብርሃን እንደ ሆነ ሁሉ የሁሉ እድገት ይህ ነው። ነጭ ጠጉር የክብር ምልክት ነው። "የሽማግሌዎችም ጌጥ ሽበት ነው።" (ምሳ. 20፥29)

የለምጥ ደዌ አስቀድሞ የጠጉር ቀለምን መቀየሩ የሚደንቅ ነው። ጠጉር በተፈጥሮው የያዘውን ጥቁር መልኩን ለማጥፋት የለምጥ ደዌ ከተንቀሳቀሰ ጥቁር መሆኑ ብቻ የተፈጥሮ ጸጋ ነው። በመካከለኛና በሩቅ ምሥራቅ በሕንድ ጭምር የሚኖሩ ሕዝቦች ጥቁር ጠጉር አድጎ

ሲታይ ምንኛ የጌታን ሥራ እናደንቃለን? በተለይ የአንዳንድ ሰዎችን ጥቁር ጠጉር አድጎ ስንመለከት የጠጉሩ ውፍረት እንደ ፈረስ ጋማ ይመስልና ቢቆነጥጡት ጥቁር ደም የሚፈስስው ይመስላል።

ጥቁሮች፣ ነጮች እየተባለ የሚነገረው የቀለም ለውጥ በዚህም የሰው ልጆች መመካት የሚደንቅ ነው። የትኛው ቀለም ነው የሚያምረው ቢባል ያለጥርጥር እንደ ሰው ምርጫ ነው። አንዳንድ ሰው ጥቁር ልብስ፣ ጥቁር መኪና፣ ጥቁር ጫማ፣ ጥቁር መንገድ (Aspalt) በጥቁር ፍሬም ያጌጡ ቁሳቁሶች፣ ጥቁር ፈረስ፣ ጥቁር እንስሳን፣ ጥቁር ሰውን ይወድዳሉ። አንዳንድ ደግሞ በነጭ ቀለም የተዋቡ ቤቶች፣ እንስሶች፣ ቁሳቁስ ወዘተ ይወድዳሉ።

አንድ በቀለም ትምህርት መስክ የተማረ ሰው ሲያጫውተኝ ጥቁር ቀለም የክብር ቀለም ነው አለኝ ማለትም አንድ የምትወድደውና የምታከብረው ሰው ጥሪ ሲያቀርብልህ በዚህ ሰው ፊት ሙሉ ጥቁር ልብስ ለብሰህ ከታየህ ለጠራህ ሰው አክብሮትህን ትገልጥለታለህ። በተቃራኒውም የምትወድደው ሰው ሲሞትብህ ለክብሩ ማዘንህን ስትገልጥለት ጥቁር ክረባት፣ ጥቁር ልብስ ለረጅም ቀናት ታጠልቃለህ።

የሰማይም ፊት ዝናብ ሲያዝል ደመና ካዘለው ውኃ የተነሳ ይጠቁራል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍጥረት እፎይ ይላል። እንግዲህ የጥቁር ጠጉር ውበትን የሚበላ የለምፅ ደዌ ከሆነ እኛ በጌታ ፊት ያማረውን መለኮታዊ ጥቁር ጠጉር ደፍተን ብንገኝ የፈጣሪያችንን ክብር በየስፍራው እንገልጣለን። በሕልም፣ በራእይ፣ በመገለጥ የአንድ ሰው ጠጉሩ ሳስቶ፣ ሌላ መልክ መያዝ ከጀመረ በተለይም መመለጥ



ከጀመረ ዛሬ ነገ ሳንል ለዚህ ሰው መልእክቱን በማድረስ መለኮታዊ ጠጉሩ (ጸጋው) እየተጎዳ እንደሆነ በወንድማዊ ፍቅር ልንነግረው በዚህም ልናስተካክለው ይገባል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን ሁሉ ዙረት ከምንዞር ጸጋው ተበላሽቷል ወይንም በጥሩ ጸጋ ሰውየው ይገኛል ብለን ለምን አይገለጥለትም የሚሉ ይኖራሉ። መለኮታዊውን ጸጋ በሚታየው ዓለም ተምሳሌት ማድረግ (Alagorizm) አይሆንም ወይ? መንፈሳዊውን ዓለም ለምን እናወሳስበዋለን የሚሉ ይኖራሉ።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም መወለድ ለኒቆዲሞስ ሲነግረው ኒቆዲሞስ ደግሞ ነገሩን ሊያወሳስብ ሞከረ። አሕዛብ የነበሩ ሁሉ ወደ ይሁዲነት ሲቀየሩ ማንም የእስራኤል ረቢ ይህ ሰው ዳግም ተወለደ፣ ወደ ተስፋው ልጅ መጣ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆነ በማለት ይናገሩ ነበር። ጌታም ይህን ቃል ሲናገር ኒቆዲሞስ ሰምቶ የማያውቅ ይመስል ተደነቀ። "ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?" (ዮሐ. 3፥12) የጌታን አሠራር በምድራዊ ቋንቋ ካልተተረጎመ በቀር ሰማያዊው ቋንቋ በምን ሊገባን ይችላል? ጌታ አጠቃላይ የመንግሥቱን ምሥጢር የገለጠው በምድራዊ ቋንቋ ነበር ለምሳሌ መንግሥተ ሰማይት በባህር የተጣለች መረብ ትመስላለች ወይንም ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች ወይንም መልካም ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች ወይንም ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥ ትመስላለች ወዘተ። የጌታን አሠራር በመለኮታዊ ጠጉር አሠራር ብንመለከተውና በቅንነት ብናስብ የተሻለ መረዳት ይኖረናል።

እግረ መንገዴን ስለ ትንቢትና ስለ ራእይ ወይንም ሕልም ጸጋ ጠቆም ላድርግ:: እነዚህ ጸጋዎች የሚገለጡት ለማነጽ፣ ለፍቅር፣ ለማቅናት እንደሆነ እናስብ:: አንድ ሰው በአደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነና የጌታ ጸጋ ከተገለጠልን ይህ ሰው ወንድማችን ወይም እህታችን ወይንም በሥጋ የወለድነው ክርስቲያን ላይ እንደ ተገለጠ አስቀድመን እናስብ:: በራእይው አደጋ ላይ ወንድማችን የተገኘ እንደሆነ ከተገለጠ በጉዳዩ እንዘን፣ እንተክዝ፣ እንጸልይ፣ ጠላት ያመጣበትም ከሆነ እንታገልለት ከዛም በትህትናና፣ በፍቅር በጥሞና ጉዳዩን እንዲያስብበት እንግለጥለት:: በዚህም የመታደግን ሥራ እንጨምር:: ወንድማችን በክብር፣ በተለየ ጸጋ፣ በሽልማትና በአክሊል ተጎናጽፎ በረጅም ጠጉር ከተመለከትን ጌታን አስቀድመን እናመስግን፣ ጌታ ሆይ ደስ ብሎኛል፣ ለምድራችንና፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ እንዲህ ዓይነት ሰው ስለሰጠኸን እናከብርሃለን በማለት ጌታን ካከበርን በኋላ ለወንድማችን ደስታ በተሞላ አንደበት እንግለጥለት አብረንም እናመስግን፣ ከክፉም እንዲታደገው እንምከረው፣ እንሸከመው:: ይህ ከሆነ ጸጋችን፣ ራእያችን፣ ትንቢታችን ሁሉ የሰመረ፣ የበለጸገ ይሆናል:: ሙሴ ከሰው ሁሉ ይልቅ ትሁት በመሆኑ እስራኤልን በሙሉ እንደ ሞግዚት አቅፎ አርባ ዓመት ተሸከመ፣ ከጌታ ጋር አፍ ለአፍ ያወራ እንደ እርሱ ያለ ነቢይ ከዚያን በኋላ እንዳልተነሣ የዘዳግም መጽሐፍ በመጨረሻ ምዕራፍ ይነግረናል::



## 5.2. የጠጉር ቀለም መለወጥ

"ካህኑም ያያል፤ እነሆም፡ ወደ ቁርበቱ ውስጥ ጠልቆ቎ ቢታይ፡ ጠጉሩም ተለውጦ ቢነጣ፡ ካህኑ፡ ርኩስ ነው ይለዋል፤ የለምጽ ደዌ ነው፤ ከቍስሉ ውስጥ ወጥቶአል::" (ዘሌዋ. 13፥20)

እግዚአብሔር በመለኮታዊው ዓለም ሕዝቡ ተስማሚ ጠጉር ይኖረው ዘንድ ይፈቅዳል:: የመለኮታዊው ጠጉር ወደ ቢጫ የሚመስል የለምፅ ምልክትን ካሳየ ይዘጋብንና ሁኔታውን እስከሚታወቅ በእሥር ያቆየናል:: በእርግጥም ደዌው የለምፅ ካልሆነ ካህኑ ንፁሕ ነህ በማለት ይጨርሳል:: እንዲህ ከሆነ አንድ የእስራኤላዊ ወጣት ጠጉሩ ነጭ ከሆነ በክህናት ራዳር ስር በመግባት ይህ ሰው ርኩስ ሳይሆን አይቀርም በሚል ስሜት ለምርመራ ይቀርባል::

የአንድ ሰው ጠጉር የለምጽ ደዌ ካገኘው መልኩን ይቀይራል በጥቁርነቱ የጀመረው ጠጉር ሌላ መልክ ይይዛል:: መለኮታዊው ጸጋ ከራስ ላይ አድጎ፣ ብዛቱም በቂ ሆኖ የመንፈሳዊ ለምጽ ሲያገኘው መልክን ይቀይራል ይህ ደግሞ ክፉ ደዌ ነው:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ካህኑ መቅረብና ለተወሰነ ጊዜ በመሸሸግ ለጠጉሩ ውበት መጨነቅ ይገባዋል:: የጠጉርን መልክ ከሚቀይር ክፉ ደዌ ራስን መጠበቅ ይገባል:: መለኮታዊ ጠጉር በቅሎ ሳለ መልኩን በመለወጡ የብዙ ሰዎች ጸጋ ተጎዳ:: መለኮታዊውን ጠጉር በመነካካት ሳይሆን መልኩን በመንፈሳዊ አይን በማየት የሰውን ጤንነት መመልከት ይበጃል በእግዚአብሔርም ቃል ማስታወቅ መጎብኘት ተገቢ ነው::

## 5.3. የተገለጠ ራስ

"የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀደደ ይሁን፥ ራሱም የተገለጠ ይሁን፤ ከንፈሩንም ይሸፍን፤ ርኩስ ነኝ ይበል። ደዌው ባለበት ዘመን ሁሉ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ ርኩስ ነው፤ ብቻውን ይቀመጣል፤ መኖሪያውም ከሰፈር ውጭ ይሆናል።" (ዘሌዋ. 13፥45-46)

የለምጽ ደዌ በብሉይ ኪዳን እጅግ አስከፊ ከመሆኑ የተነሣ የሁሉ ኃጢአት ማሳረጊያው ይህ ሲሆን በተለይ ካህኑ ርኩስ ያለውና የለየው ሰው ከሁሉ አስከፊ ነበር። አዲስ ልብስም ቢገዛ የተገዛው ልብስ መቀደድ ይገባዋል ጽድቁ የተቀደደ መሆኑን ለማሳየት የለምጻሙ እድል ፈንታ ልብሱን መቅደድ ይሆናል። ልብስ ሲቀደድ ሰውነት ይገለጣል፤ የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ማንነቱ ለማንም እንዲገለጥ በቀዳዳው ልብስ ስር ያለው ገላ የተገለጠ በመሆኑ ተመልካቹ ለራሱ ጥንቃቄ በማድረግ ከዚህ ሰው ይርቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ብልቶች አለባበስ ሲናገር ብዙ "... በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል፥ ክብር ያላቸው ብልቶቻችን ግን ይህ አያስፈልጋቸውም።" (1ኛ ቆሮ. 12፥23-24)

የለምጽ ደዌ በሰውነቱ የተገለጠ ሰው ራሱ የተገለጠ ሆኖ ምንም ዓይነት መለኮታዊ ጥበቃ የሌለው ከመሆኑም በላይ በአንደበቱ እንኳ እንዳይናገር ከንፈሩ የተሸፈነ ነው ከአንደበቱ የሚወጡ ቃላት በሙሉ ስለማይጠቅሙ ከንፈሩ ይቆለፋል። በራሱ ፈቃድ ከንፈሩን በመሸፈን ቃሉ በሙሉ የተከለከለ ነው። ትንፋሹም አካባቢውንና ዓየሩን ስለሚበክል ለዚህ ሰው መፍትሄ ከንፈሩን መሸፈን ብቻ ይሆናል።



ይህ ሰው ቢናገር እንኳ "ርኩስ ነኝ፤ ርኩስ ነኝ የሚል ብቻ ይሆናል። ስለራሱ ያለው ቋንቋ አንድ ሲሆን መርከሱን ብቻ ስለሚያውቅ ይህን በአደባባይ ይገልጣል።

የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው በሌላ መልኩ ሌላ መስፈርት አለው ይኸውም ብቸኛ ይሆናል። ከሰው ተለይቶ ይኖራል ፍቅር ለዚህ ሰው ይነፈጋል። ከማንም እንዳይቀላቀል ብቻውን ይኖራል፤ የብቸኝነት መንፈስ ይጠናወተዋል። ብቻውን ከመሆኑም በላይ ሰፈር ይቀይራል፤ ሰፈሩም በውጭ ይሆናል። በመለኮታዊው ዓለም ይህ ዓይነቱ የለምጽ ደዌ በስፋት ይታያል። መለኮታዊው ጠጉሩ ወደ ነጭነትና ብጫነት ተለውጦ ቈረቈር የወረሰው የሰው ልጅ ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቃል ይሠራበታል። በለምጽ የተመታ ሰው አንደኛው ምልክቱ መንፈሳዊ ልብሱ የተቀደደ ነው። ጽድቁ የተቀደደ በመሆኑ እንደ እብድ የተበጫጨቀ ልብስን ይለብሳል። ራሱም የተገለጠ ነው። "የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው" (1ኛ ቆሮ. 11፥3) የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ግን ራሱ የተገለጠ ይሆናል። ያለ ራስ የሚኖር ለክፉው የተገለጠ ነው። በዚህ ዘመን የተቀደደ አሪጅናል ልብስ በየመንደሩ እየተሸጠ ነው። የልብስ ኢንዱስትሪዎች ይህ ቋንቋ ስለገባቸው ለሚፈልግ ሁሉ አዘጋጅተው ብዙ ሰው እየተገለገለበት ይገኛል። ይህን ልብስ የሚጠቀም እንግዲህ ራሱን ለምጥ አለብኝ በማለት ይመሰክራል (በተለይ የጥንት የእስራኤል ካህናት ይህን ሰው ቢመለከቱት ማለቱ ነው)

መንፈሳዊ ለምጽ የተሸከመ ሰው ከንፈሩ የተሸፈነ ነው። ጽድቅን ከመናገርና ከማወጅ የታቀበ በመሆኑ ከዚህ ሰው ከንፈር የሚፈስ

ቁም ነገር የለም። አካባቢውና ዓየሩ በሙሉ ከሚበከል የዚህ ሰው እንደበት በራሱ እጅ ይሸፈን ዘንድ ይገባል። ቢናገር እንኳ ርኩስ ነኝ፣ ርኩስ ነኝ የሚለውን ሲሆን ውድቀትን፣ሽንፈትን፣ መግዛትን፣ ባርነትን እንጂ ተስፋ የሚሰጡ ቃላት አይገኝበትም። በተጨማሪም የብቸኝነት ሕይወት ይጠናወተዋል፤ ከወንድሞቹ ጋር ያለው ሕብረት እጅግ የቀዘቀዘ በመሆኑ በመለኮታዊው አደባባይ አይገኝም፡ መሸሸግ፣ መደበቅ፣ ጨለማና ብቸኝነት የዘወትር ልምምዱ ይሆናሉ። አንድ ሰው ሁልጊዜ ስለርክሰናው የሚያወራ የጽድቅ ቃል የራቀት ከሆነ የዚህን ሰው ሕይወት በዚህ ቃል መሠረት ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ የኛን ደዌ ተሸክሞ የኃጢ አት ለምጻችንን ያስወግድልን ዘንድ በኛ ስፍራ ቆመ። «በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሰፈ እንደ ተቸገረም ቈጠ ርነው።» (ኢሳ. 53፥4) ጌታ ኢየሱስ የኛን ደዌ በመሸከሙ እኛ መልበስ የሚገባንን ልብስ ለበሰ፡ በእኛ አካል መገኘት የሚገባውን ለበሰ። የለምጽ ደዌ የተሸከመ ሰው የተቀደደ ልብስ እንደሚለብስ ጌታም በመስቀል ይኸው ገጠመው። "ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት ...።" (ዮሐ. 19፥23)

ጌታ የኛን ሕመም በመሸከሙ በአንደበቱ ዝም አለ፣ እኛ ዝም ማለት የሚገባንን ለማሳየት እርሱ ዝም አለ። "... በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።" (ኢሳ. 53፥7)



ለበጎ ነገር እንኳ ዝም አለ። ከዚሁ ሁሉ በላይ ብቸኛ ሆነ፡ ሁሉ ተውት። እኛን ወክሎ በመምጣቱና ደዌያችንን በመሸከሙ ብቻውን ቀረ። "ሁሉም ትተውት ሸሹ።" (ማር. 14፡50)

ጌታ ኢየሱስ የኛን ድካም ለመሸከም ከሰፈር ውጭ መከራን ተቀበለ። በእኛ ኃጢአት ለምጽ ደዌ ምክንያት ብቻውን ከሰፈር ውጭ መከራን ተቀበለ። የተበተኑትን ይሰበስብ ዘንድ ብቸኛ ሆነ። ከሰፈር ውጭ ያለነውን ከሰፈር ውስጥ አስገባን። "ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።" (ዕብ. 13፥12)

"ያዕቆብ ሆይ፡ እስራኤልም ሆይ፡ መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች ፍርዴም ከአምላኬ አልፋለች ለምን ትላለህ? ለምንስ እንዲህ ትናገራለህ? አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፡ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፡ አይታክትም፡ ማስተዋሉም አይመረመርም።" (ኢሳ. 40፥27-28)

## 5.4. ጠጕርን መላጨት ከለምጽ መንጻት

"የነጻውም ሰው ልብሱን ያጥባል፡ ጠጕሩንም ሁሉ ይላጫል፡ በውኃም ይታጠባል፡ ንጹሕም ይሆናል። ከዚያም በኋላ ወደ ሰፈር ይገባል፡ ነገር ግን ከድንኳኑ በውጭ ሆኖ ሰባት ቀን ይቀመጣል። በሰባተኛውም ቀን ጠጕሩን ሁሉ ይላጫል፡ ራሱንም፥ ጢሙንም፥ ቅንድቡንም፡ የገላውንም ጠጕር ሁሉ ይላጫል፡ ...ንጹሕም ይሆናል።" (ዘሌዋ. 14፥8-9)

የለምፅ ደዌ መንጻት ካህኑ ለማብሰር ዋናው የጠጉር መላጨት ሥርዓት ነው። አስቀድሞ የራሱን ጠጉር ይላጭ ዘንድ ይታዘዛል ከሰባት ቀን በኋላ ግን በራሱ፣ በቅንድቡ፣ ጢሙን በገላው ያሉ ጠጉር በሙሉ ከሰውነቱ ይወገዳሉ። ይህን ጠጉር በሚያስወግድበት ጊዜ ለሚነጻው ሰው ታላቅ እፎይታ ይሆናል። የቀደመውን የክፉ ማንነቱን የሚሸረው በያዘው ምላጭ ነው። በሰውነቱ የሚገኘውን ጠጉር በሙሉ ያስወግድና ለአዲስ ጸጋ ሰውነቱን በሙሉ ማስገዛት ይጀምራል፤ የቀደመው ማንነቱን ለመሻር ሰውነቱ ላይ በሙሉ ምላጭ ያልፋል ወደ ነጭነትና ሌላ መልክ ለመያዝ የሞከረ ጠጉር በሙሉ ይጠፋል።

አንድ ሰው ወደ ጌታ ሲቀርብ አስቀድሞ የነበረው ጠጉር በሙሉ በመለኮታዊው ምላጭ ይወገዳል ለአዲስ ሕይወት አዲስ ጠጉር ይጠብቃል። በክርስቲያንም ሕይወት ከዓለም የመጣውን መንፈሳዊ ለምጽ በዚሁ መልክ ይቀየራል። የለምፃችንን ደዌ በውኃ ካጠብን ልብሳችንን ከቀየርንና በአዲስ ጸጋ በካህኑ ምሪት እንንዛለን። እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋሁ መጽሐፍ  እንደሚለን ለአዲስ ጸጋ አዲስ ጠጉር ይዘን እንገለጥ። በጌታ ቤት እየኖረን በለምጽ ደዌ ከተመታን ግን አስቀድሞ የነበረ ጸጋችን በሙሉ በምላጭ ስር ያልፋል። እስራኤላዊ ሆኖ ለምጽ የተገኘባቸው በሙሉ እንደገና ተላጭተው እንደሚነጹ መንፈሳዊ እስራኤላዊያንም ዘንድ የዚሁ ደዌ ይገኛል ይህ ሲሆን በሊቀካህናችን ኢየሱስ ፊት በመቅረብ የተበላሸውን ጠጉር ላጭተን በአዲስ ሕይወት ጸጋችንን እናሳድግ። ጌታን እንደተቀበልን በቀጥታ ለጥምቀት ወደ ውኃ የምንመጣው ለዚህ ይሆን?



# 6. የተማረከች ሴት

"ጠላቶችህን ልትወጋ በወጣህ ጊዜ፡ አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣቸው በማረክሃቸውም ጊዜ፡ በተማረኩት መካከል የተዋበች ሴት ብታይ፡ ብትመኛትም ሚስትም ልታደርጋት ብትወድድ፡ ወደ ቤትህ ታመጣታለህ፡ እርስዋም ራስዋን ትላጫለች፡ ጥፍርዋንም፡ ትቈርጣለች፥ የተማረከችበትንም ልብስ ታወልቃለች፡ ... ባልም ትሆናታለህ፡ ...።" (ዘዳግ. 21፡10-13)

የኦሪት ሕግ ውስጥ ብዙ አስደናቂ ታሪክ እናገኛለን ከዚህም መካከል በምርኮ ስለተገኘች ውብ ሴት ታሪክ ነው። እስራኤልን ለመውጋት ከተሰለፉ ጠላቶች መካከል ውብ ሴቶች ይገኛሉ። ከእስራኤል ወንዶች መካከል አንዱ ከተማረኩት ውብ ሴቶች መካከል ለራሱ ሚስት ይመኝ ይሆናል በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር ሕግ ለዚህ ጉዳይ ክፍተትን ሰጥቶአል። ከጠላት መካከል ሚስት ለማግባት ለእስራኤላዊ ወንድ ፈቃድ አለው። እንግዲህ ውበት ጠላትነትን የመሻር ችሎታውን እዚህ ላይ እንመለከታለን። የእስራኤል ወንዶችን ለመግደል ከተሰለፉት መካከል የተገኘች ሴት የእስራኤል ወንድ ሊያገባት የሚችል ሕግ በመኖሩ በእርግጥም ፍቅር ከሞት የጨከነ ነው። (የእስራኤል ደናግል በሚለው አስቀድሜ በጻፍኩት መጽሐፍ የበለጠ ማብራሪያ እዚያ ላይ ይመለከቷል።)

በምርኮ የተገኘችን ሴት በቀጥታ ሚስት ትሆን ዘንድ የሚደረግላት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ እንደመጣች ወዲያውኑ ሚስት መሆን አትችልም። እንግዳ ሴት ከመሆንዋም በላይ ምርኮኛ ነች። በመጀመሪያው በዚህች ሴት የሚከናወነው ተግባር ጠጉርዋን

መላጨት ይሆናል የባእድ ጠጉር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር መገናኘት ስለማይኖርባት የቀድሞው የምርኮኝነት ጠጉር ከላይዋ በምላጭ ይነሣል:: በመላጣነት አዲሱን የእስራኤል ሙሽርነት ትጀምራለች:: ራሰ በራ ሙሽሪት በመሆን የመጀመሪያውን ኑሮዋን በልቅሶ ዘግታ አዲሱን ሕይወት በበቀለው አዲስ ጠጉር ትጀምራለች:: ሐምራዊ ሐር የመሰለ ጠጉር ወይንም የተንዠረገገ የሚመስልም ጠጉር ቢኖራት ይህ ከእስራኤል ውጭ የበቀለ ጸጋ በመሆኑ ለአዲሱ መንግሥት የሚበጅ ባለመሆኑ በመላጣነት ሕይወት አዲስን ትዳር ትጀምራለች:: ከሰው አካል ውስጥ ያለማቋረጥ የሚበቅል ጠጉርና ጥፍር ሲሆን እነዚህ ሁለቱም ወደ እስራኤል ማኅበረሰብ በእስራኤል አገር ጸጋ፣ መብልና መጠጥ ሊበቅሉ ይገባቸዋል::

ለሴት ልጅ ውበቷ ጠጉርዋ ነው:: የአሕዛብን ውበት ይዛ ግን በእስራኤል መንግሥት ሕግ መተዳደር አይሆንም:: በአዲስ መልክ ሊገለጥ ያለ ጸጋ እንዲኖር ጠጉርና ጥፍር ይቆረጣሉ በዚህ እንደ እስራኤል ደናግል ትቆጠራለች:: ከአሕዛብ ወደ እስራኤል የተመለሱ ሕዝቦች በአዲስ ሕይወት መኖር ከፈለጉ እንደ ተወለደ ሕፃናት በአዲስ መልክ ጸጋቸው ሊያድግ ይገባል:: ከዓለምና ከምርኮ ይዘውት የመጡትን ላጭተው በእስራኤል ከተማ፣ በእስራኤል መብልና መጠጥ፣ ጸጋቸው ሊጀምር ይገባል ነገር ግን በመላጣነት ሕይወት ሲጀምሩ በእፍረት ቢሆንም ከጥቂት ጊዜ በኋላ የእነርሱም ጸጋ ሊበቅል ይገባዋል::

የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርአት በነበረ ላይ የሚበቅል ሥርአት አይደለም:: "... ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ



ሸጠና ያን እርሻ ገዛ::" (ማቴ. 13፡44) ከደስታ የተነሣ ያለንን ሸጠን በመንግሥቱ የሚገኘውን ውበት በመግዛት የምንጀምረው እንጂ ባለው ላይ የሚታከልበት አይደለም:: ከባዶነት፣ ከመላጣነት ጀምረን በዚያው መንግሥት ሥርአት የምናድግበት ከመሆኑም በላይ ሊመሰገን የሚገባው የክብሩ መንግሥት እንጂ ከምርኮ በፊት ለነበረ መንግሥት አይደለም::

በምርኮ የተገኘችው ሴት የእስራኤልን መንግሥት ስታጠፋ የነበረች ከእስራኤል ወንድ ምሕረትን አግኝታ የእስራኤል መንግሥት ተካፋይ እንደሆነች፡ እኛም የመንፈሳዊውን የእስራኤልን መንግሥት የምንገፋና የምንዋጋ በነበርንበት ወቅት በጌታ ተማርከን የተገኘን ለአንድ ወንድ የታጨን ነን:: በዚህን ጊዜ ግን ልናደርግ የሚገባን ዋናው ጉዳይ የቀድሞውን ጸጋ የሚመስለውን ጠጉር ላጭተን በአዲስ ጠጉር በክብር ተጎናጽፈን ልንኖር ተጠርተናል:: በመሆኑም የበቀለው ጸጋ በሙሉ የአዲሱ መንግሥት ክብር ነው:: በምርኮ ተይዘን መገደል ሲገባን ለአንድ ወንድ ታጭተን የተማረክንበትን የመጀመሪያውን ልብስ ገፍፈን በእስራኤል መንግሥት የተፈተለ በፍታና ሐምራዊ ቀይ ግምጃ ለብሰን ከዓለም ቅዝቃዜና ብርድ መራቅ እንችላለን:: በአዲስ ሕይወት ሊያስተምሩን ከሚችሉት ዋናዎቹ አዲስ ጠጉር፣ አዲስ ጥፍርና አዲስ መጎናፀፊያ ናቸው:: እነዚህ ብቻ ሊቀየሩ የሚችሉ ውበቶች ናቸው በዚህ ከእስራኤል አእላፋት እንደ አንዱ እንቆጠራለን::

ስለጠርነት፣ ምርኮኝነትና ሞት እንዴት እንደሚከሰቱ በጥንቃቄ መረዳት እንድንችል መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ አድርጎ በተለያዩ

ሥፍራዎች ያሰቀምጣል፡፡ ለእስራኤላውያን ጦርነት ማለት የዘወትር ሥራቸው ሲሆን ይህ የሆነበት በእኔ እይታ ሁለት ምክንያቶች አገኘሁ፡፡ በመጀመሪያ የእስራኤል መንግሥት ሲጀመር ከሌላ ሥፍራ መጥተው በመውረስ ሰፈ ቦታ ይይዙ ዘንድ ጌታ አዘዘ፡፡ "በዚህችም የእግር ጫማ ስንኳ የሚያህል ርስት (ለአብርሃም) አልሰጠውም፤ ነገር ግን ልጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው፡፡" (የሐዋ. 7፡5) ርስት ያልነበረውን አብርሃምንና ዘሩን ከወንዝ እስከ ወንዝ ድረስ ታላቅ ምድር ሰጠው፡፡ ይህም የሚሆነው በሬ ገላባን እንደሚበላ (ሞዓብ ለምድያም ሽማግሌዎች እንዳብራራው) አህዛብን በሙሉ እያጨዱ ሥፍራ እያስለቀቁ መውረስ ዓይነተኛ ሥራቸው ነበር፡፡

እግዚአብሔር በግልጥነት ለእስራኤል ማኅበረሰብ የሰጠው ርስት እንዴት እንደሚወርሱ እንዲህ ይላል "ለመዋጋት ወደ አንዲት ከተማ በደረስህ ጊዜ አስቀድመህ በዕርቅ ቃል ጥራቸው፡፡ የዕርቅ ቃልም ቢመልሱልህ ደጅም ቢከፍቱልህ፣ በከተማው ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉ ይገብሩልህ ያገልግሉህም፡፡ የዕርቅ ቃልም ባይመልሱልህ ከአንተ ጋር መዋጋት ቢወዱ፣ አንተ ከተማይቱን ትከብባለህ ታስጨንቃትማለህ፡ አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣት ጊዜ፣ በእርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላዋለህ፡ ነገር ግን ሴቶቹንና ሕፃናትን እንስሶቹንም በከተማይቱም ያለውን ምርኮ ሁሉ በዝብዘህ ለአንተ ትወስዳለ፤ ፡ (ዘዳግ. 20፡10-14) እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሌሎች ሥጋ [illegible] አይገደውምን? እስራኤል ብቻ የምታሸንፍበትን መንገድ እንዴት



መረጠ? እንግዲህ ማንም ወደደም ጠላም ይህ ቃል የጌታ ነው፡፡ ዕርቅ ከሰሙ ይገብሩ ያገልግሉህ አልያ ወንዱን ሁሉ በሰይፍ አጥፉ ይህም በሌሎች ከተሞች ሁሉ ይቀጥል፡፡ ዛሬ ክርስቶስን አምናለሁ የሚል የጌታ ባርያ ሲፈራና ሲርበተበት መመልከቱ ለሰማይ ሠራዊት አስደናቂ ይሆናል፡፡ በቃሉ መሠረት ጉንጭህን ለሚመታ ሌላውን ስጠው አክብረው ነገር ግን ማንንም እየፈራን እንድንኖር ቃሉ አይፈቅድም፡፡

ሁለተኛው የጦርነት ምክንያት ድል አድርገው ከተቀመጡ በኋላ ሌላ ንጉሥ መጥቶ እንደገና ባልተዘጋጁበት ወቅት እንዳያጠፋቸው ሁሉ እስራኤላዊ ጦርነትን እንዲለምድ ያስገድድ ነበር፡፡

"ከከነዓናውያንም ጋር መዋጋት ያላወቁትን እስራኤልን በእነርሱ ይፈትናቸው ዘንድ፣ በፊትም ሰልፍን ያልለመዱ የእስራኤል ልጆች ትውልድ መዋጋትን ያውቁና ይማሩ ዘንድ እግዚአብሔር ያስቀራቸው አሕዛብ እነዚህ ናቸው፤ ...፡፡" (መሳ. 3፡1-2) ዛሬም መንፈሳዊ ውጊያ ያልለመደ ክርስቲያን ውጊያን ይለምድ ዘንድ የሰይጣን ጭፍሮችን ለመለማመጃ ያስቀምጣል፡፡ አንዳንድ መጋቢያን ወይንም እረኞች በምዕመኑ ምትክ ይህን ሊዋጉላቸውና ምዕመኑ ዘወትር ቁጭ ብሎ አለ ጭንቅ እንዲኖር ሲታገሉ ይታያሉ፡፡ መፍትሄው ግን መጋቢው ተዋግቶ እዚህ እንደደረሰ ምዕመኑም ከከነዓናዊው ጋር ተዋግቶ እጁን እንዲያፍታታ፣ መለኮታዊ የጦር ዕቃውን እንዲፈትሽ ጌታ ያስቀመጠው በመሆኑ ምዕመኑን በርታና ተዋጋ ሊሊት እንቅልፍህን ትተህ ስትፀልይ እደር፡፡ እነዚህ ከጌታ ለአንተ የተመደቡ ናቸው ብሎ በቃሉ መሠረት ማስተማር ይበጃል፡፡

ስለ ኢትዮጵያና እስራኤልም በመጽሐፍ ተገልጿል:: አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በስህተት ይመስለኛል ራሳቸውን ከጽዮን፡ ከይሁዳ ነገድ፡ ከእስራኤል ዝርያ ጋር አዛምደው ለእስራኤል ምድር የሚሆነውን በረከት የኛም ነው ሲሉ ይደመጣሉ:: ከጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ኢትዮጵያ የእስራኤል በረከት ተካፋይ መሆንዋ የሚገልጥ የጂኦግራፊ ምህዳር (Geographical location) የታሪክ ፍሰት፡ ወይንም የባህል አንድነት የለንም:: እንዲያውም እስራኤል ሌላውን አሕዛብ እያጠፋች ስትኖር እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ የደመሰሰችው አሃዝ ያለ አይመስለኝም:: በ2ኛ ዜና መዋዕል 14 ላይ ሙሉ ታሪኩን ይመልከቱ:: እግዚአብሔርም በይሁዳ ንጉሥ አሳ ፊት አንድ ሚሊዮን የኢትዮጵያን ሠራዊት ሰባበሩአቸው (አጠፉቸው) 300 ሠረገላዎችን አጠፋ፡ ምርኮን በዘበዙ ኢትዮጵያውያንም ፈጽመው ወደቁ ይህም በኢትዮጵያ ንጉሥ በዝራ ዘመን ነበር:: በእርግጥም የይሁዳ ንጉሥ አሳ ስለ ኢትዮጵያውያን ማንነት ሲናገር «ከዚህ ከታላቅ ሠራዊት» በማለት ነበር:: እንግዲህ የኛ ትምክህት ምኑ ላይ ነው:: አንድ ሚሊዮን ሠራዊት ለዚያውም በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጥቂት በነበረ ጊዜ ያን ያህል ጦር በእስራኤል ምድር ከተሰባበረብን የብሉይ ኪዳን ተስፋ የኛ ነው ካልን አስደንጋጭ ይሆናል:: (ይቅርታ እናደርጋለን ምክንያቱም እኛ ሄድንባቸው እንጂ መጥተውብን አይደለም በተጨማሪም ክርስቲያኖች ስለሆንን ሁሉን ይቅር እንላለን! ባጠቃላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ በመሆኑ ደግመን አሜን! እንላለን) በእርግጥ የብሉይ ኪዳን ተስፋ



በክርስቶስ ኢየሱስ የኛ ነው ካልን በእርግጥም ሰማይም ምድርም ይስማማል እላለሁ:: ለእስራኤል ቅርበት አላቸው ከሚባሉ አገሮች ውስጥ ግሪክ ቀዳሚዋ ነች:: አስቀድሞ ለአይሁድ ቀጥሎም ለግሪክ ለአሕዛብ ሁሉ በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ያስተዋውቅ ነበር::

ጌታ ኢየሱስ ለኛ ያደረገልንን ማንኛውንም የበረከት ጥሪ ተቀብለን ባዘጋጀው ጥሪ ላይ መሣተፍና ሙሉ ክብር ለማንነታችን ሳይሆን ለእርሱ ማንነት የሰጠ የኢትዮጵያ፡ የግብፅ፡ የፍልስጥኤም፡ ሞዓብ፡ አሞን፡ የተባበሩት አሜሪካ፡ ታላቋ ብሪታንያ (መጽሐፍ ቅዱስ ግን ታላቋ የሚላት የሚገባት እስራኤል ብቻ ነች እንዲያውም የምድር ሁሉ ጌጥ ይላት የለ?) ወዘተ የክብሩ ተካፋይ ይሆናሉ::

እስራኤል በብዙ ጦርነት ተዋግታ ድል አድርጋለች በተጨማሪም ስለ ሴቶችና ስለ ሕፃናት ምርኮ አያያዝ ፈፅሞ በግልጥነት ተቀምጧል:: የአንዳንድ አገር ወታደሮች አንድ ከተማ በጦርነት ሲይዙ የመጀመሪያ ሥራቸው ምርኮኛ ሴቶችን መድፈር ሲሆን እስራኤል ግን በወጉ እነዚህን ሴቶች ይይዛሉ፣ የመረጧቸው ከሆነ አንድ ወር በመጠበቅ ጠጉር ተላጭቶ የምርኮ ልብስ ተገፍፎ ለቅሶ ቆሞ በወጉ ተድረው ይኖራሉ:: ለጦርነት፣ ለምርኮ፣ ለሠላም፣ ለዕርቅ፣ ሕግና ሥርዓትን ያሳየ የእስራኤል አምላክ ለዘለዓለም ይባረክ::

## 7. የአሮን ጢም

"ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፡

እነሆ፡ መልካም ነው፡ እነሆም፡ ያማረ ነው።

ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፡

እንደ አሮን ጢም፡

በልብሱ መደረቢያም እንደሚወርድ ሽቱ ነው።

በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፡

በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን

ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።" መዝ. (133) ፡1-3

ይህ የዳዊት የመዓርግ መዝሙር ነው። የወንድሞችን ኅብረትና አንድነት የሚጋብዝ የዘላለም በረከት ነው። የወንድሞች በኅብረት የመቀመጥ እድል ፈንታን የሚተነብይ ክፍል ሲሆን በዚያ እግዚአብሔር የፈቀደው ሽቱ፣ ጠልና በረከት አለ። እግዚአብሔር መልካም ነው። ወንድሞችም በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው። በመሆኑም በወንድሞች ኅብረት ላይ እግዚአብሔር አለ ማለት ነው።

የወንድሞች ኅብረት መለኪያ የሆነው የሽቱ አወራረድ ሲሆን ይህም ሽቱ ከራስ እስከ ጢም ከዚያም አልፎ መደረቢያ የሚደርስ የእግዚአብሔር ቸርነት ነው። ይህ ቸርነት የሚጀምረው ከራስ ጠጉር እስከ ጢም ድረስ ይሆናል። በራስና በፊት ላይ ያለ ጠጉር በሽቱ ከረሰረሰ በኋላ ወደ መደረቢያ ይወርዳል እንግዲህ ጠጉርና ጢም እንደ አሮን ላሉት ለከበሩ ሊቀ ካህናት የበረከት ሽቱ የሚጀምርበት ሥፍራ ነው።



ከእስራኤላውያን ሕዝብ ሁሉ ጢሙ ረጅም የሆነው አሮን ነው በመሆኑም እስከ አሮን ጢም ድረስ ይወርዳል በማለት የበረከቱ አወራረድ ይዞታን ያሳያል። አንድ ጉባኤ ትክክለኛ ኅብረት ቢኖረው በንጹህ ልብ፣ በቅንነት፣ በአንድነትና በወንድማማችነት በጌታ ፊት ቢሰባሰቡ በመለኮታዊው ዓለም የአሮን አክሊል ላይ የሚወርደውን ሽቱ እስከ ተገረገገው ጢም ድረስ በራእይ ሲወርድ መመልከት ይቻላል። የተረበሸ ሳይሆን ቀስ ብሎ እየተንጠባጠበ የሚወርድ አስቀድሞ ጠጉርንና ረጃጅም ጢሞችን አረስርሶ ቤቱን በሽቱ አውዶ በመደረቢያ ላይ ይንጠባጠባል።

በእስራኤል ካህናትና መምሕራን ዘንድ ከተለመዱ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሽቱ ወይንም ዘይት ራስን መቀባት ነበረ። "አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም፡ እርስዋ ግን እግሬን ሽቱ ቀባች። ስለዚህ እልሃለው፡ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ኃጢአትዋ ተሰርዮላታል፡ ጥቂት ግን የሚሰረይለት ጥቂት ይወዳል።" (ሉቃ. 7፡46-47) ይህ ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ሲሆን ጌታ በፈሪሳዊውና በለምጻሙ ስምዖን ቤት ያስተማረው ነው። ስምዖን ለእስራኤል መምህራን ይህ እንደሚደረግ ያውቃል ኢየሱስን ግን ገና በጥርጥር ላይ በመሆኑ ይህን ሊያደርግለት አልፈቀደም። ስምዖን ለምፃም ሆኖ ሳለ ጌታን ይስመው ዘንድ ጌታ ፈልጎ ነበር ስምዖን ግን ይህን አላደረገም። ዘይትም ውኃም አላቀረበም። ይህች ኃጢአተኛ የተባለች ሴት ግን የኢየሱስን ጭንቅላትና እግሩን በሽቱ ቀባች። ብዙ መውደድ ብዙ ኃጢአትን ያጥባል እጅግ ወዳለችና በማለት ጌታ መሰከረላት። እንግዲህ የመምሕራንን ልብ የሚያረካው በአናታቸው የሚወርደው ዘይት ወይንም ሽቱ ነው። የአጋንንትንም መንጋ

የሚያቀጥለው እግዚአብሔር ገበታን ባዘጋጀና ራስን ዘይት በቀባ ጊዜ ነው:: እጅግ መውደድ ብዙ በማውራት ሳይሆን የሽቱን መዓዛ ለኢየሱስ በመስዋእት መልክ ማቅረብ ነው::

የሊቀ ካህናት አሮን የጢሙ ውበት የእስራኤል ውበት ነው እስራኤል በአንድነት ተሰብስበው ቢቀመጡ በአሮን ጢም እንደሚወርድ ሽቱ ውበትና ሞገስ ያለው የተለየ ሕዝብ ይሆናል:: የተብለጨለጨና የተንዠረገገ ጢም ላይ ያሉ የሽቱ ነጠብጣቦች ሲፈስሱ መመልከት ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጋር ያለ አንድነትን ይወክላል::

በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ 10 ላይ አንድ መቅሰፍት እናገኛለን ይኸውም ሁለቱ የአሮን ልጆች በእግዚአብሔር መሰዊያ ላይ ልዩ እሳት በማንደዳቸው የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ነደደ፣ ሁለቱንም እዚያው አቃጠላቸው:: ከመቅደሱም ፊት ወስዶ በሌላ ስፍራ ቀበሩአቸው:: በዚህን ጊዜ አሮን ሁለት ልጆችን በአንድ ጀንበር በማጣቱ ራሱን ሊስትና ከቁጥጥር ውጭ በመሆን በጢሙ ላይ መንጨትን ሊያደርስ ይችል ነበር:: እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት አሮንን የመከረው ቢኖር ስለ አሮን ጢም ጉዳይ ነው:: "ሙሴም አሮንን፣ ልጆቹንም አልዓዛርና ኢታምርን፣ እንዳትሞቱ በማህበሩም ሁሉ ላይ ቁጣ እንዳይወርድ ራሳችሁን አትንጩ፣ ልብሳችሁንም አትቀደዱ፤ ... የእግዚአብሔር የቅባዓት ዘይት በላያችሁ ነውና እንዳትሞቱ ከመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አትወጡም አላቸው:: እንደ ሙሴ ቃልም አደረጉ::" (10፡6-7)



በዚህን ጊዜ አሮን ጢሙን ቢነጭ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ማኅበረሰብ ላይ ይሆን ነበር:: የእርሱ መንጨት የእስራኤልን ማኅበረሰብ ከስፍራው ያስነቅለው ነበር:: ይህን ከማኅበሩ ላይ ለቁጣ እንዳይወርድ ጢሙን፣ ዘይቱንና ልብሱን በስፍራው አኖረ:: እርሱም ከልጆቹ ይልቅ የእስራኤል ማኅበረሰብን በማክበር የእግዚአብሔርን ቃል ሰማ:: የወንድሞች በኅብረት የመቀመጥ በረከት የተገለጠው በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንዔም ጠል ነው ጠሉ የሚወርደው ከተከበረው ከእስራኤል ተራራ ከፅዮን ነው::

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ያለው የመጽሐፍ ክፍል ይህንን ያብራራል፡ ይህም የተራራው ስብከት በመባል ይታወቃል:: "ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፡ በተቀመጠም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፡ አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው እንዲህም አለ፡ ..." ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መካከል ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዝ ልዩ የትምህርት ርዕስ ነው:: በመንፈስ ድሆች ስለሆኑ፣ ስለሚያዝኑ፣ ስለየዋሆች፣ ጽድቅን ስለሚራቡና ስለሚጠሙ፣ ስለሚምሩ፣ ስለ ልበ ንጹሐን፣ ስለሚያስተራርቁ ማኅበረሰብ እንደ አርሞንኤም ጠል ያወርደዋል:: ከሰማይና ከምድር ጌታ አፍ እየተንጠባጠቡ ይፈስሳሉ:: ደቀመዛሙርት የዓለም ብርሃንና የዓለም ጨው፣ መሆናቸውን ሲገልጥ ከቀደመው ሕግ ይልቅ የተጠናከረ ሕግ ታክሎ "መዋደድ" የደቀመዛሙርት ሕይወት እንደሆነ አብራራላቸው:: የምጽዋትን ምሥጢርነት፣ የጦም፣ የጸሎት አድራሻን አስተምሮአል:: መዝገብን በሰማይ ለማጠራቀም የሚረዳን መስፈርት አስቀምጧል:: ይህንና የመሳሰሉትን የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት

ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል:: ሁሉ ይህን ጠል ከጠጡ በኋላ "ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ" (ማቴ. 7፥28) ወንድሞች በኅብረት ከተቀመጡ ከተራራ ላይ የሚወርድ ጠል ነው:: በጰንጠቆስጤ ቀን የተሰበሰቡ አንድ መቶ ሃያ ከሚበልጡ ደቀመዛሙርት ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር መንፈስ ይህን ቃል ያብራራዋል::

የእግዚአብሔር በረከት መነሻው ከምድር እንዲሆን እግዚአብሔር ፈቀደ:: የሰማያዊው በረከት መነሻ ምድር ነው:: እግዚአብሔርን እየፈሩ ከመለመን ይልቅ ማድረግ የሚገባውን በምድር ማድረግ:: ኅብረት ማለት መሰባሰብ ማለትን አይተካም፡ ኅብረት ማለት ወንድሞች የሚለውን ቃል ይተካል:: የወንድማማች አንድነት በጉባኤ ካለ የእግዚአብሔር በረከት እራሱ በጉባኤያችን ይገኛል:: እግዚአብሔር ለዘላለም ያዘዘው በረከት በመሆኑ የማይቀር ጸጋ ነው:: እኛ አንድነትን ሳንፈልግ በረከትን እንፈልጋለን:: በምድር የተመደበልንን ሥራ በወጉ ከፈጸምን የሰማያዊው ራሱ ይመጣል::

አሮን በመናገር መልካም ነበር "(ሌዋዊው ወንድምህ አሮን አለ አይደለምን? እርሱ ደህና እንዲናገር አውቃለሁ፡)" (ዘጸአ. 4፥14) ጠጉሩንና ጢሙን በማስረዘም የእስራኤልን ማኅበረሰብ ሲወክል ይኖር ነበር:: ሙሴ ከንፈረ ቆላፋ ሲሆን አሮን ግን አንደበተ ርቱዕ ነበረ:: ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር አፍ ለአፍ ሲነጋገር አሮን ግን ከሙሴ አልያም በሕልምና በራእይ የጌታን አሳብ ይረዳል:: እንግዲህ አንደበተ ርቱዕ ወይንም ቆላፋ መሆን ከጌታ ዘንድ የክብር ድምፅ መስማት ምልክት አይደለም ብዙዎች በመናገር መልካም ሲሆኑ ጌታን በማጸመጥ ደግሞ ደካማ ሆነው ስናገኛቸው ግራ ሊገባን አይገባም::



አሮን ሙሴን በሦስት ዓመት ይበልጠዋል (ዘጸአ. 7፥7) ነገር ግን አሮን ምንም ሊቀ ካህናት ቢሆን ታናሹ ወንድሙን ሲጠራው ጌታዬ በማለት ነበር:: (ዘጸአ. 32፥22) ሙሴ በአብዛኛው ወደ ተራራ ሲወጣና ከጌታ ጋር ሲነጋገር በእስራኤል ላይ ፍርድን የሚፈልጉ ነገረተኞች የተባሉ ግን ለአሮንና ሖር የተጠበቁ ነበሩ:: (ዘጸአ. 24፥14)

አሮን በተንዠረገው ጢሙ ላይ የከበረውን ሽቱ አፍስሶ የጌታን ቃል አፉንና ጢሙን በማንቀሳቀስ ሲናገር ምንኛ የጌታ ቃል የከበረ ይመስል እንደነበር በሕሊናችን እንሳለው:: «የእግዚአብሔር ድምፅ በታላቅ ክብር ነው::» መዝ. (29) ፥4:: በዘጸአት 30 ላይ የክብሩ ሽቱ አዘገጃጀት በውስጡ ከያዙት ቅመማ ቅመም ጋር ተገልጦ ሲታይ እንዴት ይማርክ እንደ ነበር መመልከት ይቻላል:: ከርቤ፣ ጣፋጭ ቀረፋ፣ የጠጅ ሣር፣ ብርጉድ፣ የወይራ ዘይት በቀማሚ ብልሃት እንደ ተሠራ ቅመም ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ያስደንቅ ነበር ይህም ለአሮን ብቻ ሳይሆን ለልጆቹና ለልጅ ልጆቹ የተቀደሰ የቅባት ዘይት ነበር:: አሮን የገባበትና የወጣበት ሥፍራ በዚህን አይነት ውበትና ክብር ከሆነ ዛሬስ የጌታን ቃል ስንናገር በሕዝብ ልብ ውስጥ የሚፈጥረው መለኮታዊ መዓዛና ቅመም ሁሉ ይመዝነዋል:: ብዙዎች የጌታን ቃል ሰምተው ተነጫንጨው ሲወጡ የተስተዋለበት ጉባኤ ብዙ ነው ምክንያቱም ቃል አቅራቢው እንደ አሮን መለኮታዊውን ጸጋ አሳድጎ በዚያ ላይ ከአፉ አካባቢ ባለው ሽቱ ቤቱ ካልታወደ ሕዝቡን በምን ወደ ጌታ መሳብ ይቻላል?

"በውኑ የሚዳ አህያ ሣር ሳለው ይጮኻልን?

ወይስ በሬ ገለባ ሳለው ይጮኻልን?

የማይጣፍጥስ ነገር ያለ ጨው ይበላልን?

ወይስ የእንቁላል ውኃ ይጥማልን?" (ኢዮብ 6፥5-6)

እኛስ ጌታን ተስፋ አድርገን የምንኖር ቤተ ክርስቲያን ወይንም የጌታ አገልጋዮች ቃል አከፋለውን ሲሄዱ በዚያ ቃል ውስጥ መለኮታዊ መብል ሳይኖረው ቀርቶ እንደ ሜዳ አህያ ብንጮህ ምን ይገርማል? ዝማሬ፣ ትምህርት፣ መንፈሳዊ ወረቀቶች ተሰጥተውን በዚያ የሚበላ ነገር ከውስጡ አጥተን በሬው ገለባ ሲያጣ እንደሚጮኸው የኛ መንፈስ በመራቆት ብትጮኽ ምንኛ ይገርማል? የማይጣፍጥ ነገር ያለጨው የማይበላ ከሆነ እኛስ ጨው ይጣልበት እያልን እየጮኸን አይደለምን? እንቁላልስ ሌላው አካል ሳይኖረው ውኃው ብቻ ምን ይጥማል? ኢዮብስ ከባልንጀሮቹ አንደኛው ቴማናዊው ኤልፋዝ በነገር ሲጠቀጥቀው ይህንን ቃል በምሬትና በትካዜ ከተናገረ ሌሎቹ ሁለቱ በልዳዶስና ሶፋር ሲጨመሩበት ምንኛ ያዝን ይሆን?



# 8. የተፈተለ የፍየል ጠጉር

"በልባቸው ጥበበኞች የሆኑ ሴቶችም በእጃቸው ፈተሉ፣ የፈተሉትንም ሰማያዊውን ሐምራዊውንም ቀዩንም ግምጃ፣ ጥሩውንም በፍታ አመጡ። ልባቸውም በጥበብ ያስነሣቸው ሴቶች ሁሉ የፍየልን ጠጉር ፈተሉ።" (ዘጸአ. 35፥25-26)

ይህ ስጦታ በሙሴ አማካኝነት ከታዘዙት ጥቂቶች ነበሩ። ባስልኤል ለሚሠራው የቤተ መቅደስ ሥራ የሚያግዙ ነበሩ። ዋና ዋና የሚያስፈልጉ ነገሮች ወርቅና ብር ናስም፥ ሰማያዊ ሐምራዊ ቀይ ግምጃም፣ ጥሩ በፍታም፣ የፍየል ጠጉርም፥ ቀይም የአውራ በግ ቁርበት፣ የአቆስጣም ቁርበት፣ የግራርም እንጨት፣ ለመብራትም ዘይት፣ ለቅብአት ዘይትና ለጣፋጭ እጣን ቅመም፥ መረግድ፣ ለኤፉድና ለደረት ኪስ የሚደረግ ፈርጥ እንዲመጣ ሙሴ አዘዘ።

"ሙሴ ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ላዘዘው ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጦታ በፈቃዳቸው አመጡ።" (ዘጸአ. 35፥29) ሙሴ ሊሠራ የተፈቀደለት ሥራ እጅግ ውስብስብና ብዙ ቁሳቁስ የሚጠይቁ ነበሩ የእቃዎቹ አይነት ደግሞ ፈጽሞ የተለየዩ በመሆናቸው የተወሰኑ ሰዎች ሊያሟሉት የሚሞክሩት አልነበረም። ከደቂቅ እስከ ግዙፍ ቁሳቁስና መልካቸውም ፈዕሞ በጥበብ ተሠርተው መቅረብ የሚገባቸውና እንዲሁ የሰው ጥበብ ሳያስፈልጋቸው የሚገኙም አሉበት።

ጥበብ ከሚጠይቀው ሥራዎች በአብዛኛው ሴቶች የሚሠሩት ይገኙበታል ይህም ጥበበኛ የሆነች ሴት የምትፈትለው ፈትልን ያካትታል፥ ግምጃ፣ በፍታና የተፈተለ የፍየል ጠጉር ዋናዎቹ

ናቸው:: ሁሉ ሴቶች ይህን ማዘጋጀት አይችሉም ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ጥበብ በነፍሳቸው የነገሥ እስራኤላውያን ሴቶች ግን ጣቶቻቸው እንዝርትን ይይዛሉ የፍየል ጠጉርንም ይፈትላሉ::

የእግዚአብሔር ቤት በጥበብ የተመሠረተ የዘላለም አምድ ነው:: "ጥበብ ቤትዋን ሠራች፥ ሰባቱንም ምሰሶችዋን አቆመች::" (ምሳ. 9፥1) በመሆኑም ልባቸው በጥበብ ያስነሳቸው ሴቶች የፍየልን ጠጉር ፈተሉ:: በዚህም በመገናኛው ድንኳን ለሚያገለግሉ በተቀደሰው ካህናት ልብስና በሌሎች ተግባራት የሚውሉትን የፍየል ጠጉር ፈተሉ:: የሆነ ዕቃ ገዝቶ ከማምጣት ይልቅ በእጅ ተፈትሎ የቀረበ የፍየል ጠጉር ለእግዚአብሔር ሲቀርብ መሥዋእቱ ውበትን ያገኛል ታስቦበትና ጥበብ ታክሎበት የተገኘ የፍቅር መግለጫ ነበር::

በተፈጥሮ ፍየል ጠጉር የሌላት በመሆኑ የበረሃን አየር ጠባይ ትመርጣለች:: ጠጉሮችዋም ደቃቅ ከመሆናቸው ባሻገር ዘርዘር ብለው ይበቅላሉ ከጫንቃዋና ከአንገትዋ አካባቢ በቀር ያን ያህል ለፈትል የሚውል ጠጉር ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: ልባቸው በጥበብ ያስነሳቸው ሴቶች ግን ከዚህ አካል ላይ የሚገኘውን ጠጉር ሰብስበው በመፍተል ለቤተ መቅደስ ሥራ ያቀርባሉ:: ይህን ማድረግ በመቻላቸው ጥበበኞች ተባሉ::

በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ የማማ ንጉሥ ልሙኤል የልባምን ሴት ባሕርይ ያስቀምጣል (ምሳሌ 31፥10-25)

ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል?
ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል:: ...
የበግ ጠጕርና የተልባ እግር ትፈልጋለች፥



በእጆችዋም ደስ ብሎአት ትሠራለች:: ...
እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች፥
ጣቶችዋም እንዝርትን ይይዛሉ:: .....
ለቤትዋ ሰዎች ከበረዶ ብርድ የተነሣ አትፈራም፥
የቤትዋ ሰዎች ሁሉ እጥፍ ድርብ የለበሱ ናቸውና::
ለራስዋም ግብረ መርፌ ስጋጃ ትሠራለች፥
ጥሩ በፍታና ቀይ ግምጃ ትለብሳለች:: ...
የበፍታ ቀሚስ እየሠራች ትሸጣለች፥ ...
በኋላም ዘመን ላይ ትስቃለች:: ...

ይህች ልባም ሴት ከሁሉ ነገርዋ የምትደነቀው በሥራዋ ነው:: አንድ ሴት በአንድ ቀን ውስጥ የምትሠራው ቢለካ ብዙ ሴቶች ሊሠሩት አይችሉም፥ እንደ ነጋዴ መርከብ ናት በማለት ያስተዋውቃታል:: ሁሉ ነገርና ጥበብ ሰብስባ እንደ ያዘች ከመሆኑም በላይ እድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርጋለች:: ገና ሌሊት ሳለ ተነስታ ሁሉን በወጉ ትሠራለች::

ለእግዚአብሔር ቤትም ልባም የሆኑ ሴቶች አሉት በአንድ ቀን በጥበብ ተነድተው ብዙ ሥራዎች የሚሠሩ ናቸው ሁሉ ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔር ጥበብ ይከተታቸዋል:: ከቀይ ዕንቁ ከሚገኝ በረከት ይልቅ በእነዚህ ሴቶች የመንግሥትን ዕንቁ መነገድ ይሻላል:: ጣቶችዋ በሙሉ ወደ ፈትልና ወደ ስጋጃ ሥራ ያዘነበሉ ከመሆናቸውም በላይ አስቀድማ ለቤተሰቦችዋ ታዘጋጃለች ከዝናብ ብርድ የተነሳ አይፈሩም:: ተፈትሎ የተቀመጠ የበረከት እንጀራና ልብስ በመኖሩ በመጪው የመከራ ጊዜ ላይ ትስቃለች:: ሕዝቡ በብርድ ሲንቀጠቀጥ

እነርሱ ግን በእናታቸው ድካም ይመካሉ። ሁሉ ትጻር የዚህችን ሴት ማንነት ቢረዳ በዚህ ዘመን የሚታየው የትጻር ምስቅልቅል ባልተመለከትን ነበር ለባልዋ ዘውድ እንጅ ጥቃት አትሆንም።

በዚህ ባለንበት ዘመን አንድ ሰው በእግዚአብሔር ቤት ያለው የጥበብ አስተዋፅኦ በጣም ጥቂት ነው። በጥበብ ተፈትሎ እንደ ቀረበ እንደ ፍየል ጠጉር ለጌታ ቤት የሚያቀርቡ ሴቶች አልተገኙም። የእግዚአብሔርን ቃል ከመጽሐፍ አውጥቶና ፈትሎ በልብስ ደረጃ አዘጋጅቶ የሚያቀርቡትን ይሻል። በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ በእግዚአብሔር ጥበብ የጌታን ማዕድና ልብስ ለደቀመዛሙርት የሚያቀርቡትን ጌታ ይፈልጋል። ጥሬ በረከት ተሸክሞ መምጣት ይቻላል ነገር ግን በጸሎት፣ በጾጋ፣ በትህትና፣ በኑሮ የተፈተለ በረከት ለሚለብሰውም ይሞቀዋል ይህንንም ስጦታ ጌታ ከነፍሱ ይሻዋል። ነቢዩ ናታን ዳዊት የኦርዮን ሚስት ነጥቆ ባመነዘረበትና ባልዋን ኦርዮን ባስገደለ ጊዜ ያቀረብ የነበረው እውነት ፍቅርና ጥበብ የተሞላ ነበር። በዚህን ጊዜ ዳዊት ወደ ግራና ቀኝ ሳይል በጌታ ፊት እንዲወድቅ አደረገው። እውነትን በፍቅር መያዝ ጥበብ ነው። ለጌታ ፊትለን እናቅርብ ሶምሶን ጠጉሩን እንደ ጎነጎነ ጎንጉነን እንያዘው። ከማይቻል ከሚመስል ምንጭ የሚቻል በረከትን እናቅርብ።



## 9. የሶምሶን ጠጉር

"እነሆ፡ ትፀንሻለሽ፡ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፡ ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፡ እርሱም እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል።" (መሳ. 13፡5)

እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅ ማዳን ላቀደ እግዚአብሔር ገና ያልተወለደ ህፃን መፈለጉ የሚደንቅ ነው። ህፃን ከፈለገ ከህፃናት መዋያ መርጦ መውሰድ ይችል ነበር። ከወጣትም፣ ከጎልማሳም፣ ከሽማግሌም ቢሆን አንዱን ወስዶ አዳኝ አድርጎ ማስነሳት በቻለ ነበር። በተጨማሪም የእናት ማኅፀን ውስጥ ካሉትም ከፈለገ ብዙ ወላድ እናቶች ዘንድ መሄድ በቻለ ነበር። የሶምሶን እናት መካን ወደ ነበረች ሴት የጌታ መልአክ ተልኮ፣ የልጁ ወግ ተነግሮ፣ እናቲቱ ማድረግና አለማድረግ የሚገባትን ተነግሮ፣ ህፃኑ ተረግዞ፣ ተወልዶ አድጎ የጌታን ዓላማ ለማሳየት ተንቀሳቀሰ።

የሶምሶን ጠጉር ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ምላጭ እንዳያልፍበት ተወስኖ እንደሌሎች የሰውነት ክፍሎቹ ይህም ያለማቋረጥ ያድግ ዘንድ ተወሰነ። የሶምሶን ናዝራዊነትና ጠጉሩ ሳያቋርጥ ማደግ ለእግዚአብሔር የተለየ የሚለውን ስም አመጣለት። ለእግዚአብሔር የተለየ ማለት የተቀደሰ ሲሆን ይህም ከጠጉር እርዝማኔ ጋር አብሮ የሚታይ ነው። ጠጉሩ ዝም ብሎ የሚያድግ ከሆነ ናዝራዊ ይባላል ምላጭ ያልተመለከተ ጸጋ ለእግዚአብሔር የመለየትን ማንነት ያሳያል።

እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸጋ በመጨመር ያምናል በመሆኑም ሰዎች ጸጋ ላይ ምላጭ ያርፍ ዘንድ አይፈቅድም። ካናት ውስጥ እያደገ የሚሄደውን ጠጉር እስከ መጨረሻው ያድግ ዘንድ ይወድዳል።

ሶምሶን በፍልስጥኤማውያን ላይ ይነሳ ዘንድ ጠጉሩ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ መቆረጥ አይገባውም በመሆኑም ፍልስጥኤምን ለማጥፋት ጠጉርን ከእናት ማኅፀን ጀምሮ መጠበቅ ይገባል። መንፈሳዊውም ጠጉር ማደግ ከፍልስጥኤም መንፈስ ለመታደግ ይረዳል። ፍልስጥኤም እጅ የገባን መንግሥት ጠፍር ለማላቀቅ ቅድሚያ ጠጉርን ማሳደግ ተገቢ ይሆናል። ፍልስጥኤምና መለኮታዊ ጠጉር ግንኙነት አላቸው። ሳሙኤልም ቢሆን ንጉሥ ሳኦልን ያዘዘው ፍልስጥኤምን ፈጽመህ አጥፋ ነበር። ሳሙኤል ደግሞ በራሱ ላይ ምላጭ አላረፈበትም። ሳኦል የተወውን ንጉሥ አጋግን በመሠዊያ የቆራረጠው ሳሙኤል ነበር ከሳኦል እጅ ያመለጠው በሳሙኤል ሰይፍ ተያዘ።

## 9.1. በሰባት የተጐነጐነ ጸጋ

“እርሱም፡ የራሴን ጠጕር ሰባቱን ጕንጕን ከድር ጋር ብትጐነጕኝው፡ በችካልም ብትቸክዪው፡ እደክማለሁ፡ እንደ ሌላም ሰው እሆናለሁ አላት።” (መሳ. 16፡13)

ሶምሶን ከተወለደ ጀምሮ የነበረውን ጠጉር በስርአቱ ይይዘው ነበር። የሶምሶን ጠጕር ሶምሶንን ይወክላል ጠጉሩ ከተወለደ ጀምሮ ያልተቀየረ በመሆኑ የሶምሶንን ማንነት ያመለክታል። ጠጕሩ ከራሱ ይጀምርና ትከሻው ላይ ይወርዳል ይህንን ስርአት ለማስያዝ



ይጎነጉነው ነበር። ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ የጠጕሩም ስርአት በእግዚአብሔር ቁጥር ተጐንጕኖ ተገምዷል ሰባቱን የእግዚአብሔር አሠራር ይወክላል።

መንፈሳዊ ጠጕር በወጉና በሥርዓቱ ካልተያዘ እንዲሁ ተቆራርጦ ሊወድቅ ይችላል አንዱ ከአንዱ ጋር በሚያደርገው መተሻሸት እየተነቀለና እየተቆራረጠ ያልቃል በሌላ መልኩም በሥርአት የተያዘ ጸጋ በሙሉ ለሚመለከተው ሁሉ ፍፁም ውብ ይሆናል። ጠጕሩ በአንድ ላይ ተሰብስቦ ቢታሰር ልዩ ልዩ አሠራር ዘዴዎችን አይወክልም ነገር ግን በሰባት ተጐንጕኖ ለአንድ ዓላማ ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲከፋፈሉ ፈጽሞ ውብ ይሆናል። አንድ መንፈሳዊ ሰው የጌታ ጸጋ እየበዛለትና እያደገለት ሲመጣ ሁሉን በወጉ ቢይዘው ይጠቅመዋል። ጥበብን በጥበብ፣ እውቀትን በእውቀት፣ ማስተዋልን በማስተዋል መልኩ ... ይዞ ቢጠቀምበት ሁሉ ወግ ይኖረዋል። አንድን ርእስ ከሌላው ሳይደባልቅ በወጉ ጎንጉኖ ቢይዘው ለሁሉ መፍትሄ ይሆናል።

የነቢዩ ዳንኤልም ጸጋ በሰባት ልዩ ልዩ አይነት የተከፈለ ነበር። መልካም መንፈስ፣ ጥበብ፣ ማስተዋል፣ እውቀት፣ ሕልምን መተርጎም፣ እንቆቅልሽን መግለጥ፣ የተቋጠረውን መፍታት ጸጋ እንደ ነበረው በዳንኤል ምእራፍ 5 ላይ ይገኛል። ይህ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ጸጋ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ተቀብለን በሰባት ጕንጕነን ለተለያዩ አግልግሎቶች ይውሉ ዘንድ ማድረግ ይገባል። ለሰባቱ ቀናት፣ ለሰባቱ ክፍለ ዓለማት፣ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት፣ ለሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፣ ወዘተ ይውል

ዘንድ ይገባዋል። የሶምሶን ጠጉር ከራሱ ላይ በቅሉ በሰባት ተጎንጉና እንደ ነበር ክርስቲያንም መለኮታዊውን ጸጋ ራስ ከሆነው ጌታ ተቀብሎ በወጉ ይጎነጉነው ዘንድ ይጠበቅበታል። "እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፤ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፤ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል።" (ቆላ. 2፥19) ራስ በሆነው ከክርስቶስ ላይ ተተክሎ ማደግ ይገባ ዘንድ ከዚያም ይጎነጎን ዘንድ ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምረን ሁሉን በስርአቱ ቢያዝ ውብ እንደሚሆን ነው። ለምሳሌ የእግዚአብሔር ብርሃን በሚል ርእስ አንድ ሰሞን ቢጠና በዚሁ ርእስ ትምህርት ላይ እየተጎነጎነ አንድ ወጥ የሆነ ውበት ማስያዝ ይገባዋል። በሌላ ሰሞን ደግሞ የእግዚአብሔርን ክብር በሌላ ጊዜ ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን የሰማዩን ውበት፣ በሌላ ጊዜ የምድሩን መንከራተት በሌላ ጊዜ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወዘተ በስርአቱ ይዞ ቢጎነጉን ሁሉ ውበት ይኖረዋል።

"... በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።" (መክ. 4፥12) ምንም እንኳ ጠጉር ብቻውን ከራስ ላይ ቢበቅልም ብቻውን ጥንካሬ ሊኖረው አይችልም ይልቅም አብሮ ከሚያድገው ጠጉር ጋር ተገምዶና ተያይዞ ቢያዝ ፍፁም ጥንካሬ ይኖረዋል ይህ ካልሆነ ሊበጠስ ይችላል። በክርስቶስ ተተክሎ ማደግ አንድ ትልቅ ቁም ነገር ቢሆንም ተገምዶ መጠበቅ ደግሞ እንዳይበጠስ ይረዳል።



## 9.2. የደሊላ ሽንገላ

"የፍልስጥኤማውያንም መኳንንት ወደ እርስዋ ወጥተው፤ እርሱን ሽንግለሽ በእርሱ ያለ ታላቅ ኃይል በምን እንደሆነ፣ እኛስ እርሱን ለማዋረድ እናስረው ዘንድ በምን እንደሆነ እወቂ፤ እኛም እያንዳንዳችን ሺህ አንድ መቶ ብር ሺህ አንድ መቶ ብር እንሰጥሻለን አሉአት።" (መሳ. 16፥5) "... እርስዋም፦ አንተ፦ እወድድሻለሁ እንዴት ትለኛለህ፤ ልብህ ከእኔ ጋር አይደለም? ስታታልለኝ ይህ ሦስተኛ ጊዜህ ነው፤ ታላቅ ኃይልህም በምን እንደ ሆነ አልነገርኸኝም አለችው። ዕለት ዕለትም በቃልዋ ነዘነዘችው አስቸገረችውም፤ ነፍሱም እስከ ሞት ድረስ ተጨነቀች።" (ቁጥር 15-16)

ሽንገላ ለሚለው ቃል ተስማሚ ማስረጃ የሶምሶምንና የደሊላ ጉዳይ ነው። ሽንገላ ፍፁም የጨለማ ሥራ ከመሆኑም በላይ ፍቅር በሚለው መጠቅለያ ተሸፍኖ መኖርን የሚፈልግ የዲያቢሎስ የመርዝ ሥራ ነው። ደሊላ ሶምሶንን በልዩ ፍቅር እንደምትወደውና ከእርሱ ይልቅ እርስዋ እውነተኛ ሆና የቀረበችበት ጉዳይ ነበር።

ሽንገላ ለአንድ ቀን የሚደረግ ተግባር አይደለም በአብዛኛው ውጤቱ ከፉ ፍሬ እስኪገለጥ የሚደረግ የዕለት ተዕለት ንዝንዛ ነው። በዚህ አጋጣሚ የምመክረው ጉዳይ ቢኖር የሰው ልጅን የሚጐዳው አንድን መርዝ በዳቦ ሸሽጐ በሚመጣ ሰው ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በክርስቶስ ትምህርት የምኖር ነኝ በማለት ሲመጣ ፍጹም ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። የክርስቶስን ስም እንደ ዳቦ መሸፈኛ ተጠቅሞ የራሱን ድብቅ ምሥጢር ሸሽጐ ሲቀርብ አደገኛ ይሆናል። የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለይበት አንድ ጉዳይ ዓማን ጠብሶ ሲበላ ነው። በዚያ

ውስጥ ያለ እሾክ እንዳይወጋው እያንዳንዱን ጥቃቅን እሾኽ እየመዘዘ እንደሚጠቀም የሰዎችንም ማንነት እየመዘነን ካላየን ልንረዳው አንችልም::

ሽንገላን ውጤታማ ለማድረግ ዋናው መጠቀሚያ የገንዘብና የሴት ፍቅር ነው:: በሶምሶን ጉዳይ ሶምሶን ደሊላን ይወድዳል ደሊላ ደግሞ ገንዘብ ፍለጋ የተሰማራች ሴት ነች፡ ለደሊላ የሚሰጣት የገንዘብ መጠን ደግሞ በአንድ ጊዜ አንዲትን ጋለሞታ ሴት የሚያከብር ነበር:: እያንዳንዱ የፍልስጥኤም መኳንንት አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር ሊሰጧት ቃል ተገብቶላታል:: የጌታን ጸጋ ለማዋረድ የተነሣ ፍልስጥኤም ሲሆኑ የሽንገላው ዋና ተሳታፊ ግን የፍልስጥኤም መኳንንቶች ነበሩ:: የሶምሶን ኃይል ቀጥተኛ ተጠቂዎች የፍልስጥኤም መኳንንት በመሆናቸው አስቀድመው የኃይልን ምሥጢር ማግኘት ነበር:: ሽንገላ ጠላት የሚጠቀምበት ዋናው መሣሪያ በመሆኑ ለዚህ ስለላ ደግሞ አስፈላጊ ነበረ::

ደሊላ ሶምሶንን የሸነገለችው ሶምሶን እስከ ሞት ድረስ እንዲጨነቅ በማድረግ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ሲሰላ ሶምሶምን ለደሊላ ያለው ፍቅር ከሞት የበረታ ነበር:: ነፍሱን እስከ ሞት አስጨነቀችው ሶምሶን ለደሊላ ያለው ፍቅር ከሞት በመበርታቱ ነፍሱ እስከ ሞትም እየተጨነቀች ከደሊላ ጉያ መውጣት ተሳነው:: በላዩ የነበረው ጸጋ ይወቅሰዋል:: ከሰዎች በሙሉ በረጅም ጠጉር ይኖር የነበረ ሶምሶን፡ ለእግዚአብሔርም ብቸኛ ሰው የነበረ ሶምሶን፡ ለደሊላ ሽንገላ እጁን ሰጠ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚያሳዝንና ከሚያሳፍር ታሪክ መካከል የሶምሶን ጠጉር በሽንገላ ምላጭ የተዋረደበት ቀን ነው:: በዚህ ትምህርት የጋለሞታ ፍቅር እንዴት ኃይለኛ እንደሚሆን ንጉሥ



ሉሞን አመልክቷል:: "እኔም ከሞት ይልቅ የመረረ ነገር መርምሬ አገኘሁ፡ እርስዋም ልብዋ ወጥመድና መርበብ የሆነ፥ እጆችዋም እግር ብረት የሆኑ ሴት ናት፤ ...::" (መክ. 7፡26) ሶምሶን በዚህች ሴት እጅ ለነበረ እግር ብረት በፈቃዱ ገባ:: ከዚህ እግር ብረት ለመውጣት ጠጉሩንና ክብሩን ለምላጭ አሳልፎ ሰጠ:: እስራኤልን ከፍልስጥኤም እጅ ያወጣል ተብሎ የተጠበቀ ሶምሶን በፍልስጥኤም ሽንገላና ምላጭ ስር ተካተተ::

## 9.3. የእግዚአብሔር ትዕግሥት

የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታና ትዕግሥቱን ለመመልከት በሶምሶን ራስ ስለነበሩት ሰባቱ ጉንጉን ጠጉር ማንበብ ማስረጃ ይሰጠናል:: እግዚአብሔር ጸጋውን ከሰጠ አይወስድም ተቀባይ ደግሞ እጅ ዘርግቶ መውሰድ ይገባዋል:: የወሰደውን ስጦታ ማንም እንዳይነጥቀው እግዚአብሔር ከለላ ያደርጋል::

የሶምሶን ጠጉር ጉዳይ ስንመለከት የእግዚአብሔርን ከለላ ያሳየናል:: በሶምሶን ጸጋ የኖረው በሶምሶን ጠጉር ላይ ነው ይህ ጸጋ ግን ፍልስጥ ኤማውያን አላወቁትም:: ግልጽ ሥፍራ ላይ ተቀምጦ ሳለ እነርሱ ግን መንፈሳዊ ዓይናቸው የጠፋ በመሆኑ በጠጉሩ ላይ የነበረውን ኃይል ማወቅ አልቻሉም:: ይህን ኃይል ለማወቅ በደሊላ ተጠቀሙ:: በሽንገላና በገንዘብ ኃይል የሶምሶንን ጸጋ የት ቦታ መሆኑን አወቁ::

እግዚአብሔር ለሶምሶን ጸጋ ታላቅ ጋሻ በማድረጉ የሶምሶን ጸጋ ሥፍራ ሊታወቅበት አልቻለም ነበር፡ የእግዚአብሔር ጋሻም ኃይሉን ሰወረባቸው:: የሶምሶን ኃይል የሚታወቀው በራሱ በሶምሶን ብቻ

ነው። ጸጋ ሰጭው ለተቀባዩ ሁሉን ያሳያል በመሆኑም የሶምሶን ጸጋ በእግዚአብሔርና በሶምሶን ዘንድ ብቻ የተሰወረ ነበር ሶምሶን ግን ነፍሱ ተጨንቃ ለጋለሞታ ፍቅር ሲል የእግዚአብሔርን ጋሻ አንሳ የእግዚአብሔርን ስጦታ ለሌላ አስረከበ። የእግዚአብሔርን ስጦታ ማንም ሊወስድ አይችልም የእግዚአብሔርን ጸጋ የተቀበለው ሰው ግን በፈቃዱ ለሌላ ሊያስረክብ ይችላል፤ ይህን ጸጋ ለሌላ ሊያስረክብ ሲነሳሳ ግን ፍፁም የሆነ የእግዚአብሔር ምክር እስከ መጨረሻው አይለይም። ሶምሶን የጸጋውን ኃይል ለማሳየት ጥቂት ጊዜ ሲቀረው ነፍሱ እስከ ሞት ድረስ ተጨነቀች። የእግዚአብሔር ስጦታ ይሻለኛል ወይስ የጋለሞታዋ የደሊላ ፍቅር? ሶምሶን ፈጽሞውኑ በዚህ ጭንቀት ከሚሞት ጸጋውን ያስረክብ ዘንድ ተስማማ፡ እግዚአብሔርም ከላዩ ላይ ተነሣ። "... እግዚአብሔርም ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም" (መሳ. 16፡20)

የእግዚአብሔር ትዕግሥት የሰውን ልጅ እስከ መጨረሻ መሸከም ይሆናል። ሶምሶን ነፍሱ እስከ ሞት ተጨንቃ ጸጋውን እስከ አስረከበ ድረስ የእግዚአብሔር ትዕግስት ከእርሱ ጋር ነበረች ፍልስጥኤማውያንም በተለያዩ ጊዜያት መጥተው እስኪፈታተኑት ድረስ ሶምሶን በተሰጠው ጸጋ ይጫወት ነበር። እግዚአብሔር ሰጠ ሶምሶን አስረከበ።

አንድ ጉዳይ ነፍሳችንን እስከ ሞት ድረስ ካስጨነቀን ከፍተኛ ጥፋት ከፊታችን ወይንም ዘላለማዊ ድል አለ። ነፍስን እስከ ሞት ድረስ የሚያስጨንቅ ነገር አንድ ሰው በሁለት የተለያዩና የሚቃወሙ ኃይላት ሲገፋ ነው። እግዚአብሔር በፍቅር ይለምናል ደሊላ ደግሞ በሽንገላ ታታልላለች በዚህን ጊዜ በመሃል ያለው ሰው እስከ



መጨረሻው ይወጠራል። እግዚአብሔር በጉልበት ሶምሶንን መንካት አይፈልግም ደሊላም በጉልበት ሶምሶንን መጎተት አትችልም አሁን ባለሙሉ መብትና ፈቃድ የሆነው ሶምሶን ነበር። ሶምሶን ሁለቱንም ለማጣት አይፈልግም ከዚህ ሁሉ በኋላ የሶምሶን ልብ ወደ አንዱ አጋደለ፥ ወደ ደሊላ። ደሊላ እስከ መጨረሻው ብታዋጣው መልካም ነበር ነገር ግን ገንዘብዋን በነፍስ ወከፍ አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር ከእያንዳንዱ መኳንንት ተቀብላ በዚህ ገንዘብ በልጥጋ ሶምሶን አይኖቹ ወጥተው በዚህ ውጥረቱ ተፈታ። ደሊላም ከዚህ በኋላ ዓይኑ ስውር ጓደኛ አትፈልግም።

## 9.4. የሶምሶን ጠጉር እንደ ገና መብቀል ጀመረ

"የራሱም ጠጉር ከላጩት በኋላ ያድግ ጀመረ።" (መሳ. 16፡22) የእግዚአብሔር ትዕግሥት አሁንም የሚደንቅ ነው። በሶምሶን ጠጉር የነበረው ኃይል ከተወሰደም በኋላ እንደገና ማደግ ጀመረ። ፍልስጥኤማውያን የሶምሶንን ዓይን ካወጡት በኋላ፣ ወፍጮ ይፈጭና ይዘባበቱበት ከጀመሩ በኋላ የሶምሶን ጠጉር እንደ ገና ይበቅል ጀመር።

የፍልስጥኤማውያን አለማስተዋል እዚህ ላይ እንደ ገና ተገለጠ። አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር በነፍስ ወከፍ አዋጥተው በደሊላ አማካኝነት ሽንግለው ኃይሉን ካወቁበትና ጠጉሩን ከላጩት በኋላ የሶምሶን ጠጉር ማደግን ልብ አላሉም። ያጠፋቸው ኃይል መልሶ ሲበቅል መከላከልን ረሱት ዓይኑን በማውጣታቸውና ተራ ሰው በማድረጋቸው ከእንግዲህ ወዲህ በአናቱ ላይ እየበቀለ ያለውን ጸጋ መከታተል አልሆነላቸውም። ቢያስተውሉ ኖሮ ምላጭ ገዝተው

በየማለዳው ጠጉሩን መላጨት ይገባቸው ነበር። የወደቀ መልሶ የማይነሳ መሰላቸው።

"ዛፍ ቢቈረጥ ደግሞ ያቈጠቍጥ ዘንድ፥
ቅርንጫፉም እንዳያልቅ ተስፋ አለው።
ግንዱም በመሬት ውስጥ ቢሞት፥
ከውኃ ሽታ የተነሳ ያቈጠቍጣል፤" (ኢዮብ 14፥7-9)

ሰባቱ ረጃጅም የሶምሶን የተጐነጐነው ጠጉር በፍልስጥኤማውያን መንደር ቢገባም እነዚህን ጠጉር ያበቀለ ጒንቅላት ፈጽሞውኑ አልጠፋም። ሶምሶን በፍልስጤማውያን የናስ ሰንሰለት ውስጥም ቢገባ በተፈጥሮ የነበረውን የጠጒር እድገት ሥርአትን ጸጋ ሊቋቋሙ አልሆነላቸውም። በፍልስጥኤማውያን መንደር የሶምሶን ጠጉር አደገ። የሶምሶን ጠጉር አስተዳደግ ግን ከተፈጥሮ ሂደት ቀስ በቀስ መብቀልና ማደግ ሲሆን ይህም ጊዜ የሚጠይቅ ተግባር ነበር፤ ይህ ጊዜ ግን ፍልስጥኤማውያን በሶምሶን የሚዘባበቱበት ወቅት ነበር።

መንፈሳዊያን የሆኑ ሰዎችም መንፈሳዊ ጠጉራቸውን በብዙ ሽንገላና ጭቅጭቅ አልፈው ሊሰጡ ይችላሉ። እግዚአብሔር ይመክራል፣ ያስተምራል፣ ይገስፃል ይህ ሁሉ ችላ ተብሎ ከሆነ በፍልስጥኤም እጅ የማይወድቅበት ሁኔታ አይኖርም። አንድ ጊዜ አልፎ ከተበጠ በኋላ ግን የቀድሞውን ይዞታ ለማስመለስ ጊዜ ይጠይቃል። እንደ ሶምሶን ጠጉር ቀስ በቀስ ይበቅላል በዚህን ጊዜ ግን የጠላት መንደር መጠቀሚያ ይኮናል። "የእግዚአብሔር መንግሥትም እንደዚህ ናት፤ ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፥ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል፥ ያድግማል።"



(ማር. 4፥26) የሶምሶንም ጸጋ እንዲሁ ነበር ከተላጨ በኋላ የጠጉሩና የጸጋው አስተዳደግ ይህን ሥርዓት ማዛባት አይቻልም።

አንድ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ጸጋውን ከጣለ በኋላ ወደ ቀድሞ ይዞታው ለመመለስ ጊዜያትን ይጠይቃል። ከሶምሶን እናት እንደበቀለው ጠጉር ይሆናል ይመሻል ይነጋል እንዴት እንደሆነ ሳይታወቅ ያድጋል።

## 9.5. ሁለቱ ምሶሶዎች

ሶምሶን በሰባቱ ጉንጉን ጠጉሩ ያን ያህል ሥራ ሳይሰራበት ተላጨ እንደ ገና በበቀለው ጸጋ ግን ሦስት ሺህ ፍልስጥኤም መኳንንቶቹንና ሕዝቦችን ገደለ። አይን ወጥቶና ዕውር ተሁኖ ባለጸጋ መሆን ይቻላል። ሶምሶን ሰው እየመራው ዕውር ሆኖ በበቀለው ጠጉር ተጠቀመ። ዛሬም በጌታ ጸጋ አንዳንድ ሁኔታዎችን ማከናወን ብንችልም ለአይናማነታችንና ከውርደት ለማምለጣችን ማስረጃ አይሆንም።

የሰው ልጅ ዋናውን ጸጋ ሳያውቅ ይኖራል ጸጋው ከተወሰደበት በኋላ ግን ይገባዋል። ተወስዶበት እንደገና በበቀለችው ጥቂት ጸጋ ትልቅን ሥራ ይሠራበታል። ትልቁን ጸጋ ተሸክሞ ቢጋዝና በሶሬቅ ሸለቆ ወደሚገኙ የጋለሞቶች መንደር ይሸነጋገሉበታል ከዚህ በኋላ ግን መንፈሳዊ ዓይን ከታወረ በኋላ በቀል ይጀመራል የፍልስጥኤማውያን ማንነት ይረዳል። ፍልስጥኤም ሶምሶን በእጃቸው ሲገባ መግደል ሲገባቸው ዓይን በማውጣት፣ ወፍጮ ፈጪ በማድረግ፣ መዘባበቻና መሳለቂያ በማድረግ በሕይወቱ ላይ የመጨረሻ ክፉ ነገር ሁሉ አደረጉበት። እግዚአብሔር የሰጠንን ጸጋ

ችላ በማለት ከተወሰደ በኋላ ለምን ለመንቃት እንሞክራለን በትልቁ ሳንጠቀም በትንሹ ለመጠቀም ለምን እንሞክራለን?

ከጠላት ጋር ኅብረት ማድረግ መሞከራችንና የሰይጣንን ደባ እንደ ከንቱ ነገር መቁጠር ተገቢ አይሆንም። የዲያቢሎስን ሥራ ለማፍረስ የእግዚአብሔር ልጅ መገለጥ ከተገባው የዲያቢሎስ ሥራ ተራ ነው ማለት አይቻልም። የእግዚአብሔር ልጅ እንኳ ተገልጦ እስከ ሞት በመታገል፣ በጌቴሴማኒ የደም ላብ የሚመስል ነጠብጣብ ፈስሶ በመሞት እንጂ የሰይጣን ሥራ በደከመ ጉልበት አልወደመም። በሌላ በኩልም በኢዮብ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ሰይጣን ኢዮብን እንዲመታ ሲፈቀድለት ኮርኩሞ አይደለም የለቀቀው ይልቁም ከእግሩ ጀምሮ እስከ እግሩ ጣት ድረስ በክፉ ቁስል ወዲያው መታው። የአገርንና የሕዝብን አባት ኢዮብን እንዲህ በደቂቃ ማውደም ፍላጎት ካለው አካል ጋር እስከ ደም መፋሰስ ልንታገል ይገባል።

ምንም እንኳ ሶምሶን በዚህ ሁኔታ ሰባቱን ጉንጉን ጠጉር ለፍልስጥኤም አሳልፎ ቢሰጥም እግዚአብሔር ግን በእውቀቱ ባለጸግነት የሚወዳደረው ባለመኖሩ አሁንም አልተጎዳም። የሶምሶን ጠጉር ከመላጨቱ በፊት የፍልስጥኤም መኳንንቶች ብዙ ጥፋት አልደረሰባቸውም። የሶምሶንን ጠጉር ከላጩ በኋላ ግን አስቀድመው የተገደሉት የፍልስጥኤም መኳንንቶች ናቸው። "ሶምሶንም፡ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ልሙት አለ፡ ተጎንብሶም ምሰሶቹን በሙሉ ኃይሉ ገፋ፡ … በሕዝቡም ሁሉ ላይ ወደቀ፡ በሞቱም የገደላቸው ሙታን በሕይወቱ ሳለ ከገደላቸው በዙ" (መሳ. 16፡30) የፍልስጥኤም መኳንንቶች ለደሊላ ገንዘብ በመስጠት የሶምሶንን ኃይል ለማወቅ



ታገሉ፡ ገንዘባቸውን አወጡ ሶምሶንን ተጫወቱበት እግዚአብሔር ግን ሶምሶን ከተዋረደ በኋላ ክብሩን አስጠብቋል። መኳንንቱም ጭምር ይገደሉ ዘንድ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጣ በማሰሉት ጉድጓድ እነርሱ ገቡበት። የሶምሶን የጥቃት አቅጣጫ በፍልስጥኤማውያን መኳንንት ሁሉ ላይ ሆነ።

የእግዚአብሔርን ጸጋ ብናግፋፋ፣ ለፍልስጥኤም አሳልፈን ብንሰጥ፣ ለሽንጋዮች እጃችንን ብንሰጥም የምንጎዳው እኛው ነን። እግዚአብሔር ግን በፈለገው መንገድ የራሱን ክብር ከጆርባ ቆሞ ያስጠብቃል እንዲያውም በተሻለ ሁኔታ ሊያስጠብቅ ይችላል። የእግዚአብሔር ጉዳት ግን እኛ በመጎዳታችን ብቻ ነው። በዚሁ አጋጣሚ የነቢዩ ዮናስን አለመታዘዝ ልንመለከት እንችላለን። ዮናስ ባለመታዘዙ ከእግዚአብሔር ፊት ኮበለለ፡ በመኮብለሉም ታላቁ መርከብ እጅግ ተናወጠ በዚያም የነበረ ንብረት በሙሉ ወደመ፡ የመርከቡ ሕዝብ ተጨነቀ። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ግን ዮናስ ላይ የደረሰ ጉዳት አለ። "ዮናስንም ወስደው ወደ ባሕሩ ጣሉት ባሕሩም ከመናወጡ ጸጥ አለ።" (ዮና.1፡15)

ታላቁ ነቢይ በባሕር ወደቀ በጨለማም ተጣለ ጭንቀትና መከራ በዮናስ ላይ ሆነ። ዮናስ ይህን ሲናገር፡ "ውኆችም እስከ ነፍሴ ድረስ ከበቡኝ፤ ጥልቁ ባሕር በዙሪያዬ ነበረ፤ የባሕሩ ሣር በራሴ ተጠምጥሞ ነበር።" (ዮና. 2፡6) በእግዚአብሔር በኩል ግን የደረሰ ጉዳት የለም። በዚህም ውስጥ ቢሆን እግዚአብሔር ክብሩን ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ዮናስ በመጣሉ ለእግዚአብሔር የተጨመረውን ክብር በምዕራፍ 1 ቁጥር 16 ይገኛል። "ሰዎችም እግዚአብሔርን እጅግ

ፈሩ፣ ለእግዚአብሔርም መሥዋዕትን አቀረቡ፣ ስእለትንም ተሳሉ:: በመርከቡ የነበሩ ሰዎች በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ዞሩ፣ ዮናስ ግን ተጎዳ:: እንግዲህ የእግዚአብሔር ጉዳት ዮናስ ሲሰቃይ ማየቱ ብቻ ነው:: እኛም ለእግዚአብሔር ብንታዘዝ እግዚአብሔር ይከብራል እኛም እንባረካለን፣ ባንታዘዝ ግን ባለመታዘዛችን የእግዚአብሔር ክብር አይጎድልም የራሱን ክብር በስተኋላ ቆሞ ያስጠብቃል:: የክፋት መንፈሳዊ ሠራዊትም ይህን ሊያውቁ ግድ ነው:: አንድን የእግዚአብሔርን ሰው ለማዋረድ መነሣት ይችላሉ ይህ ሰው እጅ ቢሰጣቸው ለእነርሱ ታላቅ ደስታ የሆነ ሊመስላቸው ይችላል ነገር ግን በዚህ ሰው መያዝ ተሰብስበው ደስታን ባደረጉ ቀን ታላቁ የእግዚአብሔር መቅሠፍት በላያቸው እንደሚወድቅና የእነርሱ መኳንንቶች የደስታቸው ቀን የታላቅ ኀዘን ቀን ይሆንባቸዋል:: የሶምሶንም እንዲሁ ነው የፍልስጥኤም መኳንንቶች ሶምሶንን ቢያስላፌቱም በመጨረሻ ሕይወታቸው በሶምሶን ይላጫል:: ዮናስ ባለመታዘዝ ወደ ሌላ አገር ቢኮበልል በዮናስ አለመታዘዝ የአንድ መርከብ ሕዝብ ወደ ጌታ ይመጣል በመጨረሻ በዮናስ የነነዌ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ይዞራል በመሆኑም በመቼውም ጊዜ እግዚአብሔር አይጎዳም ወይም ክብሩን አይለቅም::

ከዔደን ገነት ጀምሮ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት ሁልጊዜ ታጥቆ ይነሳል:: የቀደመው እባብ ሔዋንን በፍሬዋ አማካኝነት ከገነት ለማባረር ግማሽ እውነት ከግማሽ ሐሰት በመደባለቅ አታለላት ይህ በመሆኑ አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረሩ:: በዚህን ጊዜ የቀደመው እባብ ድል ያደረገ መስለው ደግሞም አስቆጠረ



እግዚአብሔርም ከጉዳዩ ጀርባ በመሆን የሰይጣንን ድል በሌላ የጌታ ድል ቀየረበት:: እባቡ ዘመኑን በሙሉ በሆዱ እንዲሄድ፣ ዘመኑን በሙሉ አፈር እንዲበላ፣ ከሴቲቱ የሚወለደው የእባቡን ጭንቅላት እንደሚቀጠቅጠው ተነገረው:: ይህን ሁሉ ሲመዝነው ከወጪ ቀሪ የተጎዳው የቀደመው እባብ እንጂ የጌታ የዘላለም ዕቅድ አይደለም:: ሰይጣን ይህን ሁሉ ሲመለከት በቀረብኝ ይላል::

ኤልዛቤል ነቢዩ ኤልያስን እገድልሃለሁ ብላ ስፍራ አስለቀቀችው:: ጌታ ግን ከጉዳዩ ጀርባ ቆሞ ኤልዛቤል የምትቀጠቀጥበትን ቅባት በተራራው ላይ ለነቢዩ ኤልያስ በመስጠት ለኢዩ ይዞለት መጣ:: ከፎቅ ተወረወረች ውሾችም ደሟን ላሱት::

ሰይጣን ክርስቶስን በአደባባይ በሁለት ወንበዴዎች መካከል በቀን በተራራ ላይ እንዲሰቀል ተዋከበ:: እግዚአብሔር ግን በዚሁ ጌታ ክርስቶስ የሰይጣንን ሥራ ቀጠቀጠ፤ ለተቀበሉት ሁሉ ከሰይጣንና ከሞት እስራት ለዘላለም ፈታ፤ እርሱ ግን በእሳት ባህር ከነደጋፊዎቹ (Sympetisers) ጣላቸው:: በአጭሩ እግዚአብሔር ያቅዳል ይተገብራል:: ሰይጣን የተተገበረውን ጉዳይ ለማበላሸት ይነሳል ደግሞም ያበላሻል:: እግዚአብሔር ደግሞ የተበላሸበትን ተግባር በተሻለ ክብርና ጸጋ ያስነሳዋል ነገር ግን የቀደመውን ሥራ ሊያበላሽ የተነሳውን አካል ለዘላለም ያዋርደዋል:: ከጌታ ጋር በፍቅርና በመታዘዝ የኖረና የተገዛ ሰውና ፍጥረት እንዴት ተባረከ! ጉዳዩን ያበላሸ ደግሞ እንዴት የተረገመ ነው!

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ የእግዚአብሔር ዕቅድና ሥራው ሲበላሽ ራሱ በተሻለ ክብርና ጸጋ የሚያስነሳ ከሆነ የሰው ልጅ የጌታ ሥራ

ሲበላሽ መጨነቅ የለበትም ማለት ነው? አይደለም በፍጹም! የእርሱ ዕቅድና ሥራ ሲበላሽ በመንፈስ ቅዱስ ልናዝንና ልንቆጭ ይገባናል። በተጨማሪም ጌታ መንፈሳችንን ይመዝናል በዚህም ይባርከናል። ፍቅራችንም ይፈተንና ያልፋል።

የፍልስጥኤም መኳንንቶች የመሞታቸውን ሁኔታ ሲያመቻቹ ሶምሶንን በሁለት ምሰሶዎች መካከል አቆሙት ጠጉሩን አንድ ጊዜ ላጭተው መኪታተል ሲገባቸው ረሱት። አሁን ደግሞ ጥፋታቸውን ሲያቀርቡ ሶምሶንን በሁለት ምሰሶች መካከል አቆሙት "ሶምሶንንም ከግዞት ቤት ጠሩት፤ በፊታቸውም ተጫወተ፤ ተዘባበቱበትም፤ በምሰሶና በምሰሶም መካከል አቆሙት። ሶምሶንም እጁን የያዘውን ብላቴናን፤ ቤቱን የደገፉትን ምሰሶች አጠጋባቸው ዘንድ፤ እባክህ፤ አስይዘኝ አለው።" (መሳ. 16፡25-26)

ሶምሶን ዓይኖቹ ጠፍተዋል፤ ዓይኖቹ ቢጠፉም በፍልስጥኤማውያን አዳራሽ የቆሙት ሁለት የተጠጋጉ ምሰሶዎች መኖሩን ያውቃል። የሁለቱ ምሰሶችን ስፍራ ለማግኘት የሚመራውን ብላቴና ጠየቀው። በዚህን ጊዜ የሶምሶን ጥያቄ እስራኤልን ለማዳን አይደለም ነገር ግን ለበቀል ብቻ ነው። የበቀሉም ትኩረት ስለ ሁለቱ ዓይኖቹ ነው። ሶምሶን ስለሁለቱ ዓይኖቹ እግዚአብሔርን ሲለምን እግዚአብሔር ወደ ሁለቱ የፍልስጥኤም መሰብሰቢያ አዳራሽ ምሰሶች አስጠጋው። የሶምሶንን ሁለት ዓይኖቹን እንዳወጡበት የቤቱን ሁለቱን ዓይኖች (ሁለቱ ምሰሶች) እግዚአብሔር አመለከተው። ሶምሶን በዚህ ቤት ውስጥ ሁለት ምሰሶ መኖሩን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ምሰሶቹስ ቢነቀሉ ቤቱ ፈጽሞውኑ እንደሚፈርስ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ሁለቱ



ምሰሶዎችስ (እንደ ሁለት ዓይኖች) ጎን ለጎን እንዴት ሊቆሙና ቤቱን ሊደግፉ ቻሉ?

ሁለቱን ምሰሶዎችን ስፍራቸውን ማወቅ ተገቢ ነው። እያንዳንዱን ፍልስጥኤም ከመግደል ሁለቱን ምሰሶች መደርመስና እዚያው መግደል ታላቅ ጥበብና ችሎታ ነበር። ረጅም ጠጉር በነበረበት ጊዜያት ይህን አላደረገም ዛሬ ግን በአጭሩም ጠጉር ቢሆን ይህ ይሆን ዘንድ ጸጋው አገዘው። በጥቂቱ በበቀለ ጠጉር ይህን አይነት ውጤት ካስመዘገበ በሰባቱ ጉንጉን ጠጉሩ ብዙ ይሠራ ነበር። ሶምሶን የሁለቱን ምሰሶዎች ስፍራ እንዳወቀ ሁሉ ክርስቲያንም የጠላትን መንደር ምሰሶ ማፍረስ ይገባዋል። ሶምሶን እግዚአብሔርን አስበኝ ብሎ ከመጣራቱ በፊት ባገኘው አጋጣሚ ሁለቱን ምሰሶች ስፍራ አግኝቶአል። ከንቱ ጩኸት ሳይሆን ምሰሶቹን በሁለት እጅ ይዞ እግዚአብሔርን መጥራት ተገቢ ይሆናል።

ትልቅ ጸጋ ተሸክሞ እንደልብ ከመኖር ይልቅ ባለችን የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል እምነት እስከ ሞት ድረስ መታመን ይበልጣል። ሶምሶን በትልቁ ጠጉሩ የሚረባም የማይረባም ሥራ እንደሰራበት ይታወቃል። ከማይረባ ሥራዎቹ መካከል ደሊላ በሸነገለችበት ዘመናት በጠጉሩ ይጠቀምበት የነበረ ጨዋታ ነበር። ያንን መነቃቀለ። አዲስ ገመድ በጣጥሶ መንቃት የዚህ ሁሉ ውጤት የሌለው የጸጋ አሰራር ነበር። ጠጉሩ ከበቀለ በኋላ ግን ውጤታማ ሥራ ሠራ፤ ለመሞት ቆረጠ። "በሞቱም የገደላቸው ሙታን በሕይወት ሳለ ከገደላቸው በዙ።" (መሳ. 16፡30) ጌታ ኢየሱስም

ይህን አስመልክቶ ብዙ አስተምሮአል። "ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፉታልና፡" (ማር. 8፡35)

እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ በወጉ እንጠቀምበት። ሶምሶን ለብዙ ከንቱ ነገሮች ይጫወትበት እንደ ነበረ እኛም ጸጋው በላያችን ካለ እንደ ሶምሶን እየቀለድንበት ሊሆን ይችላል። በመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መቀለድ በመጨረሻ ዓይን ተጎልጉሎ፣ ጸጋችን በፍልስጥኤም መንደር ሊያስገባ፣ ከሥራ ሁሉ መጨረሻ ወፍጮ ፈጪዎች ያደርገናል። ሶምሶንን የሚያህል የመኳንንትና የመሣፍንት መንፈስ የተሸከመ ታላቅ ሰው ወፍጮ ፈጪ ሆነ። በእስራኤል አምላክ ፊት ዝቅተኛ ሥራ ወፍጮ መፍጨት ነው። "በዙፋኑ ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኩር ጀምሮ በወፍጮ እግር እስካለችው እስከ ባሪያይቱ በኩር ድረስ፡ ...።" (ዘጸአ. 11፡5) ከንግሥና የባርነት ሥራን ሠራ። የጌታን ጸጋ ስንቀበል በታላቅ ፍርሃትና ትህትና ሊሆን ይገባል አለበለዚያ ያጠፋናል ይህን የሚያህል ጸጋ ተሸክሞ ጥንቃቄ ከሚጠፋ በሌሎች ሲሠራ አብሮ ማየትና ማገዝ ይመረጣል።

ሶምሶን እንግዲህ የመጀመሪያው የእስራኤል አጥፍቶ ጠፊ ሆነ። ሶምሶን ሁለቱ ዓይኖቹ የጠፉት በተራ ጉጠት በመሆኑ እየቆጠቆጠ ውና እየመገለ፣ እየደማ፣ እየመዘመዘው እንደ ነበር ከልመናው እንረዳለን። እባክህ ስለሁለቱ ዓይኖቼ ይላል። አብረን እንጥፋ በማለት ማለደ። በታላቋ ሰሜን አሜሪካ ላይ የደረሰውን ሁለቱን ታላላቅ ምሰሶዎች አጥፍፊዎች (twines tower) አጥፍቶ ጠፊዎች (ጠጉራቸውን የሚያስረዝሙ) ተጠግተው እንዳወደሙና በዚያው እንደ ጠፉ ሶምሶንም ሁለቱን ምሰሶች ያዘ። ሶምሶን ግን ለጽድቅ ሲሆን



አስከሬኑም ተገኝቶ ተቀበረ የእስራኤልን ታላቅነት በማንኛውም ጊዜ ገለጠ። በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል በዳን ሰፈር በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተነቃቃ ሁሉ እዚያው ሰፈር በአባቱ መካነ መቃብር ጎን ተቀበረ።

በዚሁ አጋጣሚ ስለ ሶምሶን ቤተሰቦችና ዘመዶች ጌታን አከብራለሁ። እነርሱንም አደንቃለሁ። ምክንያቱም ሶምሶን ያን ሁሉ ሕዝብ ሲፈጅ የሦስት ሺህ መኳንንት ቤተሰቦች የሶምሶንን ቤተሰብ ፈልገው እንደሚበቀሉ የታወቀ ነው። እነርሱ ግን የወንድማቸውን አስከሬን ከዚያ ሁሉ መካከል ገብተው አገኙ ወስደውም በሚፈልጉበት ቦታ ቀበሩ።

## 10. ነቢዩ ሳሙኤል

"በየዓመቱም እንዲህ ባደረገ ጊዜ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር በምትወጣበት ጊዜ ታበሳጫት ነበር፤ ሐናም ታለቅስ ነበር፤ አንዳችም አትቀምስም ነበር። ... እርስዋም፦ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ፥ ... ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፥ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ፥ ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም ብላ ስእለት ተሳለች።" (1ኛ. ሳሙ. 1፡7-11)

"ዔሊም እጅግ አረጀ፤ ልጆቹም በእስራኤል ሁሉ ላይ ያደረጉትን ሁሉ፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደ ተኙ ሰማ። ... የእግዚአብሔርም ሰው ወደ ዔሊ መጥቶ ... እንድትወፍሩም የሕዝቤን የእስራኤልን ቁርባን ሁሉ መጀመሪያ በመብላታችሁ ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርህ? ... እነሆ፥ ለቤትህ ሽማግሌ እንዳይገኝ፥ ክንድህን የአባትህንም ቤት ክንድ የምሰብርበት ዘመን ይመጣል።" (1ሳሙ. 2፡22-31)

"ብላቴናውም ሳሙኤል በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፤ በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይገለጥም ነበር።" (1ሳሙ. 3፡1)

የዔሊ ዘመን ወደማለቂያው ሲቃረብ ኃጢአት በእስራኤልና በካህናት ዘንድ እጅግ ተንሰራፍቶ ይኖር ነበር። የካህኑ የዔሊ ልጆች በምንዝር ሕይወት ከመታሰራቸውም በላይ በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉትንም ሴቶች ጭምር እንደ ተኙ ተገለጠ። የአባታቸውንም ምክር የሚንቁ እየሆኑ እያለ አባታቸው ከእግዚአብሔር ይልቅ እነዚህን ልጆቹን አከበረ። የእግዚአብሔርን



ቁርባን አስቀድመው በልተው ከወፈሩ በኋላ ለጌታ ያቀርባሉ። የእግዚአብሔርን ቁጣ በእስራኤልና በዔሊ ፊት በመንደዱ በአንድ ቀን ውስጥ ሁለቱ የዔሊ ልጆች በጦር ሜዳ ተገደሉ፣ ዔሊ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት ተማረከ፣ እስራኤል ዘንድ ኢካቦድ ሆነ።

ኃጢአት በቤተ መቅደስ ላይ ሲነግስ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃልና ራእይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይታገዳል። ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ስለሚሆን ይህ ከሌለ ምንም አይነት ሰማያዊ በረከት አይመጣም። ቃሉና ራእይ ከሌለ አንድ ሕዝብ መረን የወጣ በመሆኑ ሁሉ በገዛ መንገዱ ያዘነብላል። የዔሊ ልጆች ለዚህ ምሥክር ነበሩ። የካህኑን ልጆች መጽሐፍ ሲገልጣቸው "... ምናምንቴዎች ነበሩ፥ እግዚአብሔርንም አያውቁም ነበር።" (1ኛ ሳሙ. 2፡12) እግዚአብሔርን የማያውቅ አመንዝራ የሆነ የካህን ልጅ ቅጽል ስሙ "ምናምንቴ" ነው። ለሳሙኤል እርአያ ይሆናሉ ተብለው ሲገመት በነዚህ ምናምንቴ ሰዎች ሥፍራ አድጎ ድንቅ ማንነት ይዞ ወጣ። ዛሬም አርአያ የማይኖሩ እንኳ ቢሆኑ መልካም ባሕሪ ይዞ መገለጥን ከሳሙኤል እንማር።

አሁን ያለንበት ዘመን በአብዛኛው ይህ ክስተት ይስተዋላል። የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ከመሆኑም በላይ ራእይ ያላቸው የእግዚአብሔር ሰዎች ከየአደባባዩ የጠፉበት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተለወሰና በቅባት የታሸ የመለኮት ቃል ከሰማይ ባለመለቀቁ በአብዛኛው ሕዝቡ እግዚአብሔርን የማያውቅ ሆኗል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር መገኘት በፍቅር እንደሆነ ሲገልጥ "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ

እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ፡፡" (1ኛ. ቆሮ. 13፡1) የእግዚአብሔር ቃል ከፍቅር መድረክ ስለማይወርድ የሚጮሕ ናስና የሚንሸዋሸው ጸናጽል መሆናችን ነው፡፡ በዔሊ ዘመንም የእግዚአብሔር ቃልና ራእይ ብርቅ ሆኖ ተገኘ፡፡

የሳሙኤል እናት ሐና የምታለቅሰውና መብልን አልበላም የምትልበትን ጊዜያት ስንመለከት በየዓመቱ የእግዚአብሔር መሥዋእት በሚቀርብበት ወቅት ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን በዓል በእንባና በኀዘን ትከድነዋለች መስዋእቱንም እንዳትበላ የምግብ ፍላጎትዋ ይዘጋል፡፡ እግዚአብሔር መስዋዕትን እንዳይቀበል አስቀድመን የጠቀስነው በደል በእግዚአብሔር ጉባኤ ነግሦአል፡፡ በዚህን ጊዜ አገር በሙሉ በደስታና በሆይታ መሥዋዕቱን ሲበላና ሲደሰት አንዲት ሴት ግን በእንባና በኀዘን ተከታ መሥዋዕቱን ሳትበላ በእግዚአብሔርና በካህናቱ ፊት ትቀርባለች፡፡ እግዚአብሔርም የካህኑን ቤት ለማፍረስ ከሰማይ ሰይፍ እየሳለ ባለበት ወቅት ካህኑ ይህችን ሴት እንደ ሰካራም ቆጠራት፡፡ ሳሙኤል የሚወለድበት ማኅፀን ከዚህ ከረከሰ መሥዋእት እንዳይካፈል አስቀድሞ እግዚአብሔር የሐናን የምግብ ፍላጎት በመሥዋዕቱ ፊት ዘጋው፡፡ የእግዚአብሔር ልብ በዚህን ጊዜ ከሰማይ በኀዘን ያለቅሳል፡፡ የዚህ እንባ መገለጫ የነበረች የሳሙኤል እናት ብቻ ነበረች፡፡ እግዚአብሔር ያዝናል እርስዋም ታዝናለች፤ ታለቅሳለች፡፡ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን አልተቀበለውም ሐናም መሥዋዕቱን አልበላችም፡፡ ይህ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ግብዣ ሲጋብዙህ ምክንያቱ ከምን እንደሆነ ሳይገባህ ጥሩው ምግብ አልበላህካለ የጤና ችግር ሳይሆን



በመንፈሳዊው ዓለም የጋባዦቹን ግብዣ የተፀየፈው ሊሆን ስለሚችል ከራስ ጋር መታገል አይገባም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን መሥዋዕት አይቀበልም፡፡ ይህም በመሥዋዕቱ ላይ ኀዘንና ቃል ኪዳን የፈረሰ እንደሆነ ነው፡፡ በነቢዩ በሚልኪያስም ዘመን ይህ ነበር፡፡ "... እግዚአብሔር ቁርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት፥ ከእጃችሁም በደስታ እንዳይቀበለው መሠዊያውን በእንባና በለቅሶ በኀዘንም ትከድናላችሁ፡፡ እናንተም፥ ስለ ምንድር ነው? ብላችኋል፡፡ ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታልለሃታልና ...፡፡" (ሚል. 2፡13-14) በዔሊ ዘመን እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ቃል ኪዳን ትታለች፡፡ መስዋዕቱ ላይ ኀዘንና ዕንባ አለ፡፡

እግዚአብሔር ሰው ባጣበት ጊዜ ከሐና ማኅፀን የሚወለደውን ኤፍሬማዊውን ሳሙኤልን ይጠብቃል፡፡ የሌዊ ነገድ ቢጠፋ ከኤፍሬም ነገድ በቤቱ የሚቆም አገኘ፡፡ ሐና የእግዚአብሔር መንፈስ በእርስዋ ስለሚኖር ሳሙኤልን ለማግኘት መራራ ዕንባን በተዘጋ አንደበት በመሠዊያው ዘንድ ታፈስሳለች፡፡ እግዚአብሔር የሐናን ዕንባ ስለናፈቀ ሳሙኤል በዕንባ የተወለደ ይሆን ዘንድ ፈለገ፡፡ አገር በጨለመበት ጊዜ የሃና ዕንባ ይህን እንዲከፍት አስቀድሞ ማኅፀንዋን ዘጋ፡፡ ከዚህች ሴት የሚገኘውን ልጅ በእግዚአብሔር መቅደስ መብራትን የሚያበራ ይሆን ዘንድ ወሰነ፡፡ ዔሊም ባያውቅ፣ ሕልቃናም ባይገባው እግዚአብሔር የሚያውቀው ህፃኑ ሳሙኤል ሊፀነስ ተቃረበ፡፡

እግዚአብሔር ለሐና ልጅ የሚሰጣት ከፍናና ጋር ስላላት ቁርሾ ለመበቀል አስቦ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ለሐና ልጅ የሚሰጣት

ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አገልግሎት እንዲውል ነው። ሐና በመጨረሻ አንድ ስዕለት ተሳለች ልጅ ከሰጠኸኝ ለአንተ እሰጣለሁ አለች። የምትሰጠውም የተወሰነ አገልግሎት እንዲያገለግል ሳይሆን ዕድሜውን በሙሉ ለጌታ አገልግሎት እንዲውል ነበር። ይህን ዔሊ ባያውቅ እግዚአብሔር ቤቱ ለዘላለም እንዳይዘጋ መብራቱም እንዳይጠፋ ይህን አደረገ።

ሐና ለዚህ ስዕለት ምልክት የሚሆን አንድ ነገር ተናገረች የልጁ ራስ ላይ ምላጭ አያርፍም። ከተወለደ ጀምሮ ጸጋው የተስተካከለ ይሆን ዘንድ ከልጅነት እስከ ሽምግልና ጠጉሩ ምላጭ አይነካውም። እንደ ሶምሶን ዘወትር የሚያድግ ጸጋ ይኖረው ዘንድ በስዕለት ተማፀነች። አንድ ወንድ ልጅ ብትወልድ ለጌታ ለመስጠት ይህ የማርያም ዓይነት ሕይወት ነው። ማርያም የበኩር ልጇን ወልዳ ለእግዚአብሔር እንደ ሰጠች ይህችም ይህን አደረገች። ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ሁሉ ከማኅፀን ጀምሮ የተለየ፣ በራሱ ላይ ያለው ጠጉር ምላጭ የማይደርስበት ሁልጊዜ የሚያድግ ጸጋ ሊሆን ይገባዋል።

በእግዚአብሔር ቤት አንድ ወንድ የሚያገለግልበት ዕድሜ ከ20 ዓመት በላይ ነው። ሳሙኤል ግን ገና ብላቴና ሳለ በጌታ መቅደስ ይገኝ ነበር፤ ጌታን ያገለግል ነበር። ጠጉሩ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የበቀለ በመሆኑ በብላቴንነቱም ቢያገለግል ሕጉን አይቃወምም። በእግዚአብሔር መሠዊያ ላይ ከማዘበት ብላቴናውን ሳሙኤልን አቁሞ በእግዚአብሔር ፍርሃት መኖር እንዴት ማስተዋል ነው። ለሁሉ ጊዜ አለው። እግዚአብሔር የተከለው ተክል በወጉ ካላደገና ለፍሬ የማይበቃ ከሆነ የሚነቀልበት ጊዜ ይመጣል። "... እነሆ፡



ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም፡ ቍረጣት፤ ስለምን ደግሞ መሬቱን ታጐሳቍላለች? አለው። እርሱ ግን መልሶ፡ ጌታ ሆይ፡ ዙሪያዋን እስክከኵተኵትላትና ፋንድያ እስክፈስላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት። ወደ ፊትም ብታፈራ፡ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን ትቈርጣታለህ አለው።" (ሉቃ. 13፡7-9) በዚህ አሳብ መሠረት በለስ ከበቀለች በኋላ ለሦስትና አራት አመት ብቻ ትጠበቃለች አለበለዚያ ትነቀላለች። መሬቱ እንዳይጎሳቆል ትነቀላለች። በሳሙኤልም ዘመን ሁሉ ተነቀሉ ብላቴናው ሳሙኤል ብቻ በእናቱ እንባ በቀለ ለእስራኤልም ደጅ ከፋች ሆነ። በእንባ የተወለደ ልጅ እርሱም በእንባና በልቅሶ የተሞላን ጸሎት ተምሮ አደገ።

እንደ ሳሙኤል ጌታን ያገለገለና እግዚአብሔር የተወደዱ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳ በጣም ጥቂቶች ናቸው። አልፋና ኦሜጋ የሆነ አገልግሎትና ኑሮ የኖረ፣ ሳዖልን የሾመና የሻረ፣ ዳዊትን የቀባ፣ ለእስራኤል በወጉ የፈረደና ያስተዳደረ በመሣፍንቶችና በነገሥታት ድንቅ ዘመን መካከል (The transition governer of the transition government between princes of Israel & kings of Israel) የገባ የጌታ በረከት ነው። በምዕራፍ 12 ላይ ሳሙኤል ሲሸመግል ስለ ኑሮው፣ አገልግሎቱና ዳኝነቱ ራሱን በአደባባይ በእግዚአብሔርና በቀባው ፊት መረመረ። ይህ ሁሉ ሆኖ የሕዝቡ መልስ "... አልሸነገልኸንም፡ ግፍም አላደረግህብንም፡ ከሰውም እጅ ምንም አልወሰድህም አሉ።" (1ሳሙ. 12፡4) የሳሙኤል ቃል ለእስራኤል እንደ ደረሰና ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ የተገለጠ ነቢይ መሆኑ በ1ኛ

ሳሙኤል ምዕራፍ 1 ተገልጧል። የአንዳንዱ አገልጋይ ቃል በአንድ ምኩራብ፣ የእምነት ክልል (denomination)፣ በአንድ ግዛት ወይንም ዘመን ብቻ ይሰማል የሳሙኤል ግን ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ለዘመናት የተሰማ የጌታ ነቢይ ነበር በሞተ ጊዜ እንኳ አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ከሮቤል እስከ ቢኒያም ሁሉ እርሱ ደጅ ተሰብስበው በአራማቴም አልቅሰው ቀበሩት። የሳሙኤል ጸጋ ባለበት ስፍራ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ምህዳር የሰፋ ሲሆን በተለይ ነቢያትን ሰብስቦ በነወተዘረማ ትምህርት ሲሰጥ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ትንቢት ይናገሩ ነበር።

ዳዊት በወጣትነት ዘመኑ ከሳዖል ዘንድ ችግር ሲደርስበት ሮጦ የሚያማክረው ያሳደገው ሳሙኤል ነበር። የሳሙኤል ጸሎት ደግሞ ሌሊቱን ሁሉ በለቅሶና ጩኸት የታከለበት ነበር። ወደ አንዱት የእስራኤል መንደር ሲንቀሳቀስ የደረሰበት ከተማ ሁሉ ሳሙኤል ለምንድር ነው ወደ እኛ የመጣህ በማለት ይንቀጠቀጡ ነበር። በአጠቃላይ ጠጉሩ ምላጭ ሳይነካው እንዳደገ ሁሉ ጸጋው ከቤት ወጥቶ በሚያገለግልበት ምኩራብ ብሎም ለእስራኤል ለዓለም ሁሉ የደረሰ ነበር። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሕዝቦች የልጆቻቸውን ስም ሲያወጡ ወንድ ከሆነ ሳሙኤል ሴት ከሆነች ሐና ለማለት በተለይ በክርስቲያኑና በአይሁዱ ዕጣ ውስጥ በመግባት ቀዳሚ እንደሆነ አገምታለሁ።



# 11. ነቢዩ ኤልያስና ነቢዩ ኤልሳዕ

## 11.1. ነቢዩ ኤልያስ

"እርሱም፡ ሊገናኛችሁ የወጣው፡ ይህንስ ቃል የነገራችሁ ሰው መልኩ ምን ይመስላል? አላቸው። እነርሱም፡ ሰውየው ጠጉራም ነው፡ በወገቡም ጠፍር ታጥቆ ነበር አሉት። እርሱም፡ ቴስብያዊው ኤልያስ ነው አለ። ንጉሡም የአምሳ አለቃውን ከአምሳ ሰዎች ጋር ሰደደ፤ ወደ እርሱም ወጣ፡ እነሆም፡ በተራራ ራስ ላይ ተቀምጦ ነበር።" (2ኛ ነገሥ. 1፡7-9)

ንጉሥ አካዝያስ ከዓይኑ ርግቡ ወድቆ በመታመሙ መልእክተኞቹን ወደ አቃሮን አምላክ ወደ ሆነው ወደ ብኤልዜቡል ላካቸው። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር በኤልያስ አማካኝነት መልእክተኞቹን ተገናኘ። የተገናኘበትም ዓላማ የንጉሡን መልዕክት በመስበር ነው። ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር ታላቁ ነቢይ ኤልያስ በነበረበት ወቅት ይህ ንጉሥ ብኤልዜቡልን መጠየቁ ታላቅ ሀፍረት ነበር። በተራራ የሚኖረው ነቢዩ ኤልያስም የንጉሡን ቃል ይሽር ዘንድ ተገለጠ። ኤልያስ በንጉሡ መልእክተኛ አይታወቅም። እጅግ የሚደንቀው ግን የኤልያስ ማንነት ሳይታወቅ መልእክተኞቹ ከመንገድ ወደ ኋላቸው ተመለሱ። በኤልያስ ቃል የንጉሡን ትእዛዝ ሻሩና ተመለሱ። በኤልያስ የነበረ ጸጋ ማንነቱ ባይታወቅም በሥራ ግን ይታወቃል። ከኤልያስ በሚነገር ቃል መልእክተኞቹን ከመንገድ መለሰ።

መልእክተኞቹ ወደ ኋላ ተመልሰው ለንጉሡ የኤልያስን ቃል ሲነግሩት ንጉሡ ለምን ተመለሳችሁ አላቸውም ይልቅም ይህን

መልእክት በመንገድ የነገራችሁ ሰው መልክ ምን ይመስላል በማለት ጠየቀ:: የነዚህ መልእክተኞችን ትኩረት የሳበው የኤልያስ ቁመት፣ ዓይነ፣ ንግግር ወይንም ሌላ ሳይሆን ጠጕሩና በወገቡ የታጠቀው ጠፍር ነበር:: እንግዲህ የኤልያስ ማንነትና መልክ ትኩረትን የሚስበው አስቀድሞ ጠጕሩ ነው:: ሰውዬው ጠጕራም ነው የሚል ቃል ለንጉሡ ሲነገረው ወዲያው ቴስቢያዊው ኤልያስ መሆኑን ተረዳ::

ንጉሡ አካዝያስ ኤልያስን የሚያህል ታላቅ ነቢይ በነበረበት ወቅት እየኖረ ሳለ ከኤልያስ ይልቅ ብአልዜቡልን መረጠ:: ነገሥታት በነቢያት ከመጠቀም ይልቅ ከኢጋንንት ጋር መወዳጀትን በአብዛኛው ይመርጣሉ:: በተራራ የሚኖረውና ፍጹም ልዩ ቅባት ያለው ኤልያስ በሚኖርበት ዘመን የእስራኤል ገዢ የሆነው አካዝያስ ወደ ጣኦታት ራሱን አዘነበለ:: ኤልያስን ባያውቀው እንኳ ምናልባት መፍትሄ ፍለጋ በመሄዱ ነገሩ ይቀልለት ነበር ነገር ግን ኤልያስን እያወቀው ይህን አስከፊ በደል ፈጸመ::

በሰማርያ የሚኖረው አካዝያስ ብኤልዜቡልን ከማምለክና የኤልያስን ጸጋ ከማግፋፋት በላይ ታላቅ በደልን ይጨምር ዘንድ ተዘጋጀ:: አምሳ አለቃና አምሳ ሰዎች የሚመራ ሠራዊት ኤልያስን አውርደው በሽተኛው ንጉሥ ዘንድ እንዲያመጡት ላከ:: ከዓይን እርግቡ የወደቀና የታመመ ንጉሥ በብኤልዜቡል የሚመካ ሰው በተራራ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን ነቢይ ለመቅጣት ሞከረ:: ኤልያስም በእግዚአብሔር ስም በመርገም የመጀመሪያውን ቡድን በሰማይ እሳት ፈጃቸው:: የንጉሡ ደካማነት አሁንም አየለ:: ሁለተኛና ሦስተኛ ተመሣሣይ ሠራዊት አከታትሎ ላከ:: ሁለቱ ሠራዊቶች



ሲያልቁ ሦስተኛው ተማጸነ:: ኤልያስ በመልአኩ ቃል ወደ አካዝያስ ወረደ አስቀድሞ የተናገረውን ደገመው:: "ኤልያስም እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ሞተ::" (2ኛ ነገሥ. 1፥17)

ነቢዩ ኤልያስ ጠጕሩን ያሳድግ ዘንድ ከጌታ ሆነለት:: የነቢዩ መለያው የጠጉሩ ርዝመት ሆነ:: መጥምቁ ዮሐንስ በኤልያስ መንፈስ የተገለጠ ነቢይ ነበር:: ጌታ ኢየሱስን ያስተዋወቀው በኤልያስ መንፈስ በመገለጥ ሲሆን የጠጉሩም ሁኔታ ከኤልያስ ጋር ይቀራረባል:: ኤልያስ ብቻውን በኮራት ፈፋ እንደኖረ ዮሐንስም በምድረ በዳ ኖረ:: ኤልያስ የእስራኤልን ሕዝብ አምልኮ አቅጣጫ አስያዘ፣ ዮሐንስም ሁሉን ወደ ጌታ አምላክ ልባቸውን አቀና:: ኤልያስ በአክአብ ሚስት በኤልዛቤል ሰይፍ በላዩ ሊያልፍ ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስም በሄሮድስ ሚስት በሄሮዳይዳ ምክንያት ጭንቅላቱ ተቆረጠ:: ኤልያስም ሆነ ዮሐንስ ነገሥታትን በመገሠፅ ይታወቁ ነበር:: "ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ ልትቀበሉትስ ብትወዱ፥ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው::" (ማቴ. 11፥13)

ደቀ መዛሙርት ስለ ኤልያስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ፈሪሳውያን የሚሉትን ቃል ይዘው ለኢየሱስ አቀረቡ:: "ደቀ መዛሙርቱም፦ እንግዲህ ጻፎች፥ ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት:: ኢየሱስም መለሰ፥ ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል፥ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፥ የወደዱትንም ሁሉ

አደረጉበት እንጂ አላወቁትም፡ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው።" (ማቴ. 17፥10-12)

ፈሪሳዊያን ማለት የሚያምኑትን፣ ተስፋ የሚያደርጉትንና የሚወድዱትን ማወቅ አስቸጋሪ ነው። በየምኩራቦቻቸው ሁልጊዜ የሚሰብኩት ታላቁ ነቢያችን ኤልያስ ዳግመኛ ይመጣልናል ሁሉንም ያቀናል በማለት ሥራቸው ተገታትሮ ይናገራሉ ይሰብካሉ። በእርግጥም ትክክለኛ ስብከትና አስተምህሮት ነው። ኤልያስ ራሱ ሳይሆን መጥምቁ ዮሐንስ በቀጥታ በኤልያስ መንፈስና ኃይል መጣ። በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ማንነት እንኳ በጣም ተቀራራቢ ሆኖ መጣ። በዚህን ጊዜ ይኸው፡ ያልነው ነቢያችን መጣ ሁሉን ወደ ጌታ አምላካችን ያቀናልናል ብለው ይቀበሉታል ተብሎ ሲጠበቅ የወደዱትን አደረጉበት። የወደዱትን ካደረጉ በኋላም እንኳ ኤልያስ ይመጣል ሁሉን ያቀናል የሚልን ስብከት ይዘው በየምኩራቦቻቸው ይሰብካሉ። መሲህ ደግሞ ይመጣል ነጻ ያወጣናል የሚለው ስብከት ደግሞ ግር ቅጠሉ ከማወቁም በተጨማሪ የፕሮግራማቸው መክፈቻና መዝጊያ ነበር። ይህ መሲህ ሲመጣ ደግሞ የወደዱትን ከማድረግ በላይ ነፍስ ገዳይ በርባንን ከክርስቶስ በላይ ይሻለናል በማለት ከወይን አትክልት ውጭ ጣሉት። ዛሬም በየመድረኩ የሚሰበኩ ቁም ነገሮች ሳይሆን ወሳኙ የሚሰበኩት ነገሮች በገሃዱ ዓለም ተገልጠው ሲመጡ መልሰን እንዳንሰቅላቸው መጠንቀቅ ይበጃል። ክርስቶስ የተወለደው ተስፋይቱ ከተማ ሲሆን የተሰቀለው ጠላት አገር ሳይሆን ወዳጅ አገር በሙሉ ዐሐይ፣ በተራራ በመሆኑ እኛም ታሪክን እንዳንደግም የምንጠብቀውን ጠጉራም ሰው እንወቅ። ዛሬም ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል፣ በዓለምና በሰው ሁሉ ሊፈርድ የተመደበው እርሱ ነው



በማለት እየሰበክን ሲመጣ ግን ከጉዳዩ ተለይተን እንዳንገኝ ከቃሉና ከማንነቱ በቅርብ ርቀት ብንገኝ የተሻለ ነው።

"ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ።" (ማቴ. 3፥4) ዮሐንስ በግመል ጠጉር ማንነቱን ሲሸፍን ከሴቶች ከተወለዱት መካከል እንደ እርሱ ያለ ያልተነሣ ሰው ነበር።

ታላላቅ ነቢያት የተባሉት ኤልያስና መጥምቁ ዮሐንስ ራሳቸውን የገለጡት በጠጉር ከሆነ የዚህም ዘመን ነቢያት መንፈሳዊ ጠጉር ተላብሰው ወገባቸውን ጠፍርም ታጥቀው ማገልገል ይገባቸዋል። ከዓለም የተገኘ ልብስ ሳይሆን በተፈጥሮ የተገኘ የጠጉር ልብስ ያስፈልጋል። በአብዛኛው ራስ በራ፣ ያለመታጠቂያ የተንጠለጠሉ ልብሶች የተቀደደና የተጣጣፈ ጸጋ በክርስትናው ዓለም እየተገለጠ እንደ ሆነ በመንፈስና በትንቢት መስማት ከጀመርን ዘመን ተቆጥሯል።

## 11.2. ነቢዩ ኤልሳዕ

"ከዚያም ወደ ቤቴል ወጣ፡ በመንገድም ሲወጣ ብላቴኖች ከከተማይቱ ወጥተው፡ አንተ መላጣ፡ ውጣ፤ አንተ መላጣ፡ ውጣ፤ ብለው አፌዙበት። ዘወርም ብሎ አያቸው፡ በእግዚአብሔርም ስም ረገማቸው፡ ከዱርም ሁለት ድቦች ወጥተው ከብላቴኖች አርባ ሁለቱን ሰባበሩአቸው። ከዚያም ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሄደ ...።" (2ኛ ነገሥ. 2፥23-25)

የነቢዩ ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር የመጨረሻውን ስንብት በሚያደርግበት ጊዜ በአራት ከተሞች አብረው ተጉዘዋል። ጌልገላ፣

ቤቴል፣ ኢያሪኮና የዮርዳኖስ ማዶ ናቸው። ከኤልያስ የወደቀውን መጎናጸፊያ በማንሳት ከዮርዳኖስ ወደ ኢያሪኮ ተመለሰ። ከኢያሪኮም ወደ ቤቴል ተጓዘ።

ነቢዩ ኤልሳዕ የመጀመሪያ አስደናቂ ተዓምራት ያደረገው የዮርዳኖስን ወንዝ ሲከፍል ነበር። አንድ ጨርቅ በመጠቅለል ይህን ወንዝ መክፈሉ አስደናቂ ነው። የእስራኤል ማኅበረሰብ ወደ ተስፋይቱ ምድር በኢያሱ አማካኝነት ሲገቡ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ነበር። በኢያሱ ዘመን ዮርዳኖስ የተከፈለው ካህናት ታቦት ተሸክመው እግራቸውን ወደ ውኃ ባጠለቁበት ወቅት ነበር። በኤልሳዕ ዘመን ግን በጨርቅ ሲሆን ይኸውም አንድ ሰው ይሻገርበት ዘንድ ነበር።

የኤልሳዕ ሁለተኛው ተዓምራት በኢያሪኮ ከተማ የሚገኘውን የውኃ ማከማቻ መፍትሄ በመስጠት ሲሆን የኢያሪኮ ከተማ ኑሮው መልካም ውኃው ግን የምድሪቱን ፍሬ ያስጨንግፍ ነበር። የኢያሪኮ ከተማ ላይ ያለውን ታላቅ መርገም ለማንሳት ይህ ነቢይ ተገለጠ። በኢያሱ ዘመን የተረገመች ከተማ ላይ ቆሞ መርገምን በማንሳት በእርግጥም ታላቅ መንፈሳዊ ጉልበትና ጸጋ ተጠቀመ። የዚህ ከተማ ሰዎች ለኤልሳዕ ታላቅ አክብሮትን ሰጡት። "ጌታችን ሆይ" በማለት ነበር። ኤልሳዕም የጠየቃቸው አዲስ ማሰሮና ጨው ብቻ ነበር። ከራሳቸው ጉያ በወጣ ነገር የራሳቸውን ችግር መፍትሄ ሰጣቸው። ወደ ምንጩ በመሄድ የጭንገፋን ሥር አደረቀ ከዚያን ቀን ጀምሮ ውኃው ተፈወሰ።

የኢያሪኮን ሕዝብ ችግር ካቃለለ በኋላ በመቀጠልም ወደ ቤቴል ተጓዘ። ቤቴል የእግዚአብሔር መሰላል ተዘርግቶ ሰማይና ምድር



የተገናኙበት ስፍራ መሆኑ ይታወቃል። በያዕቆብ አማካኝነት ሁሉ የተስተካከለበት ሥፍራ ነው። "... ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ፣ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፣ ይህም የሰማይ ደጅ ነው።" (ዘፍጥ. 28፡17) እንግዲህ በዚህ ከተማ ነበር ነቢዩ ኤልሳዕ የተፌዘበት። በዚህ ከተማ ሌላ ተዓምር ይሠራል ተብሎ ሲጠበቅ የከተማ ሕፃናት አፌዙበት። ታላቅ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተሸክሞ በመጣበት ቦታ የክፋት መንፈሳዊ ሠራዊቶች ሕፃናትን ተጠቅመው አፌዙ።

በነቢዩ ኤልሳዕ አገልግሎት ሌላ ነቢይ ተሰድቧል። የኤልሳዕ አገልጋይ የነበረ ነቢይ ኢዩን ለመቀባት የዘይት ማሰሮ ተሸክሞ ኢዩን ከሸማግሌዎች ተርታ አስነስቶ በጓዳ በቀባው ጊዜ ይህ ነቢይ ተሰደበ። በዚህን ጊዜ ኤልሳዕ ያከናውን የነበረው ተዓምራት ኢዩን መቀባት ሲሆን ኢዩም የጋለሞታዎች እናት የሆነችውን ኤልዛቤልን የምትገደልበትን ትእዛዝ በወጣበት ጊዜ ነበር። በዚህን ወቅት የአጋንንት መንጋ በኢዩ ቅባት ፍፁም ጥቃት ስለሚገጥማቸው በሽማግሌዎች አንደበት ተጠቅሞ የጌታን ነቢይ ሰደቡ። "ኢዩም ወደ ጌታው ባሪያዎች ወጣ፣ እነርሱም፦ ደኅና ነውን? ይህ እብድ ለምን መጣብህ? አሉት።" (2ኛ ነገሥ. 9፡11) የእብደት መንፈስ የተጠናወታትን ኤልዛቤልን የሚገድል ዘይት በኢዩ ራስ ሲንጠባጠብ የኤልሳዕ አገልጋይና ነቢይ እብድ ተባለ። አዋቂ ናቸው በተባሉ አዛውንቶች ማኅበር የጌታን ነቢይ እብድ በማለት አፌዙበት።

በቤቴል ኤልሳዕን የጠበቀው በሕፃናት የተጠቀመ የክፋት ሠራዊቶች ናቸው። የኢያሪኮን ከተማ እርግማን በመሻሩ የተቃጠሉ

መናፍስት በቤቴል ቀደሙት። በውኃ አካል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ይሰፍፋል። በኢያሪኮ ግን ውኃው የምድራቱን ፍሬ ያስጨነግፋል። በመሆኑም ታላቅ መንፈሳዊ ጸጋን በመጠቀም ኤልሳዕ ይህን እርግማን ሰበረ። በዚህም የውጊያው አውድማ ጠበቀው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጌርጌሲኖን ከተማ የነበረውን የአጋንንት ግብረ ኃይል ከአንድና ከሁለት እብዶች ሲያወጣ እየተጣደፉ ወደ ባህር ሰጠሙ። በዚህን ጊዜ የጌርጌሲኖን ነዋሪዎች ወደ ኢየሱስ ቀርበው ከከተማቸው እንዲወጣ ጠየቁት። ለእሪያቸው ሲሉ የዓለምን መድኃኒት ከከተማቸው አስወጡት። ጌታም የሕዝቡን ደካማነት ተገንዝቦ ለዚህ ሕዝብ ሰባኪ አዘጋጀላቸው። ሰባኪውም እብድ የነበረው የተፈወሰው ሰው ነው። ሕዝቡ ከእብድ አነሰ ማለት እኮ ነው!

ኤልሳዕ የተፌዘበት ከአርባ ሁለት በላይ በሆኑ ብላቴኖች ነበር። "ኤልሳዕም ሲረግማቸው ከዱርም ወጥተው ከብላቴኖች አርባ ሁለቱን ሰባበሩአቸው።" ይህ ማለት የቤቴል ብላቴኖች በአብዛኛው ለዚህ ክፉ ተግባር ለመሰማራት ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ። በኢያሪኮ ከነበረው እርግማን ይልቅ የቤቴሉ የከፋ ነበር። በኢያሪኮ በውኃ አካል ላይ የነበረ እርግማን ሲሆን በቤቴል ግን በብላቴኖች ያለ የተሳዳቢነት መንፈስ ነው። አዛውንት ላይ የሚያፌዙ፣ በጌታ ነቢያት የሚያላግጡ፣ በኅብረት በመሆን አንድ አይነት ስድብን ለመናገር ታላቅ አንደበት የነበራቸው ብላቴኖች ነበሩ። በታዳጊ ሕፃናት ላይ የክፉት ኃይላት በዚህ መልክ ከተሰማሩ የቤቴል ከተማ የሚረከቡ በመሆናቸው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉ በዚህ የተለከፈ ከመሆኑ በላይ ከተማይቱ ራስዋን የማያታት መቅደስ ታደርጋለች።



ነቢዩ ኤልሳዕ የተፌዘበት በጠጉሩ ነው። ራስ በራ በመሆኑ መላጣ መላጣ በማለት አፌዙበት። በጭንቅላቱ ላይ ጠጉር ባለመኖሩ ይህን ተጠቅመው አፌዙበት። ራስ በራነት ደግሞ የሚያሰድብ ነገር አይደለም። የአሪት መጽሐፍ ይህን አስመልክቶ የተለየ ሕግ አለው። "የሰውም ጠጉር ከራሱ ቢመለጥ እርሱ በሀ ነው፤ ነገር ግን ንጹሕ ነው። ጠጉሩም ከግምባሩ ቢመለጥ እርሱ ራስ በራ ነው፤ ነገር ግን ንጹሕ ነው።" (ዘሌዋ. 13፥40-41) በሀ መሆን ወይም ራስ በራ መሆን ምንም ማለት አይደለም የብሉይ ኪዳን ሕግ ንጹሕ እንደ ሆነ ይመሰክራል የቤቴል ብላቴኖች ግን የሚሳደቡበትንና የሚያፌዙበትን እንኳ ለይተው የማያውቁ ነበሩ። ንጹሑን ለመስደብ ራሳቸውን አዘጋጁ።

ነቢዩ ኤልያስ ጠጉራም ሲሆን ኤልሳዕ ደግሞ ራስ በራ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነቢዩ ኤልሳዕ መንፈሳዊ ሕይወቱ የጀመረው እርፍ ይዞ ከነበረበት ከማሳ ላይ ነበር እንደነ ሳሙኤልና፣ ሶምሶን ከልጅነት ጀምሮ ለጌታ የተለየ አልነበረም።

ነቢዩ ኤልሳዕ ለቤቴል ይዞ የመጣውን በረከት ብላቴኖችን በመርገም ቀየረ። በረከትና ሰይፍ ተሸክሞ የመጣ ነቢይ ለዚህች ከተማ ሰይፍ ተመዘዘ። ድቦች እንኳ የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? አንድ ድብ ሃያ አንድ ሰው ለመሰባበር ከቻለ ደካማ የሆነ የሰው ልጅ በጌታ ነቢያት ላይ አፉን ሲከፍት እንዴት አይፈራም? ለዚስ አይደል በነቢያቱ ላይ ክፉ አትናገሩ በማለት መጽሐፍ በየስፍራው የሚያስጠነቅቀ።

ሰው ከጌታ ጋር አብሮ ከሆነ ሁሉ ፍጥረታት ይታዘዙለታል። ለኤልሳዕ ድቦች ሲታዘዙ ለሶምሶን ደግሞ ቀበሮዎች ታዘዙለት።

ኤልሳዕ ላይ ሰው ከሚያፈዝበት አርባ ሁለት ብላቴኖች በድብ ቢሰባበሩ ይቀላል። በጌታ ነቢያት ያለ ጸጋ እጅግ የሚያስፈራና ሁሉ ሊያከብሩት የተገባ ነው።

ኤልሳዕ እነዚህን ብላቴች ከረገመ በኋላ መኖሪያው የከፍታ ስፍራ ሆነ። የእርግማን ቃል ካወጣና ከተሰባበሩ በኋላ በቀጥታ ያመራው ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ነበር። የፌዘኞችን ጉልበት ከሰበረ በኋላ የከፍታ ሕይወትን ተለማመደ። ቀርሜሎስ ተራራ ነቢዩ ኤልያስ በማምለኩ ተደፍቶ ከሦስት አመት በላይ የተቋጠረውን ዝናብ እንዲዘንብ የጸለየበት ሥፍራ ነው። የበዓል ነቢያትን አንገት አርዶ በቀጥታ ያመራው በቀርሜሎስ ተራራ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ነቢዩ ኤልሳዕ የሚያፌዙትን ብላቴኖች ከሰባበረ በኋላ በቀጥታ ወደ ቀርሜሎስ አቀና። ነቢዩ ኤልያስ ከቀርሜሎስ በቀጥታ ኤልዛቤል ወደ ነበረችበት ኢይዝራኤል (ሰማርያ) አቀና። ኤልሳዕም ከቀርሜሎስ ወደ ሰማርያ ሄደ። ይህ ሁሉ የሚያሳየን የኤልሳዕ እንቅስቃሴ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ የተረጋገጠ ነበር። በዚህ ዘመንም በጌታ ነቢያትና በመቅደስ የሚያፌዙ ብላቴኖች በጌታ ቤት ተበራክተዋል። በአንድ ቃል የፌዝንና ስድብን የሚናገሩበትን መንፈስ ዛሬም ይህን በሚሰብር የጌታ ሥራ በቀርሜሎስ ይወጣል። እኛም የጌታ አገልግሎት አደራ ሲሰጠን ኤልሳዕ እንዳለ ጌታ ሆይ የሚሰድቡንን እንርገም ብለን ብንጠይቅ የጌታ መልስ በአጭሩ ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆናችሁ መርምሩ ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፉትን ለማዳን አይደለም'ን በማለት ተመልሶ እኛኑ ይገስጸናል። የብሉይንና የአዲስ ኪዳንን አሠራር መለየት ይገባናል።



ነቢዩ ኤልሳዕ ያገለገለበት ቅባት የተገኘው ከነቢዩ ኤልያስ ነበር። ኤልያስ ከኤልዛቤል ዛቻ በመሸሽ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ኮሬብ ወጣ። አርባ ቀንና ሌሊትም በመጦም፣ በመጸለይና የተራራ ጉዞ በመጓዝ ኮሬብ አናት ላይ ደረሰ። ኤልያስ የነበረው ኃይል በሙሉ አለቀ። በጦም፣ በጸሎት፣ በተራራ ጉዞ፣ በጌታ ቅንዓት፣ በብቸኝነትና ተስፋ በመቁረጥ እግዚአብሔር ጋር ደረሰ በዚህም ሁሉ ደከመ። ሐዋርያው ጳውሎስ ስደክም ኃይለኛ ነኝ የጌታ ጸጋም ይገለጥብኛል በማለት እንዳስታወቀ ኤልያስም በውስጡ ያለው ኃይል በሙሉ ደከመ። የመጨረሻ የጌታ ጸጋ ያገኘ ዘንድ በሁሉ ደከመ። ሦስት የተለያዩ ቅባት ይዞ ወረደ። ሁለቱ የነገሥታት ሲሆን አንዱ የነቢይ ቅባት ነበር። ከአዛሄልና ከኢዩ የሚያመልጠው በሙሉ በኤልሳዕ ይገደል ዘንድ ነቢዩ ኤልያስ ቅባት ይዞ ተገለጠ።

ኤልሳዕ ከግብርና ሕይወት በመውጣት ወደ ነቢይነት አመራ። ኤልያስ ይዞለት በመጣው ልዩ ቅባት ያገለግል ጀመር። ይህን ለመመልከት ደግሞ በራሳቸው ላይ ያለው ጠጉር ይመሰክራል። ኤልያስ ጠጉራም ነበር ኤልሳዕ ደግሞ ራሰ በራ ነው። ኤልያስ ይዞ በመጣው ጸጋ ኤልሳዕ ተገለገለበት። ኤልያስ ለኤልዛቤል ዛቻ ሲሸሽ ኤልሳዕ ግን በተላላኪ ነቢይ ኢዩን በመቀባት ኤልዛቤልን መግደል ቀላል ነገር ሆነለት።

ኤሳው ጠጉራም ያዕቆብ ደግሞ ለስላሳ ገላ እንደ ነበረው ይታወቃል። ለስላሳ ገላ የነበረው ያዕቆብ በኤሳው ጸጋ ተጠቀመ። ኤሳው ከውጭ አደን ለማግኘት ይጋደላል። ያዕቆብ በቤት በመቅረት ይባረካል። ኤልሳዕም ብዙ ሳይለፋ በኤልያስ ጸጋ በመጠቀም አገለገለ።

ኤልያስ ሦስት ቅባት ከተራራ ይዞ እንደ ወረደ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 19 ይገልጣል። ኤልያስ ምን ያህል ልፋት እንደ ነበረው ሦስቱም ሰዎች አያውቁም። አዛሄል አርባ ግመል የተጫኑ የሶርያ ገጸ በረከት ለኤልሳዕ ከንጉሡ ዘንድ ለማድረስ ግመል ሲጎትት የንግሥናን ቅባት ተቀበለ። ኤልሳዕ በጥማድ በሬዎች ሲያርስ የኤልያስ መጎናጸፊያ በትከሻው ወደቀለት። ኢዩም ከሰዎች ጋር እየተጨዋወተ በድንገት ወደ ጓዳ ተጠርቶ ተቀባ ሦስቱም በድንገት ተቀቡ። ሦስቱም ከሌላ ሥራ ተሳቅቀው የጌታን ሥራ ለመሥራት በድንገት ሆነላቸው። ምንም ሳያስቡት ታላላቅ ጸጋ በእናታቸው ወረደ። ከሁሉ ይልቅ በኤልሳዕ ላይ ፈሰሰ። ኤልሳዕ ይህን ተሸክሞ መለኮታዊ ሥራን ሠራ ይህ ማለት ከልጅነታቸው ጀምሮ ባላሳደጉት ጠጉር ተጠቀሙ። ኤልያስ ያን ሁሉ መከራ አሳለፈ እነርሱ ተጠቀሙበት። የአክዓብን ሚስት የኤልዛቤልን ጉዳይ በወጉ እናጢን። ኤልያስን የሚያህል ታላቅ ነቢይ ማስፈራራት የቻለችና የተሳካላት ኢዩ ግን ከደርብ ላይ እንድትራ ቁሳቁስ ሲወረውራት በውኑ በኢዩ የነበረ ጀግንነት በነቢዩ ኤልያስ ዘንድ አልነበረም ማለት ነው? ፈጽሞ አይደለም። ኢዩ ላይ የነበረ ብርቱ ቅባትና ጀግንነት የተገኘው ነቢዩ ኤልያስ ያን ያህል ጠሞ፣ ጸልዮ፣ ተጨንቆና ተጉዞ መሬት ተነቅንቆ፣ ዐውሎ ነፋስና እሳት ተገልጦ የተቀበለውን ጸጋ እነ ኢዩ ተጠቀሙበት። የነቢዩ ኤልሳዕ ቅባት ደግሞ ከኢዩም ሆነ ኤልሳዕ እንደተባለ። ዛሬም ከኢትዮጵያ አገልጋይ ያመለጠውን የኬንያ አገልጋይ ከኬንያ አገልጋይ ያመለጠውን የናይጄሪያ እንዳይባል አስቀድሞ መጠንቀቅ ለኢትዮጵያውያን እላለሁ።



በዚህም ዘመን እንዲሁ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ምድር እንዲመጣ ነፍሱንም ለወዳጆቹ አሳልፎ ሰጠ። በመስቀል ሞት በመታዘዝ እኛን ወክሎ ነበር። እንደ ያዕቆብ መለኮታዊ ጠጉር በእጆቻችንና በሰውነታችን በሙሉ በማኖር በረከትን ተቀበልን። የጌታን ጠጉር ለማግኘት ሁሉ ሆነልን። "... በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፣ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።" (ኢሳ. 53፡7) እኛ የእርሱን ጠጉር ለብሰን የራቁትነታችንን እፍረት ሸፈንን። አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ ጌታ እንስሳ አርዶ ቁርበት እንዳለበሰው እኛም ጌታ በሸላቶቹ ፊት ዝም በማለት ጠጉሩ ተሸለተ። እኛም ለበስን በዚህም ጸጋ ተጠቀምን። በተለይ የጌታ መንፈስ በምድር ይወርድ ዘንድ ጌታ ራሱን በመስቀል አሳልፎ ሰጠ። «... ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።» (ዮሐ. 7፡39) ጌታ በመስቀል በመታገስ ወደ ክብር ስፍራ ገባ በዚህም መንፈስ ቅዱስ ወረደ። መንፈስ ቅዱስ የወረደ ቀን ንግግር ያደረገው ጌታ ኢየሱስ ሳይሆን ሐዋርያው ጴጥሮስ ነበር። ጌታ ለዚህ ሁሉ ተጋደለ ለስላሳው ጴጥሮስ አገልግሎት አደረገ። ኤልያስ በመታገል ጸጋን ተቀብሎ አመጣ ኤልሳዕ አገለገለበት፤ እኛም ጌታ በለፋበት ጉዳይ ገብተን መንፈስ ቅዱስ በኛ ይጠቀማል። በራሳችን ምንም እንዳልሆንን ይገባን ዘንድ ራስ በራ በሆነው ማንነታችን የጌታ ጸጋ ወረደልን። ምንም የቤቴል ብላቴኖች ቢያፌዙብንም የጌታ ጸጋ በላያችን በስውር እንሠዲራ ጌታ ስለእኛ ደከመ። የእርሱን ጠጉር ተጠቅመን እናገለግላለን።

# 12. የአቤሴሎም ጠጉር

"በእስራኤልም ሁሉ ዘንድ እንደ አቤሴሎም በውበቱ የተመሰገነ ሰው አልነበረም፡ ከእግሩ እስከ ራሱ ድረስ ነውር አልነበረበትም፤ ጠጉሩም ይከብደው ነበርና በዓመት አንድ ጊዜ ይቈርጠው ነበር፡ ሲቈረጥም የራሱ ጠጉር በንጉሥ ሚዛን ሁለት መቶ ሰቅል ያህል ይመዝን ነበር ...።" (2ኛ ሳሙ. 14፥25-26)

## 12.1. አቤሴሎም

"... ከጌሹር ንጉሥ ከተልማይ ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም ነበረ።" (2ኛ ሳሙ. 3፥3) አቤሴሎም በአባቱም ሆነ በእናቱ የንጉሥ ልጅ ዝርያ አለው። አቤሴሎም ከአባቱ ቤት ሲኰበልል በቀጥታ በጌሹር አገር ወደ ተልማይ ዘንድ ይገባል ከእስራኤላውያን እናት ሳይሆን ከጌሹር አገር ጋር ዝምድና አለው። ጌሹር በሶሪያ የምትገኝ ግዛት ነች።

የዳዊትን በኩር ልጅ አምኖንን በመግደል የአባቱን ልብ ብዙ ዘመን እንዲያለቅስ አድርጓል። አቤሴሎም ከአባቱና ከእናቱ የተወለደች ትዕማር የምትባል ውብ እህት ነበረችው። የአባቱ ልጅ ስለደፈራት አቤሴሎም ይህን ለመበቀል ግብዣ አዘጋጅቶ የበኩር ወንድሙን በሰይፍ ስለት ገደለ። ለእኅቱ ሲል ወንድሙን ገደለ። ልጅ ሲወልድም የሴት ልጁን ስም በእኅቱ ስም ትዕማር አላት።

አቤሴሎም የዳዊትን ቤት ምስቅልቅል በማድረግ የታወቀ ነበር። ለንጉሥ ዳዊት ትልቅ ፈተና ነበር። የንጉሡን ሠራዊት አለቃ የኢዮአብን የገብስ አዝመራ በአቤሴሎም እርሻ አጠገብ ይገኛል። ከጌሹር ኰብልሎ ከሦስት ዓመት በኋላ አባቱን ለማየት ሲመጣ



ኢዮአብን እንዲያስገባው ጠየቀ። ኢዮአብም ነገርን ሲያስረዝምበት አቤሴሎም አስልኮ የኢዮአብን አዝመራ አነደደው። (እዚህ ላይ የሚደንቀኝ ዋነኛ የጦር አለቃ ኢዮአብ ከንጉሥ ደጅ በሚያገኘው ደመወዝ ብቻ ሳይሆን ራሱ መሬት ነበረው በዚህም ገብስ እያረሰ ኑሮውን ያቀና ነበር። ጦርን ከግብርና ጋር ያጣመረ ነበር በዚህ ዘመን ያሉ ባለሥልጣናት የኢዮአብን አካሄድ ቢሄዱ በቂ ንብረት በቀጥተኛ ሁኔታ ባገኙ ነበር)

አቤሴሎም በእስራኤል ዘንድ ፈራጅ ለመሆን በማሰብ የእስራኤልንም ልብ ለፍርድ ሲመጡ በማባበል ልባቸውን ሰረቀ። በተንኰልም ለመንገሥ ሁሉን አደረገ። "አቤሴሎምም በእስራኤል ነገድ ሁሉ፡ የቀንደ መለከት ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ፡ አቤሴሎም በኬብሮን ንጉሥ ሆኖ በሉ የሚሉ ገበኞች ላከ።" (2ኛ ሳሙ. 15፥10) እንደ ወንድሙ አዶንያስ ይህም ከመንገድ ውጭ ወጥቶ ንግሥናን ለራሱ ያዘጋጀ ነው። ንጉሡ የማያውቀውን ንግሥና ለራሱ ለማግኘት ሞከረ።

የአባቱን ቁባቶች ነጥቆ በፀሐይ ለማርከስ ተነስቶም ሆኖለታል። አጠቃላይ በንጉሥ ዳዊት ኑሮ ውስጥ ከንጉሥ ሳኦል በከፋ ሁኔታ አቤሴሎም ችግር አመጣበት። አባቱን ለመግደል ከአኪጦፌልና ከኩሲ ልዩ ምክር ይቀበል ነበረ። ለዳዊት ታላቅ የስንቅፋት ድንጋይ ሆኖበታል።

## 12.2. የየዓመቱን የአቤሴሎም ጠጉር ክብደት

አንድ ሰው አቤሴሎምን ተመልክቶ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይነሳል። በእስራኤል ሁሉ ዘንድ እንደ አቤሴሎም ውብ ባለመገኘቱ ሁሉ የአቤሴሎምን ውበት ያደንቃል። ከራሱ እስከ እግሩ እንከን

የማይወጣለት በመሆኑ ነውር የሚባል በእርሱ ላይ አይታይም። ከእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች መካከል የሰው ልጅ ከፍተኛ ነው። አቤሴሎም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች መካከል በውጭ የሚታዩ ፍፁም እንከን የሌለው በመሆኑ የሰማይና የምድር ጌታ ይመስገንበታል። ከአዲስ ኪዳን በፊት ትልቁ የሰዎች ልጆች ውበት የሚለካው በተክለ ሰውነታቸው እንደ ሆነ ይታወቃል። ለምሳሌ ኢዮብ ከመከራው በኋላ ከጌታ ዘንድ ከተባረከበት መካከል ሦስት ሴቶች ልጆች ነበር። ከነስማቸውና ከነውበታቸው በምዕራፍ 42 ተገልጾ ይገኛል በምድር ሁሉ እንደ ኢዮብ ሴቶች ልጆች ውብ አልነበረም።

አቤሴሎምን መጽሐፍ በግልፅነት ያስቀመጠው ከተክለ ሰውነት ውበቱ መካከል የጠጉሩ ጉዳይ ሲሆን በአንድ ምዕራፍ ውስጥ በሁለት ቁጥሮች ውስጥ (ቁጥር 25-26) ስለ አጠቃላይ ውበቱ ሲገልጥ ከዚህ ውስጥ አንዱ ቁጥር የጠጉሩን ውበት ብቻ በመግለጥ ነው። ስለዓይኑ፣ ስለአፍንጫው፣ ጥርሱ አልተገለጠም። ስለ ጠጉሩ ክብደት፣ አቆራረጥ፣ አመዛዘን ተዘርዝሮአል። አቤሴሎም ጠጉሩን በየዓመቱ መቆረጥ ይገባዋል። በየዓመት መጨረሻ ሊቆረጥ ሲቃረብ ጠጉሩ እየከበደው ስለሚመጣ እንቅስቃሴውን ይገታበታል። እየተራመደ ጭንቅላቱ ወደ ኋላ ዝቅ ስለሚያደርገው እረፍት ያጣል በመሆኑም በየዓመቱ ይቆረጥ ዘንድ ይገደዳል።

አቤሴሎም ጠጉሩን ሲቆረጥ በቀጥታ ወደ ሚዛን ይወስደውና በንጉሥታት ሚዛን ያስመዝነዋል። የየዓመቱን ክብደት ያነፃፅራል። በአማካኝ የዓመቱ የጠጉሩ ክብደት 200 ሰቅል (2.5 ኪ.ግራም) ያህል



ይሆናል። ይህን ለአንድ ዓመት ባሉ ቀናት ቢካፈል በየቀኑ እግዚአብሔር ደግሞ የአቤሴሎምን ጠጉር 7 ግራም ይጨምርለታል። ይህ ማለት አቤሴሎም ጠጉሩን በ7 ቢጎነጉን ለእያንዳንዱ ጉንጉን አንዳንድ ግራም በየቀኑ ይጨምርለታል።

የአቤሴሎም ጠጉር እድገት ለመንፈሳዊው ጸጋ አስተዳደግ ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል። ከሰውነታችን ክፍል እድሜ ልክ ከሚያድጉ ብልቶች መካከል ዋነኛው ጠጉር ነው። የመንፈሳዊው ሰውም እድገት እንደ አቤሴሎም ጠጉር በየዓመቱ ይህን ያህል ቢጨምር ከጥቂት ጊዜ በኋላ እጅግ የተጠራቀመ ጸጋ ይኖረዋል። አቤሴሎም ለ30 ዓመት ያህል ጠጉሩን እየመዘነ ቢያስቀምጥ ወደ 75 ኪ.ግራም ይደርሳል። ይህ ደግሞ የትልቅ ሰው ክብደት ነው። የክርስቲያንም ጸጋ በየቀኑ እያደገ በየዓመቱ የውበቱን ክብደት ምን ያህል እንደ ሆነ መገመት ይቻላል። ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን በአንድ ርዕስ ላይ አንድ ዓመት ቢጸልይ ይህ ጉዳይ በየዓመቱ ተቆርጦ መለካት ይኖርበታል። በየቀኑ የሚያድገው ጸጋ በየዓመቱ መቋጫ ማግኘት ይገባዋል። ለምሳሌ አንድ መንፈሳዊ መምህር ተማሪዎቹን "በእግዚአብሔር ክብር" ርዕስ ላይ እየጸለየ ቢያስተምር በዓመት መጨረሻ ይህ ርዕስ በክርስቲያኑ ልብ ክብደትን አግኝቶ መቋጫ ሊኖረው ይገባል። በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚቀጥለው ደግሞ "የእግዚአብሔር ብርሃን" ወዘተ እያደገና እየተቋጨ ወደሚቀጥለው ጸጋ ሊታደግ ይገባዋል። "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ።" (2ኛ ጴጥ. 3፥18) ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ የእድገትን

አቅጣጫ ሲጠቁመው "ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር። ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።" (1ጢሞ. 4፥15-16)

## 12.3. የአቤሴሎም መጨረሻ

"አቤሴሎም ከዳዊት ባሪያዎች ጋር በድንገት ተገናኘ፡ አቤሴሎምም በበቅሎ ተቀምጦ ነበር፥ በቅሎውም ብዙ ቅርንጫፍ ባለው በታላቅ ዛፍ በታች ገባ፥ ራሱም በዛፉ ተያዘ፤ ... ተንጠለጠለ፥ ተቀምጦበትም የነበረ በቅሎ አለፈ። ኢዮአብም፥ ... ሦስት ጦሮች በእጁወስደ፥ አቤሴሎም ገና በዛፍ ለይ ተንጠልጥሎ ሕያው ሳለ በልቡ ላይ ተከላቸው።" (2ኛ ሳሙ. 18፥9-14)

የአቤሴሎም ውበቱ በራሱ ባለው ጠጉሩ ነበረ። ዓመት መጨረሻ ላይ ራሱ ከጠጉሩ የተነሣ ይከብደው ነበር። ከንጉሥ ዳዊት ጋር ጦርነት በከፈተ ጊዜ ግን ራሱ በሰማይና በምድር ለሚያንጠለጥለው ለታላቁ ዛፍ ተጣለ። ብዙ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ ብዙ ጠጉር ያበቀለውን ራስ ያዘው። ብዙ ጠጉሩ ለመንጠልጠል መንገድ ሆነበት። የገዛ በቅሎው ጌታውን ትቶ አንጠልጥሎት ከዳው፥ ከዳዊት ጋር የሚጣላ ሰው ለሰማይም ለምድርም እንደማይበጅ ሆኖ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠለጠለ። አንድ ሰው የከፋ በደል ሲሠራ በእንጨት ይሰቀላል በእንጨትም የተሰቀለ የተረገመ ነው። አቤሴሎም በራሱ በቅሎ በእንጨት ተንጠለጠለ። እንግዲህ ለውጊያ በተሰማራን ጊዜ የተቀመጥንባቸው መለኮታዊ በቅሎ ወይት



እንደሚገቡ በጥንቃቄ ልንመራ ይገባል። በቅሎውን መግራት ያልቻለ ሰው ከንጉሡ ጋር ተጋጨ።

አቤሴሎም የእስራኤልን ሕዝብ ልብ ሰርቆ የራሱ አድርጎ ነበር። ሕዝቡ ከዳዊት ልብ ተነስቶ ወደ ራሱ ያዘነብል ዘንድ በዳዊት በር ላይ ይህን አደረገ። ዛሬ ደግሞ የአቤሴሎም ልብ በሦስት ጦሮች ይወጋ ዘንድ ተንጠለጠለ። ተንጠልጥሎ በጦር የተወጋ ጌታ ኢየሱስ ነው። ጌታ የሕዝቡን ኃጢአት ሲሸከም ረጅም ሰአት በእንጨት ተሰቅሎ ተሰቃየ ከዚያም በጦር ተወጋ። አቤሴሎም የእስራኤልን ሕዝብ ልብ በመስረቅ ይህን ተሸክሞ በታላቅ እንጨት ተንጠለጠለ በጦርም ተወጋ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ይህ ዕጣ ደረሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ጽድቅ አቤሴሎም ግን በራሱ ኃጢአት።

ሰው ከዳዊት (ከእግዚአብሔር ልብካለው) ጋር ሲጣላ ይህ እጣ ከደረሰው ከእግዚአብሔር ልጅ (ከኢየሱስ ክርስቶስ) ጋር የሚጣላ መጨረሻው ምን ይሆን? እግዚአብሔር የሰጠው ጸጋ በወጉ ካልተጠቀምንበት መጨረሻ የተዋጥንበት ጸጋ ይጣላናል አቤሴሎም ውበት በራሱ ላይ ነበር። መሞቻውና ለጠላት እጅ መውደቂያው ራሱ ሆነበት። ሶምሶን ያን ሁሉ ጸጋ ባይሸከም የፍልስጥኤም መኳንንት በሙሉ እርሱን ለማጥፋት ያን ያህል ባልሸመቁበት በመጨረሻም ዓይኖቹ በጠላት ጦር ባልጠፉ ነበር።

ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔር ልብ እያለው የቤቱ ኑሮ ግን እጅግ ምስቅልቅል ያለ ሆነ። አቤሴሎም አባቱን ለመግደል በመነሳት በዚህ አይነት መልክ ተገደለ። የበኩር ልጁ አምኖን እኅቱን ትዕማርን ድንግልናዋን በመድፈሩ አቤሴሎም ወንድሙን ገደለው ትዕማርም ሃፍረትዋን ትሸከም ዘንድ የጋለሞታን ልብስ ለበሰች። ሰሎሞን

ወንድሙን አዶንያስን በሱናማይቱ አቢሳ ምክንያት ገደለው። ሱነማይቷ አቢሳ ደግሞ ንጉሡ ዳዊትን ታሞቀው ዘንድ የተፈለገች ውብ ሴት ነበረች። ሰሎሞንም በብዙ ሴቶች ፍቅር በመነደፍ ጣኦታትን ያመልክ ዘንድ ራሱን አዘነበለ በዚህም የእስራኤል መንግሥት ለሁለት እንዲከፈል ምክንያት ሆነ። በመሆኑም የሰው ልጅ አስቀድሞ የቤተሰቡን ሁኔታ ፈር ያስይዝ ዘንድ እግዚአብሔርን መማፀን ይገባዋል። በተጨማሪም የንግሥና መንፈስ የተጠናወተው ሰው አባቱን በግልጥ ጦርነት አውጆ ከዘመተ ዛሬም ይህን የሚመኙ ሁሉ ማንኛውንም ጥፋት ለማጥፋት ወደ ኋላ እንደማይሉ ማስረጃ ጥሎልን ሄዷል።



## 13. ሱነማይቱ አቢሳ

"ወዳጄ ሆይ፡ እነሆ፥ ውብ ነሽ፡ ...
ጠጕርሽ በገለዓድ ተራራ እንደሚወርድ
እንደ ፍየል መንጋ ነው። (መኃ. 4፥1፡ 6፡ 5)
የራስሽም ጠጕር እንደ ሐምራዊ ሐር ነው፥"
(መኃ. 7፥6)

መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ የሰሎሞን መዝሙር እንደ ሆነ በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ተጠቅሶአል። ከመዝሙሩም ዋና ፍሬ ነገሮች መካከል የወዳጆቹን ፍቅር በጥበብ መደርደር ሲሆን ሁሉ በወጉ ተስለው አንዱ አንዱን የሚገልጥበት ስንኞች ናቸው። በእዚህ መጽሐፍ ላይ ፍቅር ቀዳሚ ሲሆን ይህም በግልጥነት ልጁም ሰሎሞን በጥበብ ተነድቶ ይዘምራል። ይህ ዝማሬ ከመዝሙሮች ሁሉ የሚበልጥ በመሆኑ ከወንድና ከሴት ፍቅር፣ ከትዳር ፍቅር፣ ከቤተሰብ ፍቅር፣ ለአገር ፍቅር፣ ወይንም ፍቅር ተብሎ ቋንቋ ከወጣለት ፍቅር የሚበልጥ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን በመሆኑ የዚህ መዝሙርን ፍቺ ለዚህ መለኮታዊ ፍቅር ልንጠቀምበት እንችላለን። "ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤" (ኤፌ. 5፥26) የሁሉ ማሰሪያ የክርስቶስ ፍቅር ነው። ከመዝሙሮች ሁሉ የሚበልጠውም መዝሙር የክርስቶስ የፍቅር ሥራ ነው። ማንም እርሻውን፣ ልጁን፣ ሚስቱን፣ የራሱን ሕይወት ስንኳ ካልካደ ለእኔ ሊሆን አይገባም በማለት ጌታ ከተናገረ ከሁሉ የእርሱ ፍቅር በለጠ።

ንጉሥ ሰሎሞን ሱላማጢስ ወይንም ሱነማይቱን አቢሻ የውበቷን ግርማ ሲገልጥ ጠጉሯን በሰፊው ሲያብራራ በተለይም የጠጉሮችዋ መቀመጫ የሆነውን ራስ እንደ ቀርሜሎስ ተራራ በላይዋ እንደ ተቀመጠ አመለከተ። ከዚህ ላይ ጠጉሮችዋ በገለዓድ ተራራ እንደሚወርድ እንደ ፍየል መንጋ ነው ይህ ማለት የእርስዋ ጠጉር ሕይወት እንዳለው አካል የሚንቀሳቀስ ዚግዛግ እየሰራ በተርታ የሚወርድ አንዱ አንዱን ሳይገፋ መንገዱን እየጠበጠበ የሚጓዙ መንጋዎች አስመስላቸው። ከአናትዋ ወደ ታች የተንዠረገገው ጠጉሮችዋ እንደሚንቀሳቀሱ የእንስሳት አወራረድ ይመስላሉ። መጨረሻቸው ምድር የሆነ የፍየል መንጋ ከተራራ እንደሚወርድ ሁሉ የእርስዋም ጠጉር መጨረሻ ምድር እንደ ሆነ ያመለክታል። ጠጉር የእግዚአብሔር ውበት ካለውና በጥንቃቄ ከተያዘ በውስጡ የደም ስር እንዳለው ሕያው አካል ይመስላል። የሚንቀሳቀስ ከተራራ እንደሚወርዱ የፍየል መንጋ ይመስላል።

ሰሎሞን ይህን ጠጉር በሌላ ቋንቋም ገለጠው ሐምራዊ ሐር እንደሚመስል ተናገረ። ሐር ከጥቃቅን ነፍሳት የሚሰራ ክር ሲሆን ይህም በጥንቃቄ የሚፈተል የልብስ ዓይነት ነው። የዚህችም ውብ ሴት ጠጉር ሐር የሚመስል ሆኖ መልኩም ሐምራዊ ነው። የሴቶች ጠጉር ይህን ከመሰለ ለንጉሡ ሰሎሞን ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር ውስጥ ይካተታል። የውበት መደመደሚያ የሆነችው ይህች ውብ ሴት ጠጉሮችዋ ሐምራዊ ሐር መስለው ከገለዓድ (ከመድኃኒት) ተራራ እንደሚወርዱ እንደ ፍየል መንጋ ይመስላሉ ይህ መለኪያዊውን የሴቶችን የጠጉር ውበት መግለጫ ነው።



የቤተ ክርስቲያን ውበትም በራስዋ ላይ የሚበቅለው የመለኪያዊው ጠጉር ውበት ነው። የቤተ ክርስቲያን ራስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተተክሎ ከዚህ ስፍራ የሚበቅለው ሐምራዊ ሐር የሚመስል ጠጉር ተጎናጽፋ ልትገኝ ይገባታል። በጠጉሮችዋ ላይ ያለው ውበት ሕይወት እንዳለው ተንቀሳቃሽ ጠጉር ማለትም ከገለዓድ ተራራ እንደሚወርድ እንደ ፍየል መንጋ መሆን ይገባዋል። በዚህ ውበት ላይ ከሰሎሞን የበለጠው ጌታ ከዝማሬ ሁሉ የሚበልጠውን ዝማሬ ያሰማል። "ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ በማኅበርም መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ።" (ዕብ. 2፡13) ጌታ ይዘምራል በማኅበርም ይዘምራል።

አንድ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ራእይ ስትታይ በጠጉሮችዋ ውበት ሐምራዊ ሐር ከመሰለ ከመዝሙር ሁሉ መዝሙር የዘመረችና የተዘመረላት ነች።

# 14. የዕዝራ ጸሎት

የዕዝራን ጸሎት ከመመልከታችን በፊት ጥቂት ስለ ዕዝራ እንመልከት:: መጽሐፈ ዕዝራ አስር ምዕራፍ ያዘለ የመጽሐፍ ክፍል ሲሆን ከ70 ዓመት ባቢሎን ምርኮ በኋላ የእግዚአብሔር ቤት ስለመሠራት፣ መታደስ፣ የክህንነት አገልግሎት አጠቃላይ መንፈሳዊ መነቃቃት (Spiritual Revival) ያካተተ መጽሐፍ ነው:: የዕዝራ የራሱ ታሪክ የሚጀምረው ግን ከ7ኛው ምዕራፍ ላይ ነው::

በመጀመሪያው ምዕራፍ እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ በማነሳሳት የእግዚአብሔርን ቤት በማሠራት ይህ ንጉሥ እንዲህ በማለት ተገለጠ:: "የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፡ በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፡" (ዕዝ. 1፡2) እንዲህ ዓይነት ንጉሥ በዘመናት ይኑሩልን:: እግዚአብሔርን የነገሥታት ንጉሥ እንደሆነ በሥራቸው የሚገልጡ:: የሰማይ ንጉሥ እግዚአብሔርና የምድር ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር የተሾመ ንጉሥ ቂሮስ አንድ ዕቅድ ለማስፈጸም ተዋዋሉ:: በይሁዳ ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ብቻ ነው የዚህ ውጤት ግን ማንም እንደሚጠብቀው አልሆነም:: "በዚያን ጊዜም በኢየሩሳሌም ያለው የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ቀረ፡ እስከ ፋርስም ንጉሥ እስከ ዳርዮስ መንግሥት እስከ ሁለተኛው ዓመት ድረስ ተጓጐለ::" (ዕዝ. 4፡24) ይህ ለምን ሆነ? ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ ሲቃረቡ ኢየሩሳሌምን አስቀድመው የያዙ ሕዝቦች የቂሮስን አሳብ አስገለበጡት:: እነዚህ የእስራኤል ልጆች ወደ ምድራቸው ከገቡ ለአንተ አደገኛ ናቸው ግብርና ምጥን አይከፍሉም



በአሕዛብ መካከል አደገኛና አደናጋሪ ናቸው ብለው ንጉሡን ሌላ መልክ እንዲይዝ አደረጉት፤ የእግዚአብሔርም ቤት ሥራ ተጓጐለ:: እንግዲህ የሰማይን ንጉሥና የምድር ነገሥታት በአንድ አሳብ ተስማምተው አንድ ሥራ ለመሥራት ቢዋዋሉም ሊስተጓጐል የሚችልበት ሁኔታዎች ከጠላት ሊነሣ ይችላልና ለምን ዛሬ የተስፋ ቃሌ በጌታ ቃል በገባልኝ መሠረት አልተፈጸመም በማለት መታገሉ የሚያዋጣ አይመስለኝም:: በእርግጥም በሌላ ዘመን (በዳርዮስ ሁለተኛ ዓመት) ይፈጸማልና እንደገና መጠበቅ ተገቢ ነው:: ዕዝራ የአሮን ዘር ሲሆን ካህንና ጸሐፊ ነበር:: በንጉሥ አርጤክስስ የከበረ የእስራኤል ልዩ አምባሳደር ነበር:: "... ከንጉሥ ነገሥት አርጤክስስ ለሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ለካህኑ ለዕዝራ፡ ሙሉ ሰላም ይሁን፡ በመንግሥቴ ውስጥ ካሉ ከእስራኤል ሕዝብ ... ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ የሚወድድ ሁሉ ከአንተ ጋር እንዲሄድ አዝዣለሁ:: በእጅህ እንዳለችው እንደ አምላክህ ሕግ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ትጎበኝ ዘንድ፡ ንጉሡና አማካሪዎቹም መኖሪያው በኢየሩሳሌም ለሆነው ... ለአምላካቸው ቤት በፈቃዳቸው የሚያቀርቡትን ትወስድ ዘንድ በንጉሡና በሰባቱ አማካሪዎች ተልከሃልና ስለዚህ በዚህ ገንዘብ ... ግዛ፡ በኢየሩሳሌም ባለው በአምላካችሁ ቤት መሠዊያ ላይ አቅርባቸው:: ... እኔም ንጉሡ አርጤክስስ በወንዝ ማዶ ላሉት በጅሮንዶች ሁሉ ይህን ትእዛዝ ሰጥቻለሁ፡ የሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ሁሉ አዘጋጁለት፡ ... አንተም ዕዝራ፡ በእጅህ እንዳለው እንደ አምላክህ ጥበብ መጠን በወንዝ ማዶ ባሉ ሕዝብ ሁሉ የአምላክህን ሕግ በሚያውቁ ሁሉ ላይ

ይፈርዱ ዘንድ ዳኞችንና ፈራጆችን አስነሣ፡ የማያውቁትንም አስተምሩአቸው። የአምላክህንም ሕግ፡ የንጉሡንም ሕግ በማያደርግ ሁሉ ላይ ሞት ወይም ስደት ወይም ገንዘብን መወረስ ወይም ግዞት በፍጥነት ይፈረድበት።" (ዕዝ. 7፡12-26)

እንግዲህ ንጉሥ ነገሥታት አርጤክስስ ከካህኑ ከዕዝራ በቀር ልዩና ሙሉ ሥልጣን የሰጠው የለም። ገንዘብ ውሰድ፣ መሥዋዕያ ሰዋ፣ ዳኞችንና ፈራጆችን ሹም፣ ለአንተና ለሕጉ የማይታዘዝ ፈጣን እርምጃ እስከ ሞት ድረስ ይወሰድ። በተለይም አርጤክስስ ዕዝራን ሲጠራው "የሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ" በማለት ነበር። የዓለም መንግሥታት ለእግዚአብሔር ካህን ይህን ያህል ሥልጣንና ክብር ሲሰጡ የእስራኤል ሽማግሌዎች ግን ካህኑን አስጮኹት፣ አስለቀሱት ...

ከዕዝራ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ የዕዝራ ጸሎት በሰፊው የሚገኘው በምዕራፍ 9 ውስጥ ነው። ምዕራፍ 8 ሲጠቃለል የመስዋዕት ዓይነቶች ተገለጹ። ለእስራኤል አምላክ ያቀረቡት የመስዋዕት ብዛት ከፍተኛ ነበር ይህ ከተፈጸመ በኋላ ለዕዝራ የደረሰው መልእክት እጅግ አስደንጋጭ ሆነበት። የእስራኤል ሕዝብና ካህናት ሌዋውያንም ጭምር በከነዓን ምድር እንደሚኖሩ የአሕዛብ ዓይነት ኑሮ ይኖሩ ነበር። በምዕራፍ 9 ቁጥር 2 የተገለጠው ደግሞ እጅግ አሳፋሪ ሆነበት። "ለራሳቸውና ለልጆቻቸውም ሴቶች ልጆቻቸውን ወስደዋል፡ የተቀደሰውንም ዘር ከምድር አሕዛብ ጋር ደባልቀዋል፡ አስቀድሞም አለቆቹና ሹማምንቶቹ በዚህ መተላለፍ መጀመሪያ ሆነዋል አሉኝ።" እስራኤል መስዋእት በማቅረብ የታወቁ ሲሆኑ የተቀደሰውን ዘር



ከአሕዛብ ለመደባለቅም ቀዳሚ ናቸው። በዚህ ጉዳይ ፍፁም አይጠነቀቁም፡ ካህናትም ሌዋውያንም ሽማግሌዎቹም ቢሆኑ በዚህ ታላቅ ኃጢአት ተላልፈው ተገኙ።

"ይህንም ነገር በሰማሁ ጊዜ ልብሴንና መጐናጸፊያዬን ቀደድሁ፡ የራሴንና የጢሜንም ጠጕር ነጨሁ፡ ደንግጬም ተቀመጥሁ።" (ዕዝ 9፡3) ዕዝራ ምን ያህል የጌታ ፍቅርና ፈቃድ በእርሱ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል። ጠጉርንና ጢምን መንጨት ማለት ከፍተኛ ብስጭት ያዘለ መግለጫ ነው። የሚያደርገውን ሲያጣ ጠጉሩንና ጢሙን ነጨ። ካህናት ጠጉራቸውና ጢማቸው ዋና መለያቸው ሲሆን ዕዝራ ግን የእስራኤል በደል ሲመለከት ማንነቱን ሳተ። የራስ ጠጉርና ጢም ሲነጭ በአንድ ሰው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ያን ያህል በመሆኑ በዕዝራ ተገለጠ።

ዕዝራ ከፍተኛ የቁጭት ጸሎት ሲጸልይ ከእንባ ጋር ነበር። "ዕዝራም እያለቀሰና በእግዚአብሔር ቤት ፊት እየወደቀ በጸለየና በተናዘዘ ጊዜ ከእስራኤል ዘንድ የወንድና የሴት የሕፃናትም እጅግ ታላቅ ጉባኤ ወደ እርሱ ተሰበሰበ፡ ሕዝቡም እጅግ አለቀሱ።" (ዕዝ. 10፡1) የዕዝራ ዕንባ በሁሉ ዘንድ ዕንባን ፈጠረ። እርሱ በማልቀሱ ሕዝቡም አብሮ አለቀሰ። እጅግ የተጨነቀ ሰው ጸሎትን አሰማ። እውነተኛ ሰው በጸሎቱ ወቅት ዕንባ ይኖረዋል ከዚህም በላይ የድንጋጤ መንፈስ ይታይበታል። አገር በሙሉ ስድ ሲለቀቅና የእግዚአብሔር ቁጣ ሲመጣ እንደ ዕዝራ ጢማቸውን እየነጩ

መንፈሳዊ ስሜት የሚያራምዱና የሚያስተምሩ ልጆችን ጌታ በሁሉም ዘመን ይፈልጋል።

በዚህን ጊዜ እስራኤል ከ70 ዓመታት የምርኮ ጊዜያት የተመለሰበት ነበር። በብዙ ቅጣት ከተቀጡ በኋላ ይስተካከላሉ ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ ከበፊቱ የከፋ በደል በእስራኤል ቅሬታ ተገኝባቸው። ዕዝራ ከምርኮ የተረፉትንና የተመለሱትን "ትንከር" በማለት ይጠቅሳቸዋል። እነዚህ ትንከሮች የእስራኤል ሕዝብ ፈጽሞውኑ ከሚጠፋ የተረፉ ነበሩ። አሁንም ይህን ኀዘን ለመግለጥ የተከበረውን ጠጉሩንና ጢሙን ነጨ።

በዚህ ባለንበት ዘመን የዕዝራ ልብና መንፈስ ያላቸው ትንከሮች በምድር ቢኖሩ የጌታን ልብ ወደ እስራኤል አእላፋት እንዲያዘነብል ያደርጉ ነበር። ስለጽድቅ ነፍሳቸውን የሚያስጨንቁ፣ ስለ ኃጢአት የሚጋደሉ፣ ጠጉራቸውንና ጢማቸውን የሚነጩ፣ የሚያለቅሱና መንፈሳዊ ያቸውን የሚቀድዱ የልብ ሰው ቢነሱ ሁሉን ያቀናሉ። ዕዝራ ይህን ሁሉ ሲያደርግ ራሱን ከበደለኞች ለይቶ አልነበረም። "... እነሆ በፊትህ በበደላችን አለን፣ ስለዚህ በፊትህ ሊቆም የሚችል የለም።" (ዕዝ. 9፥15) ከዓለማውያን ጋር ተባምዶ ሁሉን ማድረግ እንደ ወግ በተያዘበት በዚህ ዘመን ውስጥ አለን ጌታን እናገለግላለን በምንል ሰዎች መካከል ዘርን የደባለቅን እንገኛለን። በጌታ ሕዝብ ገንዘብና ንብረት በመነገድ ቤቶቻችንን በከበሩ ማስደናት የምናስጌጥ አያሌዎች ነን። ከአገር ወጥተን ማገልገል ማለት ለራስ ጥቅም ከሚወጡ ነጋዴዎች መደብ የተሰለፍንም ተገኝተናል። ጠምና ጸሎት እንደማያስፈልግ አድርገን በየመሰብሰቢያው አዳራሾች ተናግረናል።



ያለዝሙት ምክንያት ሚስቶቻቸውን ፈትተው ሌሎችን የሚያገቡም ተበራክተዋል። የዓለማዊ ባህል አጥንቶቻችን ድረስ ዘልቆ በመግባት በአንደበት በጌታና በዙፋኑ ዙሪያ ስናሸበሽብ እንገኛለን። ላባችን እስኪፈስ ለጌታ እንዘምራለን፣ ለኃጢአትና ለዓለማዊነትም ላባችንን እናፈሳለን። ይህ ሁሉ ሆኖ በጌታ ጸጋ እንነግዳለን።

ጌታ ኢየሱስ ይህን አስከፊ ኃጢአት አስመልክቶ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ገልጦልናል። ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትቦ በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው እንኳ መንካት አይወዱም። ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ፣ ዘርፋን ያስረዝማሉ፤ በምሳም የከበሬታ ስፍራ፤ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር፤ በገበያም ሰላምታና፤ መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ። እናንተ ግን፣ መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለሆነ እናንተ ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና፥ ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ።

በዚህም ዘመን የክርስቲያኑን ከተማ ያጥለቀለቀው ይኸኛው ነው። መምህር ለመባል ሁሉን ማድረግ። ከሁሉ መጀመሪያ ወንበር ለማግኘት መሽቀዳደም ወይንም ሊቀ ሊቃውንት ተብሎ መጠራት መፈለግ ከተጀመረ መቼ እንደሆነ አይታወቅም። ክርስቶስ ነው ሊቃችሁ ብሎ ክርስቶስ ከተናገረ ለምን ይህን ጉዳይ በስፋት ዘመትንበት? ዕዝራ ቢኖር ይህ ሁሉ ጠጉሩንና ጢሙን ያስነጨው ነበር። ሁሉ በደለኛ ሆኖ በጌታ ፊት ማንም መቆም እንደማይችል ይረዳ ነበር።

የክህናት ጢም የከበረና የጸጋ ምሳሌ ነው። ይህ ጢም የእስራኤልን ሕዝብ ልዕልና ያመለክታል። የእስራኤል ማኅበረሰብ ከኃጢአት በታች ከዘቀጡ ይህ ጢም በምላጭ ሳይሆን በመነጨት ያውም በራሱ በካህኑ እጅ ይነቀላል። ከሰውነቱ በመጣበቁ እንደ ጉድፍ በመቁጠር ነቅሎ ይጨርሰዋል። በጌታ ዘንድ የኃጢአት አስከፊነት ከዚያ የባሰ በመሆኑ ጌታ ኢየሱስ ራሱን እንደ በግ በመቁጠር (በሸላቶቹ) በወገኖቹ ፊት ዝም አለ። በአራጁ ፊት ዝም የሚያሰኝ ኃጢአት በዓለም በመኖሩ ጌታ ዝም ብሎ መለኪያዊ ጠጉሩ ከላዩ ተነሳ።

ዕዝራ በዚህ ሁሉ ጉስቁልና ጢሙንና ጠጉሩን ነጭቶ አልቅሶ፣ ተዋርዶ፣ ማቅ ለብሶ በመጨረሻ የዚህ ፍሬ ምን ሆነ? "እስከ መጀመሪያው ወር እስከ መጀመሪያው ቀን ድረስ ሠርተው እንግዶቹን ሴቶች ያገቡትን ሰዎች ሁሉ መርምረው ጨረሱ። ከካህናቱም ወገን ልጆች እንግዶቹን ሴቶች ያገቡትን ሰዎች ሁሉ መርምረው ጨረሱ። ከካህናቱም ወገን ልጆች እንግዶቹን ሴቶች ያገቡ ሰዎች ተገኙ፤ ከኢዮሴዴቅ ልጅ ከኢያሱ ልጆችና ከወንድሞቹ፡ መዕሤያ፡ አልዓዛር፡ ያሪብ፡ ጎዶልያስ። ሚስቶቻቸውን ይፈቱ ዘንድ እጃቸውን ሰጡ፤ ... እነዚህ ሁሉ እንግዶቹን ሚስቶች አግብተው ነበር፤ ከእነዚህም ሚስቶች አያሌዎቹ ልጆችን ወልደው ነበር።" (ዕዝ. 10፡17-44)

እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ምርመራ አያሌዎችን ከነስማቸው ዝርዝራቸውን በመጽሐፍ ከጻፈና ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ ቃል እንዳስገባቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ተናገረ። ዛሬ በአዲስ ኪዳን



ያለን እኛ ከብዙ ነገር ጋር ተጋብተን (አንደኛው ከማያምኑ ጋር ጋብቻ ነው) በፍጹም ድፍረት በእግዚአብሔርና በመቅደሱ ከተገኘን በውኑ የኛን ስም ከመጽሐፉ ይደብቅልን ይሆን? የታላቁ ካህን የኢዮሴዴቅ ልጅ የኢያሱ ልጆች በዚህ ወንጀል ከተገኙ ማን ጤነኛ ይሆን? እግዚአብሔር የሰማይ አምላክ ፈጣን ሕግ ጸሐፊና የታወቀ ከህንን ቢያስነሳልንና ቢማልድልን ምኞቴ ነው። ዘማሪው - ፍሬ አልባ ንስሃ ነጋ ጠባ አማረኝ በማለት የተናገረው ፈዕሞ ለዚህ ትውልድ ላለነው መሆኑ አሁን ተረድቻለሁ።

# 15. የሕዝቅኤል ጠጉር

"አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ የተሳለን ጐራዴ ውሰድ፥ እንደ ጢም መላጫ ወደ አንተ ትወስደዋለህ፥ ራስህንና ጢምህንም ትላጭበታለህ፤ ሚዛንንም ውሰድ ጠጕሩንም ትከፋፍላለህ። የመከበብም ወራት በተፈጸመ ጊዜ በከተማይቱ መካከል ሢሶውን በእሳት ታቃጥላለህ፥ ሢሶውን ወስደህ ዙሪያውን በጐራዴ ትመታለህ፥ ሢሶውንም ወደ ነፋስ ትበትናለህ እኔም በኋላቸው ጐራዴ እመዝዛለሁ።" (ሕዝ. 5፥1-4)

"ከአንቺም ሢሶውን በቸነፈር ይሞታል፥ በመካከልሽ በራብ ያልቃል፥ ሢሶውን በዙሪያሽ በሰይፍ ይወድቃል፥ ሢሶውንም ወደ ነፋሳት ሁሉ እበትናለሁ በኋላቸውም ሰይፍ እመዝዛለሁ።" (ሕዝ. 5፥12)

## 15.1. የእስራኤል ሕዝብ በዚያ ዘመን

ሕዝቅኤል ምዕራፍ 2 ላይ የእስራኤልን የወቅቱ ባህርይ ይገልጣል። ዓመፀኛ፣ ኩርንችት፣ እሾህ፣ ጊንጥ፣ የጠነከረ ግንባር መገለጫቸው ነበር። ሕዝቅኤል በእነዚህ ምርኮኞች መካከል ይቀመጣል ተማርከውም ሳሉ ከዚህ ባሕሪያቸው አልተላቀቁም።

በዚያን ዘመን ሕዝቅኤል እንደ እነርሱ እንዳይሆን ተነግሮታል ለዚህም መፍትሔ የእግዚአብሔርን ቃል ጠቅልሎ መብላት ነበር። ከዚህም በላይ የእስራኤልን ሕዝብ በደል ለመሸከም ይችል ዘንድ በግራ ጎኑ ሦስት መቶ ዘጠና ቀናት ተኛ በሌላ ጊዜ ደግሞ በቀኝ ጎኑ ተኛ። አንድ ቀን መኝታ የአንድ ዓመት ኃጢአት የሚያክል



ለማስተሰረይ ታገለ። ሕዝቅኤል በእነዚህ ቀናት የመከራ እንጀራ ይበላ ዘንድ ተወሰነበት። ከስንዴና ከገብስ፣ ከባቄላ፣ ምስር፣ ጤፍና አጃ በአንድ እቃ ውስጥ አድርጎ ቂጣ እንዲበላ ተመደበ። ከሰውም በሚወጣ ፋንድያ በእስራኤላውያን ፊት እንዲጋግር ቃል መጣለት። ይህ የሆነበት እስራኤል በተበተኑበት አገር ሁሉ በአሕዛብ መካከል ርኩስ እንጀራ ይበሉ ዘንድ ነበር።

የእስራኤል ሕዝብ ታላቅ በደልን ሲፈጽም ነቢያትና ካህናት አብረው ይሰቃያሉ። በአሕዛብ መካከል ከአሕዛብ በደል የሚከፋ ፈጸሙ፥ በዚህም እግዚአብሔር እስራኤልን በአሕዛብ መካከል በተናቸው። በነዚህ አሕዛብ መካከል ሲኖሩ ከአሕዛብ ይልቅ እየተጎሳቆሉ የመከራ እንጀራ ይበሉ ዘንድ ተጣለባቸው።

## 15.2. የተሳለ ጐራዴ

ሕዝቅኤል ካህን ነው "ወደ ካህኑ ሕዝቅኤል መጣ።" (ም. 1፥3) ሕዝቅኤል ነቢይም ነው። (ም. 2፥5) እስራኤል በሙሉ በከፋ በደል ውስጥ ሲገኙ ሕዝቅኤል ግን ሁለቱን የጌታን በር ይከፍት ነበር። በሁለት የተለያዩ ጸጋዎች ያገለግላል፥ በክህነት ጸጋው የቤተ መቅደስን ሥራ ይሠራል የሕዝቡንም በደል ለማስተሰረይ ሁሉን ያደርጋል፥ በነቢይነት ጸጋው ለሕዝቡ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት ተቀብሎ ያመጣል፥ ሕዝቡን በጌታ ቃል ያፀናል፣ ይመክራል፣ ይገስፃል፣ ይባርካል።

ሕዝቅኤል ካህን በመሆኑ የጠጉርና የጢም ማሳደግን ሕግ ይከተላል በዚህም ምክንያት ጠጉሩና ጢሙን በማሳደግ በምርኮኞች አገርም ቢሆን ጌታን ያገለግላል። ሕዝቅኤል ይህንን ጠጕሩን ይላጭ

ዘንድ ልዩ ትእዛዝ መጣለት። በምላጭ ወይንም በሌላ ሳይሆን የተሳለ ጕራዴ ይወስድ ዘንድ ነበር። ጠጕሩንና ጢሙን በተሣለ ጕራዴ መቆረጥ እጅግ የሚያስቃይ ሲሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅና የክብር መውረድ ነው። በክህነትና በነቢይነት የሚያገለግልን ሰው በጕራዴ ጠጕርህን ተላጭ ማለት የሚያስደነግጥ ነው። የእስራኤል ጠባቂ የነበረ ሰው አናት ላይ አክሊልና ጸጋ መቀመጥ ሲገባው የተሳለ ጕራዴ እንዲያርፍበት ተደረገ።

የሕዝቅኤል ጠጕርና ጢም በጎራዴ መላጨቱ በምድረ እስራኤል ሕዝብ ሊያልፍ ያለውን ሰይፍ ያመለክተናል። የተሳለ ጕራዴ ትላልቅ ነገር መስራት ሲችል ለሕዝቅኤል ጠጕር መላጫ ማገልገሉ የሚደንቅ ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ከፍተኛ በመሆኑ ታላቅ የበቀል መገልገያ ተላከ። የሕዝቅኤልን የክህነት ውበት የሚላጭ ጕራዴ ተወሰነ።

## 15.3. በሚዛን የተመዘነ ጠጕር

በጕራዴ የተላጨውን ጠጕር በሦስት እኩል ቦታ ይከፋፍል ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ። የሕዝቅኤል ጠጕር የእስራኤልን ሕዝብ ስለሚወክል የሚዛን አመዛዘኑ ፍጹም ጥንቃቄን ይፈልጋል። በሦስት እኩል ቦታ ተከፋፍሎ ለሦስት የተለያዩ ጥፋቶች ይውላሉ።

የመጀመሪያው ሢሶ ለእሳት ሲደረግ ሕዝቅኤል በዓይኑ እየተመለከተ የጠጕሩንና የጢሙን ጠጕር አቃጠለ። የእግዚአብሔር ጸጋና ቅባት ያደረበት የካህኑ ጠጕር ይቃጠል ዘንድ ተመደበ። ይህን ጠጕር ለእሳት የዳረገው ከተማይቱ ከተከበበች በኋላ ነበር። ለእሳት የተሰጠው ይህን ሢሶ ሕዝቅኤል ሲገልጠው ቸነፈርና ራብ ነው።



ቸነፈርና ራብ በእሳት የተቃጠለውን ጠጕር ሲገልጠው ይኸውም የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቁጣ ቸነፈርና ራብ ነው ይህም የእሳት ምሳሌ ነው። በሰይፍ የሞተው ከራብ ከሞተው ይሻላል። ራብ የእሳት ምሳሌ በመሆኑ አስጨናቂው ቅጣት ይህን መስሎ ተገለጠ። እንግዲህ የአንድ ካህን ጠጕር ሲቃጠል ከታየ በዚያች ምድር ቸነፈርና ራብ እንደሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ይገልጣል። የሕዝቅኤልን ጠጕር እሳቱ በልቶ አመድ እንዳደረገው ሁሉ ሢሰው ሕዝብ በቸነፈር ይሞታል በራብም ያልቃል።

የሁለተኛውን ሢሶ በጕራዴ ተቀጠቀጠ። ጠጕሩን የላጨው በጕራዴ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሢሶውን በዚሁ ጕራዴ ቀጠቀጠ። ረጅሙ ጠጕርና ጢም በጕራዴ ተቀጥቅጦ ተቆራረጠ ብናኝ ሆነ በዚህም የእስራኤላውያን ሢሶ ለሰይፍ ተዳረጉ። የእግዚአብሔር ሰይፍ በነፍሳቸው አለፈ። ሕዝቡ በሰይፍ ተመታ ተቆራረጠም። ሕዝቡ በሰይፍ ከመመታቱ በፊት የካህኑ ጠጕር በሰይፍ ተመታ እግዚአብሔር ከካህኑ ጋር ተስማማ። የበቀል ቀን መቆረጡ በመሆኑ ሁሉን በሥርአቱ አደረገ። ትንቢቱ ሲፈጸም ለሕዝቅኤል አዲስ አይደለም ነገር ግን ሕዝቅኤል የሚጸልይበትን የጸሎት ርዕስ አገኘ። ነቢዩ አጋቦስ የሐዋርያው ጳውሎስን የኢየሩሳሌም መከራ ያስረዳው በምሳሌ ነበር። "... ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁዳ ወረደ። ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወስዶ የገዛ እጁንና እግሩን አስሮ፡ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ፡ ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያስሩታል ...።" (የሐዋ. 21፡10-11) ሕዝቅኤል የራሱን ጠጕር በጕራዴ እንደቀጠቀጠ

እግዚአብሔርም የራሱን ሕዝብ በራሱ ሰይፍ ይቀጠቀጥ ዘንድ ሁሉን አዘጋጀ። እስራኤል በገለጡት ኃጢአት የእግዚአብሔር ሰይፍ ይመዘዝ ዘንድ መንገድ ከፈቱ።

የሦስተኛው ሚሶ ጠጉር ምስጢር ወደ ነፋሳት ይበተን ዘንድ ስላለው ሕዝብ ነው። ለሰማይ ነፋሳት ተጣለ። ሁለቱ በአገር ውስጥ መከራ ሲደርስባቸው የሦስተኛው ሚሶ ደግሞ ከአገር ውጭ በአሕዛብ መንደር የሚደርስባቸው መቅሰፍት ይሆናል። ወደ ሌላ አገር መወሰዳቸው ማምለጣቸውን አይተካም በተበተኑበትም ምድር ሰይፍ ያገኛቸው ዘንድ በኋላቸው ሰይፍን እመዛለሁ የሚል መልእክት አለ። ከሕዝቅኤል ጠጉር በጎራዴ ተነቅለው ለነፋሳት እንደተጻረጉ እነዚህም በተበተኑበት አገር ሰይፍ ይከተላቸዋል።

## 15.4. ከራስ የወደቁ ሕዝቦች

የሕዝቅኤል ጠጉርና ጢም የእስራኤልን ሕዝብ ይወክላል። ከሕዝቅኤል ቍንቅላት በጎራዴ የወረደው ጠጉር ተላጭቶ ባዶ እንደሆነ እስራኤልም ባዶ ትሆን ዘንድ ተወሰነ። ካህኑ ጠጉሩ ተለየው ሕዝቡም የሕይወት ጸጋ ተለየው። ሕዝቅኤል ጠጉሩን በሚዛን በመከፋፈሉ ሕዝቡም እንዲሁ በሦስት የጥፋት ረድፍ ተሰለፈ። ለአንደኛው ሚሶ በስህተት ከፍ ያለ ሚዛን ቢመጣ የእስራኤልም ሕዝብ በዚህኛው ሚሶ አንጻር ይጠፋል። በመሆኑም ሕዝቅኤል ጠጉሩን በጥንቃቄ በሚዛን መደበ። በዚያን ዘመን ይህን ዓይነት ሚዛን መኖሩ ይደንቃል።

የሕዝቅኤል ጠጉር ከራሱና ከጢሙ ያድግ እንደ ነበር እስራኤልም እንዲሁ ያድግ ነበር። እግዚአብሔር ከሰማይ



የሕዝቅኤልን ጠጉር ሲመለከት በዚህ ውስጥ እስራኤልን ይመለከታል። የመንግሥት ልጆች የተባሉት የእስራኤል ማኅበረሰብን ተሸክሞ ይንቀሣቀሳል። የሕዝቅኤል የራሱ ጠጉር የተቈጠረ ነው። "የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል።" (ማቴ. 10፥30) የካህኑ ጠጉር ከራሱ ላይ ተላጭቶ በመውደቁ እስራኤል ከክህናትና ከነቢያት አገልግሎት ተለዩ በዚህም መስዋእት ሆኑ። ክህናትና ነቢያትን ማክበር ይገባናል በክህናትና በነቢያት መሠረት የተመሠረተው እስራኤል በዚህ መልክ ረገፉ። በሕዝቅኤል ልብስ መቋጠሪያ እንዲጠበቁ የታዘዘው ጥቂት ጠጉር ቅሬት ሆኑ። ለእስራኤልም ችንካር ሆኑ። አዲስ ኪዳን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ሲጸና የብሉይ ደግሞ በክህናትና በነቢያት ነበር።

## 16. በናቡከደነፆር ላይ የወረደ ቅጣት

"ቃሉም ገና በንጉሡ አፍ ሳለ ድምፅ ከሰማይ ወደቀና፡ ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ፡ መንግሥት ከአንተ ዘንድ አለፈች ... በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነፆር ላይ ደረሰ፥ ጠጉሩም እንደ ንስር፡ ጥፍሩም እንደ ወፎች እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተለይቶ ተሰደደ፡ እንደ በሬም ሣር በላ፡ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ።" (ዳን. 4፡31-33)

እንዲት ከእስራኤል ውጭ የሆነች ምርኮኛ ሴት ለእስራኤል ወንድ እንዴት እንደምትዳር በዘዳግም 21 ተመልክተናል። የእስራኤልን ምድር ለማጥፋት መጥታ ልትማረክ ትችላለች። የእስራኤል ወንድ ደግሞ ውበቷን ተመልክቶ ሊያገባት ይመኛል በዚህን ጊዜ ሊደረግላት የሚገቡ ነገሮች አሉ።

1. የምርኮ ልብሷን ታወልቃለች፡
2. ጠጉሯን ትላጫለች ጥፍሯንም ትቈርጣለች፡
3. አንድ ወር ያህል ለዘመዶችዋ ታለቅሳለች።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ትዳራለች። ማለትም ከላይ የተጠቀሱትን ሥርአቶች ከተሟሉ ይህች ሴት በእስራኤላውያን ሴቶች መዝገብ ትገባለች።

የናቡከደነፆር የትዕቢት ቋንቋም ሰውየው ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንዲቀይር አስገደዱት፡ ጠጉሩና ጥፍሩን መቀየር ተገባው። ይህ ከሆነ ሰው መሆኑ ይቀርና እንደ ሌላ ፍጡር ይቆጠራል ጠጉሩና ጥፍሩ ዕድሜ ልኩን የሚያድጉ በመሆናቸው ሁለቱ ተቀየሩ። የሰው ፍጡር መሆኑ ቀርቶ በእንስሳ ተርታ ተመደበ።



የናቡከደነፆርን ትዕቢት ለመምታት ሥልጣን እንዳለው ልዑል አምላክ መሰከረ። በዓለም መንግሥታት ረድፍ የወርቅ መንግሥት ተብሎ የተመሰከረለት ንጉሥ በዚህ መልክ ፍርድን ተቀበለ። የንስሩ ላባ ላይ የሰማይ ጠል እያረሰረሰው ብርድን እንዲቋቋም ይጠቅመዋል። መሬት ቆንጥጦ እንዲይዝ የወፍ ጥፍር ይረዳዋል። የዚህ ሁሉ ቅጣት መነሻው ትዕቢት ሲሆን የቅጣቱም ይዘት ዓለምን የሚሞላ ዛፍ በመጥረቢያ ተቆርጦ ፍሬውና ቅጠሉ ረግፎ ጉቶው እንዲቀር ነው። ናቡከደነጾር ከዚህ ቅጣት እንዲካፈል እንጂ እንዲያመልጥ ዳንኤል ሲገልፅ "በብረትና በናስ ማሰሪያ ታስሮ በመስክ ውስጥ ይቈይ።" (ቁ.23)

ናቡከደነፆር በዚህ ቅጣት ወቅት ሰዎች ፈልገው እንዳያገኙት መጽሐፍ ይገልጣል። ሰባት ዓመት ከተፈፀመና ቅጣቱ ካለቀ በኋላ ግን "በዚያን ጊዜም አእምሮዬ ተመለሰልኝ፡ ለመንግሥቴም ክብር ግርማዬና ውበቴ ወደ እኔ ተመለሰ፡ አማካሪዎቼና መኳንንቶቼም ፈለጉኝ፡ በመንግሥቴም ውስጥ ጸናሁ፡ ብዙም ክብር ተጨመረልኝ።" (ቁ.36)

እግዚአብሔር በትዕቢት የተሞሉትን የነገሥታት ንጉሥ የሆኑትን ሰዎች ለመቅጣት አስቀድሞ መልክን ይቀይራል። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ምሳሌና መልክ በመሆኑ የከፋ ቅጣትን ሲያስተላልፍ ሰውን አውሬ ይመስል ዘንድ ቃል ይሰጣል። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ እስከ ዕለተ ሞት የሚያድግ ጠጉርና ጥፍር በመሆኑ የመጀመሪያው ቅጣት ይካፈላል።

አንድ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፊት ሲበድል መለኮታዊ ጠጉር ይቀየራል መለኮታዊ ውበቱም ይጠፋል። ናቡከደነፆር እንደ በሬ የሆነ ሆድ ዕቃ እንደ ነበረው ሁሉ ክርስቲያኑም ለሆዱ የሚሠራ ይሆናል። የናቡከደነጸር አእምሮ እንደ ተወሰደበት ይኸውም በጠጉር እንደ ተገለጠ የክርስቲያንም አእምሮ ከተወሰደ በመለኮታዊ ጠጉሩ ይታወቃል። በጥፍሩ እንደሚከላከል ወፍ የክርስቲያኑም ጥፍር ኃይለኛ ይሆናል። ይህ ሁሉ በብረትና በናስ ማሰሪያ የተደረገ የፍርድ ውሳኔ ነው። ማንም ሊፈታው የማይችል ከሰው የሚለይ፣ ያለመኖሪያ የሚያስቀር፣ ሙሉ ዘመን (ሰባት ዓመት) የሚፈጅ ቅጣት ነው። እግዚአብሔር በዚህ መልክ የሚያስተምራቸው አያሌዎች ናቸው። የናቡከደነፆርን የትዕቢትን ቋንቋ በግልጥ ተቀምጧል። "ንጉሡም፡ ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን? ብሎ ተናገረ።" (ቁ.30)

በመጀመሪያ ናቡከደነፆር ያመሰገነው ራሱን ነው በጉልበቱም ፍፁም ተማምኗል የሚሠራው ሥራ ሁሉ ለራሱ ግርማዊነትና ክብር ነበር። በሌላ መልኩም የራሱን መንግሥት መኖሪያ አከበረ። ከሁሉ የከፋው እግዚአብሔርም የተፀየፈው ባቢሎን የናቡከደነፆር ለግርማዊነቱ መግለጫ መሆንዋ ነበረ፣ እግዚአብሔር በዘፍጥረት ያፈረሰውን ይህ ሰው በዚህ ዘመን ገነባት። የጋለሞቶች እናት በተባለችው ባቢሎን ተደስተ ቋንቋ የተደባለቀበት ሥፍራ ናቡከደነፆር ለመክበር ተነሣ። በዚህ የልዑል ቁጣ ወረደበት በዚያችው ሰዓት ጠጉሩና ጥፍሩ ተቀየረ። ከሁሉ የሚደንቀው ግን ታላቂቱ ባቢሎንን



ለመግዛት አያሌዎች ይመኛሉ። ሰባት ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ግን የናቡከደነፆር ቦታ ክፍት ሆኖ መጠበቅ መቻሉ ነው። ዛሬ አንድ መሪ ከስፍራው ከጠፋ ወዲያው ገልብጠው ይቀመጡበታል። ናቡከደነፆር ግን ቅጣቱን ከጨረሰ በኋላ ስፍራው፣ ሕሊናውና ግርማዊነቱ በልዑል አምላክ ተጠበቀለት አማካሪዎቹና አገሩ ሁሉ በክብር ፈለጉት።

አሁን ባለንበት ዘመን መጨረሻ ላይ ደግሞ ታላቂቱ ባቢሎን በመንፈሳዊው ዓለም ትገኛለች። ለአሁኗ ባቢሎን (መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ባቢሎን) ደግሞ ቁጣ ከልዑል አምላክ ተመድቧል። "ከዚህም በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር በራች። በብርቱም ድምፅ፦ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም መናፍስት ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤ አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሣ ወድቀዋልና፥ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ዘንድ ውጡ፥ ኃጢአትዋ እስከ ሰማይ ደርሶአልና እግዚአብሔር ዓመፅዋን አሰበ። ... ስለዚህ በአንድ ቀን ሞትና ኀዘን፥ ራብም የሆኑ መቅሠፍቶችዋ ይመጣሉ፥ በእሳትም ትቃጠላለች፤ የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና።" (ራእ. 18፥1-8)

# 17. የወንድና የሴት ጠጉር

"በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፡ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን? ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት፡ ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንኳ አያስተምራችሁምን? ጠጉርዋ መጎናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቶአታልና። ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ፡ እኛ ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ ልማድ የለንም።" (1ኛ. ቆሮ. 11፡13-16)

"ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም፡ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት።" (1ኛ. ቆሮ. 11፡7)

የቆሮንቶስ መልእክት ምዕራፍ 11 አንድ ልዩ የሚያደርገው ባሕሪ አለው ይኸውም ስለ ሐዋሪያው ጳውሎስ የመንፈሳዊ ሕይወት እድገትን በማውሳት የሚጀምርም ነው። "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል ..." ወልድን የተመለከተ አብን እንደሚመለከት ሁሉ ሐዋርያው ጳውሎስን (ጌታ ኢየሱስን ስለሚመስል) የተመለከተ ጌታን ይመለከታል። እንግዲህ ጌታ ካረገ በኋላ እርሱን የሚመስሉ ልጆች በሥጋ የገለጠላቸው በመሆኑ የቆሮንቶስ ምዕመናን እጅግ የተባረኩ ናቸው።

የሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን የመምሰል ምሥጢር ከተናገረ በኋላ በቀጥታ የገባው ሴት፣ ወንድ፣ ክርስቶስና እግዚአብሔር ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በራስ አስመስሎ አስተማረ። አንዱ አንዱን ይገልጣል። ሚስት ባልዋን እንደምትገልጥ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ይገልጣል። ወንድ (እንደ ጳውሎስ አይነቱ) ክርስቶስን ይገልጣል



ይህም በራስ ነው አንዱ የአንዱ ራስ ነው። አንድነት ይኖር ዘንድ መከባበርን አስቀመጠ።

በጸሎት ጊዜ ሊሆን የሚገባውን አስተማረ። አንድ ሰው ወደ ጸሎት አደባባይ ሲቀርብ ወንድ ወይንም ሴት መሆኑ የሚለየው በተገለጠው ጠጉር ነው። በጸሎት ወቅት ጠጉር ከተገለጠ ይህ ወንድ ነው ጠጉር ከተሸፈነ ወይንም መላጣ ከተሆነ ደግሞ ይህች ሴት ናት እንደሚባል ጳውሎስ በመንፈስ ጠቆመን። ይህ ማለት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ሲያደርግ በጭንቅላቱ ላይ ወይንም ውስጥ የሚካሄድ መለኮታዊ ግንኙነት እንደሆነ ነው።

ወንድ ሲጸልይ ራሱን ገልጦ ጠጉሩን ማሳየት እንደሚገባው ተናገረ። በዚህም የወንድ ራስ ለክርስቶስ የተሰጠ በረከት እንደሆነ አመለከተን። ሴት ራስዋን በመሸፈንዋ ለወንድ ክብር የተጠበቀች መሆንዋን ያመለክታል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ሁሉ ለጌታ ክብር ነው። ለምሳሌ የክርስቶስ ራስ እግዚአብሔር ነው በሚለው ቋንቋ መሠረት የሴት ራስ ወንድ ነው የሚለውን መመልከት ይበጃል። ክርስቶስ በእግዚአብሔር አምሳል የሚኖር እግዚአብሔር ወልድ ነው። ሴትም በወንድ አምሳል የምትኖርና የተፈጠረች ነች። ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ራሱን እንዳስገዛ ሴትም ለወንድ ወንድም ለክርስቶስ ራሱን ቢያስገዛ የመለኮታዊ ሥርአት ፈርን ይይዛል።

"ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፡ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነውና።" (1ቆሮ. 11፡5) በዚህ ጥቅስ መሠረት ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ብትጸልይ ወይም ትንቢት ብትናገር ምንም አይነት መለኮታዊ ጸጋ

አይጎድልባትም። መጸለይ፣ ትንቢት መናገር ወዘተ ይቻላል። ሸፈነችም አልሸፈነችም ጸጋው አይጎድልም በሰውም ስትታይ ያው ነች። ነገር ግን ጠጉርዋን ሳትሸፍን ብትጸልይና ትንቢት ብትናገር በእግዚአብሔርና በሰማይ ሠራዊት ፊት ራስዋን ታዋርዳለች። ራስዋን የተላጨች ሴትና ራስዋን ሳትሸፍን የምትጸልይ በሰማይ ሠራዊት ፊት አንድ ነው።

በአዲስ ኪዳን ዘመን ይህን አይነት ሥርአት መኖሩ የሚደንቅ ነው። የመለኮታዊው ጠጉር ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮም ጠጉር የጸሎት አውድማ ላይ ያን ያህል ጉልህ ሚና መኖሩ የሚደንቅ ነው። ይህ ግን ብዙ ክርክርና ውዝግብን እንደሚያስነሳ አውቆ ቅዱስ ጳውሎስ ጆሮ ያለው ይስማ በሚል ቋንቋ ዘጋው። የአንድ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሳይሆን የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ሕይወት እንደሆነ መሠከረ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በውጭ ባለ ሥርአት እጅግ የማይጨነቅ ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ነበር። ለምሳሌ በእስራኤል ባህል መሠረት ዋናው ሕግ የመገረዝ ሕግ ነው። በቅዱስ ጳውሎስ ሕይወት ግን ይህ ታላቅ በውጭ የሚደረግ ሥርአት ሥፍራ አልሰጠውም። "በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፤ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፥ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፤ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም።" (ሮሜ 2፡28-29) በመንፈስና በሥጋ የሚደረገውን የመገረዝ ሥርአት በዚህ መልክ ያስቀመጠ ጳውሎስ በሥጋ የሆነ የጠጉር ሥርአት ያን ያህል እንዴት ሊገደው እንደቻለ



በመንፈስ ቅዱስና በቅንነት ጌታን ልንጠይቅ ይገባል። አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ተገርዘዋል ኢየሱስም የመረገዘን ኪዳን ጠብቋል። ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ጳውሎስ በዚያን ዘመን ስለመገረዝ ሲያስተምር የውስጥ የልብ እንጂ የውጭ እንዳልሆነ ያስተምራል። ስለ ጠጉር ግን ከፍተኛ ስፍራ ሰጥቶ ክርስቶስ የወንድ ራስ በመሆኑ ወንድ ጠጉር መሸፈን የለበትም የሚል ትምህርት አስተማረ። ሴት የወንድ ክብር በመሆንዋ ጠጉርዋንና ራስዋን ልትሸፍን ይገባታል ይለናል።

ለወንድ ጠጉር ማስረዘም ነውር እንደሆነ እያስተማረ በአሁኑ ሰዓት ወንዶች ጠጉራቸውን በማስረዘም ከተፈጥሮ ጋር እንኳን ሲጋጩ እንመለከታለን። በተለይም የኢየሱስ ክርስቶስ ምስል ነው ተብሎ የሚነገረን ፎቶግራፍ ላይ ኢየሱስ ራሱ ጠጉሩን አስረዝሞ ይስሉታል። ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ እንደ ማንም አይሁዳዊ ወንድ ኖረ እንጂ ሌላ ልዩ ምልክት አልነበረውም። ጌታ በጌቴሴማኒ ሌላ ልዩ ምልክት ቢኖረው የይሁዳን እርዳታ ባላስፈለጋቸው ይሁዳም የሚፈልጉት ስፍራ ካደረሳቸው በኋላ ምልክት የሰጠው በመሳም እንጂ በሌላ አልነበረም። የኢየሱስ ናዝራዊነት ናዝሬት ከተማ በመኖሩ ብቻ ነበር።

ማንኛውም ክርስቲያን በጸሎት ወቅት የተወሰነ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባዋል። በተለይም ጭንቅላቱን ለመንፈሳዊው ዓለም መክፈትና ቋንቋን መጠበቅ ያስፈልጋል። ያዕቆብ በቤቴል ሲጸልይ ሰማይ እንደ ተከፈተና የእግዚአብሔር መልአክት ሲወጡና ሲወርዱ እንደታዩት እግዚአብሔርም ከመሰላሉ ጫፍ ላይ መኖሩን ተገንዝቦ መጸለይ ይኖርብናል። በዚህን ወቅት ለመላእክቶችም ሲባል ሴቶች

ጠጉራቸውን ቢሸፍኑት ተገቢ ነው ይህም በፍቅር የሚሆን ጥያቄ እንጂ በግድ አይደለም:: ጌታ ይህን ምሥጢር በመንፈስ ለአንዲት እኅት ቢገልጥላት ለወደፊቱ ተሸፍና መጸለይ መጀመር ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ሳትሸፈን የጸለየችባቸው ጊዜያት ሁሉ ፀፀት ውስጥ ይጥላት ነበር:: ከክርስትና እምነት ውጭ የሆኑ ሴቶች በየመንገዱ ለጠጉራቸውና ለልብሳቸው ሲጠነቀቁ የሰማይ አምላክ በዚህ ጉዳይ በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የሚያፍር ይመስለኛል:: ቢያንስ ስትጸልዩና ትንቢት ስትናገሩ ጠጉራችሁን ሸፍኑ ከተባለ ቀላል ትዕዛዝ መሆኑ ታውቆ መተግበር ይኖርበታል:: በሌላ እምነት ክፍል የሚገኙ ደግሞ በመንገድ ስትሄዱ ፊታችሁን ሸፍኑ ሲባሉ እንኳ ይህን አደረጉ::

ሐዋርያው ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ስለ ባልና ሚስት ጉዳይ በሰፊው ማብራሪያን ሰጥቷል:: ምዕራፍ 3 ሲጀምር እንዲህ በማለት ነው:: "እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው:: ለእናንተም ጠጉርን በመሽረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጐናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ::" በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት ላይ ስለ ባልና ሚስት ጉዳይ ምክርን ሲሰጥ የጀመረው በሚስት እንጂ በባል አይደለም:: ከባሎች መካከል ለእግዚአብሔር ቃል ትምህርት የማይገዛ ቢኖር ለዚህ ሰው መፍትሔ ሚስትየዋ እንድትጸልይ፣ እንድትጦም፣



እንድትመክረው ወይንም እንድትማረር አልተናገረም:: ወይንም ሚስትየዋ ለጌታ ትምህርት ታዛዥ ሆና ባልየው ባይታዘዝ በባልየው ላይ መቅሠፍት እንደሚወርድበት አልጠቆመም:: ሚስትየዋ በጌታ ትምህርት እኖራለሁ ካለች ልታደርግ የሚገባት ቃሉን በሥራ መተርጐም ብቻ ነው:: ማለትም ሰውየው የፈለገው ዓይነት ባሕሪይ ይኑረው ሚስትየዋ ልታደርግ የሚገባት ንጹሑን ኑሮዋን እያሳየችው፣ እየታገሰች፣ አንድ እርምጃ ሂጂ ስትባል ሁለት እያደረገች፣ እየመረቀች እንድትሄድና (ከተቻለም) ሣራ አብርሃምን ጌታ ብላ እየጠራች እየታዘዘች ብትኖር ይህች ሴት የሣራ ልጅ ትባለለች:: ይህ እየሆነ ሲሄድ የባልየው አለመታዘዝ ወደ መስበር ይመጣና በሴትየዋ ኑሮ ሳያውቀው የጌታን ትምህርት ተግባራዊ ማድረግ ይጀምራል:: በዚሁ ምዕራፍ ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲያብራራ "ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው፥ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልክል፥ ከክፉ ፈቀቅ ይበል፥ መልካምንም ያድርግ፥ ... በጎ ስለ ማድረግ መከራን ብትቀበሉ ይሻላችኋልና::" (1ኛ ጴጥ. 3፥10-17) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎችን፣ ጠቦቶችንና ግልገሎችን አደራ የሰጠው እረኛው ጴጥሮስ ከሆነ ከሁሉ ቅዱሳን ይህን አባት መስማት ግዴታችን ይሆናል::

ቅዱስ ጴጥሮስ ሴቶችን ካስጠነቀቀበት ዋነኛ ጉዳይ በውጭ ሽልማቶችን በማያበዙ ላይ ነው:: በተለይም ጠጉርን በመሽረብና ወርቅን በማንጠልጠልና ልብስን በመጐናጸፍ ላይ በሚያተኩሩ ሴቶች ላይ መንፈሱ እንደማይመቸው ገለጣ አደረገ:: በውጭ የተሸረበ ጠጉር ሳይሆን በልብ በውስጥ የተገለጠ የዋህነትና ዝግተኛ መንፈስን ፈለገ::

ኃይለኛ፣ ተናጋሪ፣ ተከራካሪ፣ ሽማግሌ እርቅ አዘውታሪ ሴቶችን ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የማይጠፋና የተሰወረ ልብን ሲፈልግ እንመለከታለን:: ለብዙ ባሎች መገዛትና ክብር ወደ ጌታ ትምህርት መመለስ ዓይነተኛ ተግባር የሚገኘው ከጥሬ ቃሉ ብቻ ሳይሆን ከሚስቶች እጅግ የከበረ ጸጋ መሆኑ ነው:: በአንድ አገር አንድ መሪ፣ በአንድ አውራጃ አንድ ተጠሪ፣ በአንድ መሥሪያ ቤት አንድ አለቃ እንዳለ ሁሉ በአንድ መኖሪያ ቤት አንድ ተጠሪ እንጂ ሁለት ከሆነ ያ ቤት አይቆምም:: ለቤታቸውም ይህን ባል ተጠሪ ቢያደርጉትና እነቶች ቢገዙለት ሁሉ ቤት ምንኛ ወደ ክብር ይመለስ ይሆን? ይህን ደግሞ ለጌታ እግዚአብሔር ክብር ለስፈራችንና ለአገራችን ጌጥ በሆነ እላለሁ:: በምዕራባውያንና በሰለጠኑት አገር ስንመለከት ሴት ልጅ ተወልዳ እስክትዳር ድረስ በአባትዋ ስም ትጠራለች:: አባትና እናቷን ታከብራለች፣ ትገዛለች ይህም የታወቀና ተጨማሪ ማብራሪያ አይጠይቅም:: ይህች ልጅ ለትዳር ስትበቃ ወዲያው የአባቷን ስም ማስጠራት ታቆምና በባልዋ ስም ትጠራች:: ባለቤትዋ እንደ አባትዋ በመሆን የመጀመሪያውን ስም መጠሪያ ትቀይራለች:: ይህ ማለት ይህች ሴት የባልዋ ልጅ ነች እንደ ማለት ይመስላል:: ልጅ ደግሞ ለአባትዋ ትገዛለች::

የሥጋ ጠጉር ይህን ያህል የሚያስተምር ከሆነ በመለኮታዊ ጠጉር ልንጠነቀቅ ይገባል:: ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ነች:: ለአንድ ወንድ የታጨች ድንግል ነች:: ጠጉርዋን እንደ ሐምራዊ ሐር አስረዝማ ለክርስቶስ ሽፍና የምታቀርብበት ራስዋንም



የምትጎናጸፍበት በመሆኑ ለዚህ ልትጠነቀቅ ይገባታል:: "ጠጉርዋ መጎናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቶአታልና::" (1ኛ ቆሮ. 11፥15) ቤተ ክርስቲያን ጠጉሯን አስረዝማ ልትጎናጸፍበትና ለክርስቶስ ልትጠብቅ ይገባታል::

በየሰርግ ቤቱና በየአብያተ ክርስቲያኑ ውስጥ አንድ የምረቃ ቃል እንሰማለን:: ትዳራችሁ "የአብርሃምና የሣራ ያድርግላችሁ::" በእውነትም የሚደንቅ ነው::: አብርሃም ሦስት ሰዎች ከሩቅ ሲመጡ አየ:: የሣራን ፈቃድ ሳይጠይቅ የሚከተሉትን ትእዛዝ ለሣራ አወረደው::

- ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ፥ ለውሺውም እንጐቻም አድርጊ አላት፥
- እጅግም የሰባም ታናሽ ጥጃ ያዘና ለብላቴናው ሰጠው ያዘጋጅም ዘንድ ተቻኮለ፥
- እርጐና ወተትም ...

"እነርሱም፦ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? አሉት:: ..." (ዘፍጥ. 18፥9)

ይህ ሁሉ ሲሆን ሣራ በድንኳን ተቀምጣ እንግዶችን እንኳ አላየቻቸውም:: ከየት መጡ? እነማን ናቸው? እኔ ለማላውቃቸው ሰዎች ይህ ሁሉ ነገር ለምን ይሰጣል አላለችም:: ፈጥኖ፣ ፈጥኖ፣ ፈጥኖ ተዘጋጀ፣ አዘጋጀች:: በዚህ ዘመን የቤት ሠራተኛ እንኳ ይህን አዘጋጂ ስትባል ከአንድ ቀን በፊት ይነገረኝ ትላለች:: አብርሃም ግን በቤቱ ሙሉ አላፊ ነበር:: ይስሐቅን ሲሠዋ ወደ ሞሪያ ተራራ ሲወጣ ለባለቤቱ ሲያማክር አልተጻፈም:: ልጅም ቢሆን ሙሉ ማንነቱን

ለአባቱ ሰጠ። የሰማይ መልአክ መጥቶ አትረደው ካለው በኋላ ከሞሪያ ተራራ ሲመለሱ ልጁ አባቱን አልተቀየመም። ቆይ ያደረከኝን ሁሉ ለሣራ እነግራለሁም ሲል አልተገኘም። አብርሃም የቤት ኃላፊ ሣራ እናት ይስሐቅ ልጅ ነበረ። አብርሃም ሦስቱን የጌታ መልአክተኞች ከተቀበለ በኋላ ውጤቱ "የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬ ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራም ልጅን ታገኛለች።" እኅቶች ዝም ብለው ባሎቻቸውን አምነው ቢኖሩ ጌታ ቤቱን በሙሉ ኃላፊነት እንደሚወስድ እምነቴ የጸና ነው።



## 18. የጽዮን ቈነጃጅት ጌጣጌጥ

"ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦ የጽዮን ቈነጃጅት ኰርተዋልና፥ አንገታቸውንም እያሰገጉ በዓይናቸውም እያጣቀሱ፥ ፈንጠርም እያሉ፥ በእግራቸውም እያቃጨሉ ይሄዳሉና ስለዚህ ጌታ የጽዮንን ቈነጃጅት አናት በቡሀነት ይመታል፥ እግዚአብሔርም ኀፍረተ ሥጋቸውን ይገልጣል። በዚያም ቀን ጌታ የእግር አልቦውን ክብር፥ መርበብንም፥ ጨረቃ የሚመስለውንም ጌጥ፥ የጆሮ እንጥልጥሉንም፥ አንባሩንም፥ መሸፈኛውንም፥ ቀጸላውንም፥ ሰንሰለቱንም፥ መቀነቱንም፥ የሽቱውንም ዕቃ፥ አሸንክታቡንም፥ የእጅና የአፍንጫ ቀለበቱንም፥ የዓመት በዓልንም ልብስ፥ መጐናጸፊያውንም፥ ልግምበገላውንም፥ ከረጢቱንም፥ መስተዋቱንም፥ ከጥሩ በፍታ የተሠራውንም ልብስ፥ ራስ ማሰሪያውንም፥ ዓይነ ርግቡንም ያስወግዳል። እንዲህም ይሆናል፤ በሽቱ ፋንታ ግማት፥ በመታጠቂያውም ፋንታ ገመድ፥ ጠጕርንም በመንቀስ ፈንታ ቡሀነት፥ በመጐናጸፊያ ፋንታ ማቅ፥ በውበትም ፋንታ ጠባሳ ይሆናል።" (ኢሳ. 3፥16-24)

የጽዮን ቈነጃጅት በእግዚአብሔርና በፍጥረት ላይ የኰራትን መንፈስ ሲገልጡ እግዚአብሔር በተራው ደግሞ ለዚህ በቂ ምላሽን በግልጥነት አስቀምጧል። አንገት ማስገግ፣ በዓይን መጣቀስ፣ በእግርም እያቃጨሉ መሄድ መሠረታዊ መገለጫቸው ነበር። ነቢዩ ኢሳይያስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ700 ዓመት በፊት የኖረ ሰው ሲሆን በዚያን ዘመን የጽዮን ቈነጃጅት ይሄን ያህል ዘመናዊነትና ስልጣኔ ማሳየታቸው በዚህ ዘመን ላሉት ቈነጃጅት አስደናቂ ነው።

የጽዮን ቈነጃጅት መልበሻ ቤታቸው (Dressing room) ከአጫናነቁት መሠረታዊ የውጭ ልብሶችና ጌጣጌጦች መካከል

- የእግር አልቦ
- መርበብ
- ጨረቃ መሳይ ጌጥ
- የጆሮ እንጥልጥል
- አንባር
- መሸፈኛ
- ቀጸላ
- ሰንሰለት
- መቀነት
- የሽቱ ዕቃ
- አሸንክታብ
- የእጅና የአፍንጫ ቀለበት
- የዓመት በዓል ልብስ
- መጐናጸፊያ
- ልግምበገላ
- ከረጢት (ቦርሳ)
- መስታወት
- የጥሩ በፍታ ልብሶች
- ራስ ማሰሪያ
- ዓይነ ርግብ



እንግዲህ አንዲት ቆንጆ ይህን ሁሉ ከውጭ ደርባው ስትሄድ በውኑ ልዩ ፍጡር ሳያስመስላት አይቀርም:: በዚህ ላይ እነዚህን ለማዋሃድ የምትጠቀምባቸው ጥበብ አያሌዎች ይሆናሉ::

እነዚህ የጽዮን ቈነጃጅት የድፍረት ኃጢአትን በኩራት መንፈስ ሲተገብሩ ከእግዚአብሔር ቅጣቶች ውስጥ ዋነኛው አናታቸውን በቡሀነት ማምታት ነው:: ጠጉራቸውንም ተነቅሰው ውበታቸውን ተጐናጽፈው ሲጓዙ አስቀድሞ በቡሀነት ከተመቱ ነገሮች ሁሉ እንክትክቱ ይወጣል:: ሌላው ማቅ፣ ጠባሳነት፣ ግማት ተከታታይ የጥፋት እርምጃዎች እንደሚሆኑ ነቢዩ በመንፈስ አመለከተ::

በሴቶችም ሆነ በወንዶች የውጭ ገጽታ ላይ ዛሬ ሳይሆን ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ከፋዎች እየተፈራረቁ በመጠቀም የእግዚአብሔርን የታላቅነትና የግርማዊነት ክብር ለመጋፋት ያልተሞከረበት ዘመን የለም:: እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ግሩምና ውብ አድርጎ ሲፈጥር የሰው ልጆች ደግሞ በተገቢው ሁኔታ ሰውነታቸውን ሸልመው የፈጠራቸውን አምላክ ክብር በተገቢው ሁኔታና ጊዜ እየገለጡ እንዲኖሩ ሲገባ ነገር ግን በላያችን በዘረጋነው ነገሮች ለራሳችን ፈጣሪው ራሳችን መሰልን::

በተለይም ክርስቶስን የምትከተል የእውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ለዚህች ለጠፊ ዓለም ብርሃንና ጨው ሆነን የሚመጣውን የጽድቅ ዓለም ሰዎች ሁሉ ተስፋ አድርገው እንዲኖሩ ልንገልጥ የተገባን እንደሆነ ከማንኛችንም የተሰወረ አልነበረም:: "ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ

እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።" (1ኛ ዮሐ. 2፥15-16) በዚህ ዘመን አንድ መንፈሳዊ ጉባኤ ተከፍቶ የእምነት አባቶችና የእምነቱ ሕዝብ ተሰብስቦ በዚህ መሀል አንዱ ተነሥቶ ዓለም ወይንም በዓለም ያሉትን መውደድ የለብንም ማንም ዓለምን ቢወድድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ የለም ቢል በእርግጠኝነት ይህ እብድ ከየት መጣ እንደሚባል እገምታለሁ። ነቢዩ ኤልሳዕ የላከው ነቢይ በእስራኤል ሽማግሌዎች የተባለው ትዝ ካለን "ኢዩም ወደ ጌታው ባሪያዎች ወጣ፤ እነርሱም፦ ደህና ነውን? ይህ እብድ ለምን መጣብህ? አሉት።" (2ኛ ነገሥ. 9፥11)

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ወንድሞችና እኅቶች በየጎዳናውና በየሥፍራው የጌታን ቃል ለዓለም ይዘው ይወጣሉ። በዚህን ጊዜ በክርስቶስ ያመኑና የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነትና የማዳንን ተግባር ለመመሥከር ይሠማራሉ። በዚህን ጊዜ ሰውነታቸውን በፍጹም ግሩም የሆነ አለባበስ ሥርዓት የተካኑ ሴቶች ነገር ግን ከክርስትና እምነት ውጭ የሆኑ ይገኛሉ። ክርስቲያን ኅእኅት ደግሞ አስቀድመን ነቢዩ ኢሳይያስ እንደገለጣት የጽዮን ቈነጃጅት ራስዋን ከልክ በላይ አስጊጣ ይገናኛሉ። እንግዲህ "አንቺ ሴት ወደዚህ ጌታና ንጉሥ ተመልከቺ እኔን ከዚህ ዓለምና ከእርኩሰትም ያስመለጠኝን ጌታ ወደ ውስጥሽ አስገቢ" በማለት ብትመሠክርና ፍፁም ክርክር ቢነሳ ሦስተኛ ሰው መጥቶ ቢያደምጣቸው ማን ለማን እየመሠከረ ነው?

እግዚአብሔር ስለውስጥ ማንነታችን እንጂ ስለውጪ ማንነታችን አይመለከትም የምንል ከሆነ ከውጭ የሚታየው



የውስጡ ነጸብራቅ እንደሆነ መጽሐፍ ይገልጣል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ወንድና ሴት ጠጉር ለምን አስተማረ? ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለሴቶች ጠጉርና አለባበስ ስለምን አስተማረ? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "እነሆ፥ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ።" (ማቴ. 11፥8) በማለት እነዚህ ሰዎች መጥምቁ ዮሐንስ ዘንድ ወይንም ሐዋርያት ዘንድ ሳይሆን ይሁዳ ነገሥታት ቤት ፈልጉአቸው ያለው ለከንቱ ይሆን?

በዚህ ዓለም ያለች ቤተክርስቲያን ይህን የጌጥና የአለባበስ ሥርዓት ቸል ያለችበት ምክንያት ይኖራል። አስቀድሞ ከዚህ ይልቅ አውራ ኃጢአትና አንኳር ዓመፃ በበዛበት ወቅት ይህን ጉዳይ እንደ ሞት ቀጠሮ አንገብጋቢ አይደለም። ጌታ ፈሪሳውያኖችንና ጻፎችን ሲያስጠነቅቅ "... ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ ... እናንተ ዕውሮች መሪዎች ትንኝን የምታጠሩ ግመልን የምትውጡ።" (ማቴ. 23፥23-24) አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ከሁሉ አስቀድሞ ሕጉም ጸጋውም የሚጠይቀው ፍርድ፣ ምሕረትና ታማኝነት ነው። እነዚህን እንደ ግመል ሕጎች ብንመለከት (ወይንም በዘመኑ ቋንቋ ሕገ መንግሥት) ሌሎቹን እንደ አዋጆችና መመሪያዎች እንመልከት። ነቢዩ ዘካሪያስም ይህንን ምክር ተናግሮታል። "የምትሠሩት ነገር ይህ ነው፤ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ

በበር አደባባያችሁም የእውነትንና የሰላምን ፍርድ ፍረዱ፤ ሁላችሁም በባልንጀራችሁ ላይ ክፉን ነገር በልባችሁ አታስቡ፤ የሐሰትንም መሐላ አትውደዱ ይህን ነገር ሁሉ እጠላለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር።" (ዘካ. 8፥16-17)

እኔ ልጅ ሆኜ ሰዎች ሲያወሩልኝ ከነበረው ተነስቼ ስለ ጻድቃንና መንግሥተ ሰማያት ስለሚገቡ ሰዎች ሲነገረኝ በአእምሮዬ ይቀረጽ የነበረው፦ ቅጠል የሚበሉ፣ አልፎ አልፎ እንደ መስቀል ወፍ የሚታዩ፣ የሰውነታቸው አካል ፈጽሞ የተሸፈነ፣ ቤቶቻቸው በየተራራውና ገደል የሆነ፣ እጅግ በጣም ከሲታዎች፣ በጣም የሚጸልዩ፣ የሚጦሙ፣ እንቅልፍ የማያሸንፋቸው ይመስለኝ ነበር። አሁን ግን በጌታ ቤትና መጽሐፍ ራሴን ሳገኝ እኛ ክርስቲያን ተብለን የተቀመጥን ሰዎች ለጌታና ለቃሉ ፈጽሞ ደንታ አጥተን መደበኛ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ ሥርዓትና ሕግ ሲኖረን ይገባናል ስንባል ፈጽሞ ማንም በኛ በውጭ ጌጣጌጥና አለባበስ ሊመክረን አይገባም ካልን በጣም አስደንጋጭ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ በዚያ ዘመን አንድ ሰው በእርሱ ምክንያት እንዳይሰናከል የመጨረሻውን ጥንቃቄ አደርጋለሁ ይለናል። "ስለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፥ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።" (1ኛ ቆሮ. 8፥13) ሥጋ መብላት ማንንም አያሰናክልም ነገር ግን ይህ ወንድሜን



የሚያሰናክል ከሆነ ዋናው የምግብ ኃይል የሆነውን ሥጋ ለዘላለም አልበላም ይላል። እኛ ግን ለወንድማችን ወይም ላልዳኑ እኅቶቻችን በውጭ ባለው ብዙ ነገራችን የምናሰናክል ከሆነ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ለዘላለም ማሰናከያን እናነሳለን።

እንግዲህ የጽዮን ቈነጃጅት እናት በበሁነት ለመቅጣት የትንቢት ቀጠሮ ለነቢዩ ኢሳይያስ ከተሰጠው ይህ ትንቢት በኛ ላይ ፈጽሞ እንዳይደርስ በጌታና በመንግሥቱ ላይ ፍጹም ትህትና ልንላበስ ይገባል። እግዚአብሔርም ለትሁታን ጸጋን የሚሰጥ ከሆነ በጸጋ ተከናንበን እንጂ በቁሳቁስ ራሳችንን ከልለን እንዳንገኝ በዚህ ልንተጋ በተገባን!

# 19. በጠጕር የታበሰ እግር

አንዲት ሴት በኢየሱስ በምድር ወቅት ለኢየሱስ ክብር ሽቱ እንዳፈሰሰች በአራቱም ወንጌላት ተጽፎ እናገኛለን። አራቱም ወንጌላት ስለዚህ ጉዳይ የተለያዩ ዘገባዎችን ይዘዋል።

## ሀ. የቅዱስ ማቴዎስ ዘገባ

"... ለደቀ መዛሙርቱ፦ ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ፥ ... ኢየሱስም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች በማዕድም ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተቈጡና፦ ይህ ጥፋት ለምንድር ነው? ይህ በብዙ ዋጋ ተሽጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና አሉ።" (ማቴ. 26፥2-9)

## ለ. የቅዱስ ማርቆስ ዘገባ

"ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካና የቂጣ በዓል ነበረ። ... እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ ስምዖን ቤት በነበረ ጊዜ፥ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የከበረ ጥሩ ናርዶስ ሽቱ የመላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ መጣች ቢልቃጡንም ሰብራ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። አንዳንዶችም፦ ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድር ነው? ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሽጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና ብለው በራሳቸው ይቈጡ ነበር፤ እርስዋንም ነቀፉአት።" (ማር. 14፥1-5)



## ሐ. የቅዱስ ሉቃስ ዘገባ

"ከፈሪሳውያን አንድ ከእርሱ ጋር ይበላ ዘንድ ለመነው፤ በፈሪሳዊው ቤትም ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ። እነሆም በዚያች ከተማ ኃጢአተኛ የነበረች አንዲት ሴት በፈሪሳዊው ቤት በማዕድ እንደ ተቀመጠ ባወቀች ጊዜ፥ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ አመጣች። በስተ ኋላውም በእግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርስ ጀመረች፥ በራስ ጠጕርዋም ታብሰው እግሩንም ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበረች። የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፦ ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ። ... እርስዋንም፦ ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል ... እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት።" (ሉቃ. 7፥36-50)

## መ. የቅዱስ ዮሐንስ ዘገባ

"ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ ... ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። ነገር ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፦ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ። ..." (ዮሐ. 12፥1-8)

የነዚህ አራት ጸሐፊዎች አጻጻፍ ዘይቤያቸውን ተመልክተን የጌታን አሰራር በተለያየ መንገድ መገንዘብ እንችላላን:: አንደኛው ጸሐፊ አንዲት ሴት እያለ ሲዘግብ ሌላኛው ደግሞ ማርያም (የነአልዓዛር እኅት) መሆንዋን ይገልጻል:: አንዱ ጉዳዩ የተፈጸመበትን ቤት ሲናገር በፈሪሳዊ ቤት በማለት ሲዘግብ ሌላኛው ደግሞ ለምጻሙ ስምዖን ይለዋል:: አንደኛው የሽቱውን ዋጋ በደፈናው ዋጋው እጅግ የከበረ በማለት ሲገልጥ ሌላው ከዋጋው ተመን ጋር 300 ዲናር ይለናል:: አንደኛው ጸሐፊ ሽቱውን ሴቲቱ ስታፈስሰው ይህ ሁሉ ጥፋት ለምንድር ነው የሚል ድምፅ ተጽፏል ነገር ግን ቃሉን የተናገሩት ደቀ መዛሙርቱ ይላል ሌላው አንዳንዶቹ ይላል ዮሐንስ ደግሞ ራሱ ደቀ መዛሙርት በመሆኑ አስቆርቱ ይሁዳ ይህን ቃል የተናገረው እርሱ ሌባ ስለሆነ እንጂ ለድሆች አስቦ አይደለም በማለት በግልጥ ያስቀምጣል:: እንግዲህ ይህን ዓይነት መለያየት ለምን ይፈጸማል? የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ስለሆነ አራቱም ወንጌላት ይህን ጉዳይ ከጸፉት የካርቦን ግልባጭ መሆን ይገባዋል በማለት ይናገራሉ:: ነገር ግን አራቱ የተለያየ አጻጻፍ መስመር ይዘው እንዲሄዱ የሚያስገድዱ ጉዳዮች አሉ:: በመጀመሪያ ዘገባው የተካሄደበት ቦታ ላይ ብዙ ሰዎች አሉ:: አንደኛው ጸሐፊ ከታደሙት ውስጥ የአንዱን ሰው አባባል በግልጥ ያስቀምጣል:: ሌላው የትኩረት አቅጣጫ በሴትየዋ ላይ ይሆንና ይህን ያደረገችው ማርያም ነች በማለት ሲገልጥ ሌላው ደግሞ አንድ ኃጢአተኛ ሴት ፈውስ የምትሻ በማለት ያሳጥረዋል:: ሰባት አጋንንት የወጣላት ሴት መባል እንጂ ስም መጥቀስ በመጽሐፍ አይገባም የሚል ጸሐፊ አለ::



ነገር ግን ጥንቃቄ የሚጠይቀው ጉዳይ ሁለቱ ጸሐፊዎች (ማቴዎስና ማርቆስ) ሽቱው የፈሰሰው በኢየሱስ ራስ ላይ ነው በማለት ሲናገሩ ዮሐንስ ደግሞ እግሩን ቀባች በማለት ሲገልጥ ሉቃስ ደግሞ እግሩን በእንባዋ እንደምታርስና ሽቱ እንደምትቀባው ይናገራል:: ይህን ለማስማማት እንደ እኔ አሳብ ይህች ሴት ብዙ መጠን (volume) ያለው ሽቱ ይዛ ጠጉሩን፣ ሰውነቱን፣ እግሩንና አካሉን በሙሉ ስትቀባ አንደኛው ትኩረት የሰጠው በእግሩ የፈሰሰው ሲሆን ሌላው ግን ራሱ ላይ ነው:: ይህን ልናገር የቻልኩት በማጠቃለያ ኢየሱስ ሲናገር "እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች" በማለት ተናገረ:: በእስራኤል ባህል ደግሞ የመቃብር ሽቱ የሚቀባው ሰው ሲሞት መላ አካላቱን ነው:: በኢየሱስም ሰውነት ሁሉ ላይ ሽቱው ሲፈስ ራሱና እግሩ ላይ በብዛት ፈስሶ ይሆናል ጸሐፊው አንዱን ሲጠቅስ ሌላው ደግሞ ሌላኛውን እንጂ ምንም አልተቃረነብኝም:: ከሉቃስ በስተቀር ሦስቱም ስፍራውን በግልጥ ተናግረዋል ቢታንያ ነበር:: ሰዓቱም ዮሐንስ እንደ ገለጠው በራት ሰዓት ነበር::

በሉቃስ ወንጌል መሠረት ሴቲቱ የቆመችው በኢየሱስ ኋላ ሆኖ እግሩን በእንባ እያራሰች ሽቱ ትቀባው ደግሞም እግሩን ትስመው ነበር:: ለዚህ ሁሉ ማጠቃለያ በጠጉርዋ ታብሰው ነበር:: በሽቱ፣ በእንባ፣ በመሳም፣ በእግሩ የፈሰሰው ፈሳሽ ሊወለወል እንደሚገባው በማወቅ የሴት ልጅ ክብር ("ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንካ አያስተምራችሁንም? ጠጉርዋ መጐናጸፊያዋ እንዲሆን ተሰጥቶአታልና::") (1ኛ ቆሮ. 11፥15) በሆነው

ጠጉርዋ የጌታን እግር አበሰች። ለኔ ክብር የእርሱን እግር ማበሻ እንጂ ሌላ አይደለም።

ዓለም በሙሉ ከሁለት ቀናት በኋላ መድኃኒያለም ክርስቶስን ይሰቀል! ይሰቀል! እያለ ሊጮኽበት ሲቃረብ ይህች ሴት ግን አስቀድማ ለክርስቶስ ያላትን ፍቅር በተግባር ስትገልጥ እጅግ አስደናቂ ነው። መናገር የለም ድምጽም የለም ነገር ግን ቃልዋ እስከ ሩቅ አገርና ዘመን እንዲሰማ አደረገች። ይህንን እድል ጌታ ለሁሉ ሰጥቶ ሳለ የቅብዓ ቅዱስ ሥርዓት ያለ አንዳች አጋዥ ለመቃብሩ ቀባች። እርስዋ የእነርሱን ጌታና ንጉሥ እንዲህ ልታስውብ በጠጉርዋና በገንዘብዋ ስታገለግል ደቀ መዛሙርቱ ግን ይህ ሁሉ ጥፋት ለምንድር ነው በማለት ተናገሩ። ለክርስቶስ ክብር የተደረገውን ጉዳይ ይህ ሁሉ ጥፋት ብለው ተናገሩ። ክርስቶስ ግን ለማንም ያላካፈለውን ክብር ተካፋይ ሆነች። "እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበክበት እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።" (ማቴ. 26፥13) ዛሬም በአንተና በነገርህ ላይ የጌታ ሽቱና ቅባት ሲያርፍ፣ የሚቃወሙህ ደቀ መዛሙርት እንጂ ከውጭ አትጠብቅ። የአንተን በረከት ይህ ሁሉ ጥፋት ለምንድር ነው በማለት በጸሎት ሪፖርት ያደርጋሉ።



# 20. የጌታ ኢየሱስ ጠጉር

"በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ፥ ... ራሱና የራሱ ጠጉርም እንደ ነጭ የበግ ጠጉር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፥" (ራእ. 1፥13-14)

"ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፥ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፤ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ፥ የራሱም ጠጉር እንደ ጥሩ ጥጥ ነበረ፤ ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፥" (ዳን. 7፥9)

## 20.1. የመጨረሻው መልእክተኛ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመጣበት ዓላማዎች አንደኛው የወይኑን ፍሬ ከተከራዩት ገበሬዎች ተቀብሎ ለባለርስቱ ለሆነው ለእግዚአብሔር በወቅቱ ለማስረከብ ነው። የእግዚአብሔርን ድርሻ ለመቀበል አስቀድሞ ብዙ መልእክተኞች ተልከዋል። በመጨረሻም አንድያ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደ ምድር መጣ በዚህ ምክንያት የተከራዩት ገበሬዎች ለባለርስቱ ወይን ፍሬ እንዳይጠየቁ ልጁን ገደሉት። "የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረው፤ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ እርሱን ከሁሉ በኋላ ወደ እነርሱ ላከ። ... ይዘውም ገደሉት፥ ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ ጣሉት።" (ማር. 2፥6-8) ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ሆኖ ሳለ ነቢያት፣ ነገሥታት፣ ሌዋውያንና ካህናት ተልከው ካለቁ በኋላ በመጨረሻ የመጣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። ሊታፈርና ሊፈራ እንደሚገባው እግዚአብሔር በማመን ልጁን በጨካኞች እጅ ጣለው። በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ ሊፈራና ሊከበር፣ ሁሉ ሊሰግዱለትና

ሊታዘዙለት እንደሚገባ የወይኑ አትክልት ባለቤት እግዚአብሔር ያምናል። የተከራዩ ገበሬዎች የኢየሱስን ታላቅነት ተመልክተው ከወይኑ ፍሬ በጊዜው ሊያስረክቡ ይገባቸው ነበር።

እኛም ስለመለኮታዊ ጠጉር የተለያዩ ሰዎችን ከተመለከትን በኋላ በመጨረሻ ሊታፈርና ሊከበር የሚገባውን የክርስቶስን ውበት መግለጫና መከበሪያ የሆነውን ጠጉሩን በሥርዓቱ ልንመለከት ይገባል። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጠው ውበት ውስጥ መከበሪያ ያደረገው ጠጉርን ነው። ጠጉር የሰውን ራስ የሚሸፍን ከመሆኑም በላይ በጠጉር የሚታየው ሽበት የእድሜ ባለጠግነትና መከበሪያ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ለሰዎች በአናታቸው በሚኖር ጠጉር ላይ አስቀምጦታል። የሁሉ ነገር ማጠቃለያ በመሆኑም የመጨረሻውን መልእክተኛ ውበት ብንመለከትና ብንታዘዝ በረከታችን የሰፋ ይሆናል።

## 20.2. ሽበት

"በሽበታም ፊት ተነሣ፥ ሽማግሌውንም አክብር፥ አምላክህንም ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።" (ዘሌዋ. 19፥32)

"የጎበዛዝት ክብር ጉልበታቸው ናት፥ የሽማግሌዎችም ጌጥ ሽበት ነው።" (ምሳ. 20፥29)

የእስራኤላውያን ጠጉር በልጅነት ጥቁር ይሆናል ሲሸመግሉም ወደ ነጭነትና ሽበታምነት ይሸጋገራሉ። የመጽሐፍ ቃል የሚያስጠናንም የእስራኤልን ታሪክ እንጂ የሌሎችን አሕዛብ አይደለም። እንግዲህ የእስራኤል ዕድገት ከጥቁር ወደ ነጭነት ነው የቀን አቆጣጠራቸውም ከጥቁር ወደ ነጭ ይሆናል "ነታም" ሆነ



ጠዋትም ሆነ የሚል እናገኛለን። በነጭ ሽበት ወደ መቃብር መውረድ በረከት ነው። በነጭ ሽበት ወደ መቃብር ሲጓዙ ግን በደስታና በምሥጋና እንጂ በኀዘን መሆን የለበትም። ያዕቆብ ይህን አስመልክቶ ለልጆቹ ሲናገር "ሽምግልናዬን በኀዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ።" (ዘፍጥ. 42፥38) ሽምግልና በክብር ወደ መቃብር የሚወርድበት እንጂ በኀዘን መሆን የለበትም። ያዕቆብ ግን ልጁ ዮሴፍ በመጥፋቱና ብንያምን አምጣ በመባሉ ይህን ቃል ተናገረ። ዮሴፍንና ብንያምን መልሶ ካገኘ በኋላ ግን ሽምግልናው በደስታ ወደ መቃብር ወረደ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ያዕቆብ በዚህ ዕድሜው ዮሴፍን ሲያገኝ በጌሤም ምድር የተናገረው ይገልፅልናል። "እስራኤልም ዮሴፍን፦ አንተ ገና በሕይወትህ ሳለህ ፊትህን አይቻለሁና አሁን ልሙት አለው።" (ዘፍጥ. 46፥30)

ሽምግልና ወይንም ሽበት ታላቅ ጌጥ ሲሆን የዕድሜ ባለጠግነትና ሁሉን የማወቅ ምሥጢር የሚገለጥበት ነው። እግዚአብሔር የሰዎችን ልጆች ዕድሜ በማርዘም ያምናል ይህም ከሁሉ የሚሻል በረከት ነው። "ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር።" (ኤፌ. 6፥3) ይህ የአዲስ ኪዳንም ተስፋ ነው። በምድር ዕድሜ ሲረዝም የእግዚአብሔርንም የሰውንም፣ የአገርንም ሥራ ባልተጣበበ መልኩ የሚሠራበት ነው ሁሉን ለማየትና ለማወቅ ለመለማመድ ለሰው ልጅ ዕድሜና ጤና ወሳኝነት አለው። ይህ ደግሞ በሁሉ ዘንድ የሚታመንበት ነው።

አንድ እስራኤላዊ አንድን ሽበታም ሰው በመመልከት ብቻ ከወንበሩ ይነሳል። በሽበት ብቻ መከበርን ያገኛል። ሽበት ደግሞ

የተገለጠ ስፍራ የተቀመጠ በመሆኑ አንድ ሰው ለመከበር የሚያደርገው መሯሯጥ የለም። የተገለጠው ሽበት መከበሪያ ነው። ይህን ክብር ያስቀመጠ እግዚአብሔር ነው። በሽበታሙ ፊት ተነስቶ ለሽበታሙ ስፍራን መተው የእስራኤል መለኮታዊ ሕግ ነው። ነጭ ጠጕር ያለው ሰው ማረፊያ ለማግኘት ብዙ ምቹ ሁኔታ አለው።

የጎበዛዝት ክብር በጉልበታቸው ከሆነ የሽማግሌዎች ደግሞ በጠጕራቸው ከሆነ የሰው ዕድገት ከጉልበታምነት ወደ ነጭ ጠጕር ጸጋ ነው። ከጉልበት ወደ አእምሮ እድገት ይሆናል። ጉልበትን ወይንም ኃይልን ይገልጥ የነበረ የሰው ልጅ ወደ ሽበትና ወደ ብስለት ይሸጋገራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ የሚገልጥልን ነገር አለ። "... ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ፥ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም። በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን ..." (1ቆሮ. 2፥3-5)

የሐዋርያው ዮሐንስንም ዕድገት ስንመለከት በመጀመሪያዎቹ አገልግሎት ዘመኑ ስለመንፈሳዊ ጉልበት የሚያሳይ ነው። በሽተኞችን ሲፈውስ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ሲጸልይ ወዘተ። በሽምግልናው ወቅት ግን የሚያስደስተው ሆኖ ያገኘው "እውነትን" ነበር። ሽማግሌው ዮሐንስ የሚናገረው የመንፈስ ኃይል ሳይሆን የመንፈስን ፍሬ ነበር። "ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም።" (3ኛ ዮሐ. ቁ.4) የእግዚአብሔር መንፈስ ጉልበት ሰዎችን በእውነት እንዲሄዱ የወረደ ጸጋ ነው። ጌታ ኢየሱስም ወደ ምድር የመጣው ስለ እውነት ለመመስከር ነው። ሰይጣንም የሐሰት አባት በመሆኑ



በእውነት አልቆመም በመሆኑም የሰይጣንን ሥራ የሚያፈርስ እውነት ነው።

## 20.3. በዘመናት የሸመገለው

የኢየሱስ ክርስቶስ ጠጕር እንደ ጥጥ፣ እንደ በረዶ፣ እንደ ነጭ የበግ ጠጕር መሆኑን ነቢዩ ዳንኤልና ሐዋርያው ዮሐንስ ገልጠውታል። እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ በዘመናት የሸመገለ በመሆኑ የክርስቲያኖች ዕድገት ወደዚህ ይሆናል። «ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ...» (ኤፌ. 4፥13)

አንድ ክርስቲያን ጌታን ሲቀበል እንደ ህፃን ይሆናል። ከምንም ወደ ጥቁር ጠጕር ያድጋል ሕፃን ሲወለድ ጠጕሩ በፊቱ ድፍት ያለ ከመሆኑም በላይ ስስና ዘርዛራ ነው። በፍፁም ከጭንቅላቱ ጋር የተዋሃደ እስከማይመስል የሚኖር ነው። ከዚያም እየጠነከረና እየበዛ ይመጣል። በጎልማሳነት ወቅት ወደ ግብስማ ይሸጋገራል ከረጅም እድሜ በኋላ ወደ ፍፁም ነጭነት ይለወጣል።

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመጣ በነገር ሁሉ እኛን መስሎ ነው። "በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው" (ዕብ. 2፥17) ጌታ ራሱን ስለ እኛ ቀደሰ። እኛ እርሱን እንመስል ዘንድ እርሱ እኛን መሰለ። ከህፃንነት ጀምሮ እስከ ሽምግልና እኛን ለመምሰል ራሱን ስለ ለየ በሁሉ እኛን መሰለ። "እስከ ሽምግልና እኔ ነኝ" (ኢሳ. 46፥4) አንድ መንፈሳዊ ሰው በጌታ አዲስ ልደት ሲወለድ ጌታ እርሱን መስሎ ይገለጥለታል። ሕፃናት ከሕፃናት መጫወት እንደሚወዱ በመንፈስ አዲስ ልደትን ያገኙ ከሕፃኑ ኢየሱስ ጋር መጫወትን ይመርጣሉ።

በናዝሬት ያደገው ኢየሱሰ ከዚህ ሰው ጋር ይሆናል:: ይህ ሰው ሲያደግ የክርስቶስም በዚሁ ልክ ከፍ ብሎ ይገለጥለታል:: በመጨረሻም በመንፈሳዊ ዕድገታቸው ከፍተኛ ደረጃ ለደረሱ እነርሱን መስሎ ነጭ ጠጕር ሆኖ ይገለጣል::

ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነጭ ጠጕር ሆኖ የተገለጠው ለሽማግሌዎችና ለሚወዳቸው ለሐዋርያው ዮሐንስና ነቢዩ ዳንኤል ነው:: በነቢያት መጽሐፍም ቢሆን ለሽማግሌው ነቢዩ ዳንኤል ወይንም ለሽማግሌው ሕዝቅኤል ነው:: በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሁሉ በሁሉ ነው መንፈሳዊ ታላቅነትም ሁሉ በሁሉ ለመሆን መዘጋጀት ነው:: ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያው ጴጥሮስን አንድ ጥያቄ ጠየቀው "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው:: አዎን ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው::" (ዮሐ. 21፥15) የዮና ልጅ ስምዖን ከሁሉ ይልቅ ጌታን ከወደደ ግለገሎችም፣ ጠቦትም፣ በጎችም፣ ጠባቂና እረኛ ይሆናል:: ጴጥሮስ ለሁሉ እንደ ሁሉ ይሆናል::

ከሁሉ ይልቅ ጌታን መውደድ ማለት ከበጎች ጋር መዋል መቻል ይመስለኝ ነበር አሁን የተረዳሁት ግን ከሁሉ ይልቅ ጌታን መውደድ በዘመናት መሸምገል ሲሆን የዚህም ውጤት ለሁሉ እንደ ሁሉ መሆንን ያሳያል:: የዮና ልጅ ስምዖን በመጀመሪያ አደራ የተሰጠው ለበጎች ሳይሆን ለግልገሎች ነው::

ጌታ ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን ከፈፀመ በኋላ ደመና (ነጭ) ሰውራ ተቀበለችው በክብር ጨረሰ:: በመንፈሳዊ ዓለም አንድ ሰው እንዲደርስበት የተፈለገበትን ደረሰ:: ነጭ የበግ ጠጕር የሚመስልን



ጠጕር ተሸክሞ በክብር ዙፋኑ ተቀመጠ:: ፍርድን እንዲያደርግ የክብር ዙፋኑ ላይ ተቀመጠ:: ሕፃናት አይፈርዱም በዘመናት የሸመገለ ግን ይፈርዳል፤ ሁሉን ስለሚያውቅ ፍርድን አያዛባም:: እግዚአብሔር በክርስቶስ ጸጋ እንድናድግ ሁልጊዜ የሚከተከቱተን በዘመናት ወደ ሸመገለው እንድንደርስ ነው:: መለኮታዊ ጠጕራችን ከጥቁርነት ወደ ሽማግሌዎች ውበት እንዲደርስ ነው::

የፍርድ ቀን ጌታ ይህን ጠጕር ይዞ ሲገለጥ ሁሉ በሽበታሙ ፊት ይነሳል:: በምድር ኃያላን ነን ያሉ ሁሉ ከወንበራቸው ለጠጉሩ ክብር ይነሳሉ ጌታ ይቀመጣል:: ሁሉ ፍርዱን ይቀበል ዘንድ ይቆማል:: የመጽሐፍ ቃልም "አሕዛብ ሁሉ በፊቱ እንዳልነበሩ ናቸው ከምናምን እንደሚያንሱ፥ እንደ ከንቱ ነገርም ይቆጥራቸዋል::" (ኢሳ. 40፥17)

ሶምሶን ከልጅነቱ ጀምሮ የበቀለው ጸጋ በሰባት ጎንጉኖ እንደያዘው እኛም የጠጉራችን ጥቁረት ወደ ነጭነት ተቀይሮ እግዚአብሔር እስከወሰነልን ዕድሜ እየጎነጎንን እንድንኖር ጌታ ይርዳን:: እነ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከክርስቶስ መከራ እስከ መጨረሻው በመታገሳቸው ዙፋናት እንደ ተዘረጋላቸው በዚህ ዘመንም ያለን ክርስቲያኖች ክርስቶስን እስከ መጨረሻው በመከተል የክብር ዙፋን ላይ አብሮ ይቀመጥ ዘንድ ድል መንሳት ይገባናል:: ድል መንሳት መለኮታዊ ጠጕርን ጠብቆ እስከ መጨረሻው አሳድጎና ጉንጉኖ ማቆየት ነው:: በእሳት ነበልባል ዙፋኖች ለመቀመጥ የእሳት ነበልባል የሆነችውን ዓለም በክርስቶስ ጸጋ ማሸነፍ ይጠይቃል:: አሜን!

በሌላ ርዕስ በጌታ ጸጋና ቸርነት ዳግመኛ እንገናኛለን::